# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 84ኛ ዓመት ቁጥር 106 ታኅሣሥ 16 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50 ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# የናይል ወንዝ ተፋሰስ ኮሚሽን ምሥረታን ለማፋጠን


አስቴር ኤልያስ


**ዜና ትንታኔ**

የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ወደተፈጻሚነት ከገባ ሁለት ወር ሞልቶታል። ማሕቀፉ ሕግ ሆኖ መጽደቁ ኢትዮጵያን ጨምሮ በወንዙ ውሃ ፍትሃዊ አጠቃቀም ዙሪያ ጥያቄ ላላቸው የተፋሰሱ ሀገራት ታሪካዊ ድል እንደሆነ ይታመናል።

ኮሚሽኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተቋቁሞ ወደሥራ እንዲገባ ኢትዮጵያ የትብብር ማሕቀፉን በመመሥረት የነበራትን የመሪነት ሚና ዳግም መጫወት እንዳለባት የዘርፉ ምሁራን በስፋት ይናገራሉ። ግብጽ የኮሚሽኑን መመሥረት ለማደናቀፍ የተጀመረውን ሴራ መከላከል የሚቻለው ይህን በማድረግ እንደሆነ ይመክራሉ።

አቶ ፈቂአሕመድ ነጋሽ የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያው ናቸው። እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ ግብጽና ሱዳን መጀመሪያ ላይ ድርድሩ ውስጥ የገቡት በቅኝ ግዛት የደለደሉትን ውሃ እውቅና እናስጣለን በሚል ነበር። እንደተጀመረም አካባቢ የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት እነርሱን የመደገፍ አዝማሚያ ያሳዩ ስለነበር የተሳካላቸው መስሏቸው


የናይል ወንዝ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# ለኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ የፈረንሳይ አበርክቶ


ኢያሱ መሰለ


ከሰሞኑ የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በባሕር በር ጉዳይ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ከፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን የሚጨበጥ ውጤት እንደሚጠብቅ ገልጸውላቸው ነበር፤ ፕሬዚዳንቱም ለጥያቄው አዎንታዊ ምላሽ እንደሰጧቸው ይታወሳል።

ለመሆኑ ፈረንሳይ ኢትዮጵያ የባሕር በር እንድታገኝ ተጽዕኖ ፈጣሪነቷ ምን ያህል ነው? ሚናዋንስ እንዴት ልትወጣ ትችላለች? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ ምሁራን አስተያየት እንዲሰጡባቸው አድርገናል።

በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ምሁር ዓለምሰገድ ደበሌ (ዶ/ር) እና


ለኢትዮጵያ የባሕር በር ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል


# «የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ተወካዮች በኦሮሚያ የአጀንዳ ማሰባሰብ መድረክ መሳተፉ ትልቅ ስኬት ነው»

- መስፍን አርዓያ (ፕሮፌሰር)
የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር


መዓዛ ማሞ


**አዳማ፡-** ከኦሮሚያ ክልል መንግሥት ጋር በቅርቡ የሰላም ስምምነት ያደረገው የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ተወካዮች በኦሮሚያ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ መሳተፋቸው ትልቅ ስኬት መሆኑን ኮሚሽኑ ገለጸ።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ(ፕሮፌሰር) የኦሮሚያ ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ መጠናቀቁን አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ ፤ በትጥቅ ትግል ላይ ያሉ ወገኖች በምክክሩ እንዲሳተፉ ለማድረግ በተደጋጋሚ ዝግጁነቱን ሲገልጽ ቆይቷል። በቅርቡ ከኦሮሚያ ክልል መንግሥት ጋር ስምምነት ያደረገው የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት አመራሮች ተወካዮች በምክክሩ መሳተፋቸውም ትልቅ ስኬት እንደሆነ አስታውቀዋል።

ምክክር አንዱ ተሸናፊ አንዱ አሸናፊ የሚሆንበት ሂደት ሳይሆን ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት መድረክ መሆኑን



የተናገሩት ዋና ኮሚሽነሩ፤ ምክክሩ በመደማመጥ፣ ከስሜታዊነት ይልቅ ምክንያታዊነትን በመላበስና መተዛዘንን በማስቀደም ወደ መግባባት የምንደርስበት መንገድ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ዋና ኮሚሽነሩ ገለጻ ፤ ከታህሳስ 7 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ የነበረው የኦሮሚያ ክልል አጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ከሰባት ሺህ በላይ ተሳታፊዎችን በማወያየት ታሪካዊ መድረክ ሆኖ ተጠናቋል።

ምክክሩ በአራት ትልልቅ ክላስተሮች ተከፋፍሎ መካሄዱን ተናግረው 5 ቀናት በወሰደ ሂደት 640 የምክክር ቡድኖች ተዋቅረው ነጻና ግልጽ ውይይት ማድረጋቸውን አመልክተው፤ አጀንዳዎችን የመለየት ሥራዎች በየቡድኑ በአግባቡ መከናወኑን ተናግረዋል። በየቡድኑ የተደራጁ እና የተጠናቀሩ አጀንዳዎችን ለኮሚሽኑ አስረክበዋል።

እንደ ዋና ኮሚሽነሩ ገለጻ ፤በቀጣይ ለሚከናወነው ሀገራዊ የምክክር ጉባዔም 320 የህብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች፣12 የሃሳብ መሪዎች እና ታዋቂ ግለሰቦች ተወካዮች፣ 31 የመንግሥት ተወካዮች እና ሌሎችም ተመርጠዋል።

ምርጫው ከፍተኛ ፉክክር የታየበት ግልጽ እና አሳታፊ እንደነበር ገልጸው፤ በአሁኑ ወቅት ተወካዮቻቸውን


«የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# ታታሪዎቹ የምዕራብ አባያ አርሶ አደሮች

ማህሌት አብዱል

**ዜና ሐተታ**

በደቡብ ኢትዮጵያ ጋሞ ጎፋ ዞን ምዕራብ አባያ ወረዳ የቆላ ሙላቶ ቀበሌ ነዋሪው አርሶአደር ዳዊት ገሳ እንደወትሮ ሁሉ ማልደው ተነስተዋል። ከዓመታት ልፋት በኋላ ተፈጥሯዊ ልምላሜው በተመለሰለት ሃደቼ ተፋሰስ ተራራ ላይ ከሚገኘው የማህበራቸው የንብ መንደርም ሲደርሱ ማንም አልቀደማቸውም። ነጩን ጋዋናቸውን ከራስ ቅላቸው እስከ እግራቸው ድረስ ተላብሰውና ቦት ጫማቸውን ተጫምተው የማነብ ሥራቸውን ጀምረዋል።

ብዙም ሳይቆይ ሌሎችም የማህበሩ አባላት የሊቀመንበራቸውን እግር ተከትለው ከንብ መንደሩ ተሰይመዋል። የተለመደውን አካባቢውን የማፅዳትና የመንከባከብ ሥራቸውን በጋራ አከናወኑ። በኋላም ለቆረጣ የደረሰውን ማር በተሻለ ጥራትና ዋጋ ለገበያ በሚያቀርቡበት፤ የገቢ አቅማቸውን በሚያሳድጉበት ሁኔታ ላይ በአርሶ አደር ዳዊት መሪነት ምክክር ያካሂዳሉ።







አርሶ አደር ዳዊት እንደሚሉት፤ የሃደቼ ተፋሰስ እንዲህ እንደዛሬው ውብና ማራኪ ከመሆኑ በፊት ደኑ በመናመኑና በመራቆቱ ምክንያት ብሎም የአባያ ወንዝ ሙላት እያደገ በመምጣቱ አብዛኛው የቀበሌዋ ነዋሪዎች የጎርፍ አደጋ ተጋላጭ ነበሩ። እርሳቸውን ጨምሮ የበርካታ አርሶአደሮች ማሳ በተደጋጋሚ በጎርፍ በመጥለቅለቁ የመንግሥትና የሌሎችንም እጅ ለመጠበቅ ተገደው ቆይተዋል። ትንሽ የማይባለው አርሶአደር የቤተሰቡን የእለት ጉርስ መሸፈን ስለተሳነውም የልማታዊ ሴፍትኔት ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል።

በአባያ ሃይቅ ላይ ዓሳ በማስገርና አነስተኛ ግብርና ሥራ ላይ ይተዳደሩ እንደነበር የሚያነሱት አርሶ አደሩ፤ አካባቢው ዝናብ አጠርና ጎርፍ በተደጋጋሚ የሚያጋጥም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቂ ምርት ማምረት ከባድ ፈተና እንደሆነባቸው ያስታውሳሉ። የነበሯቸው ከብቶች ሁሉ በአደጋው በማለቃቸው ለከፋ ችግር በማጋለጣቸው እርሳቸውም ሆነ ባለቤታቸው የቀን ሥራ በመሥራት የምግብ ፍጆታቸውን ለመሸፈን ጥረት ያደርጉ እንደነበርም ይገልፃሉ።

ይህም ቢሆን ሰባት ልጆቻቸውን የምግብ ፍላጎት ማሟላትና ትምህርት ቤት መላክ ስለከበዳቸው በ2013 ዓ.ም መንግሥት ባመቻቸው የልማታዊ ሴፍትኔት መርሃግብር ለመታቀፍ መገደዳቸውን ያብራራሉ።

በመርሃ-ግብሩ ተካተው ለስድስት ወራት ያህል በየወሩ ሶስት ሺህ ብር ድጋፍ ማግኘት ከመጀመሩ ወዲህ የቤተሰቡን ቀለብ መሸፈን መቻላቸውን ይናገራሉ። ድጋፍ አገኘሁ ብለው ግን እጃቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም፤ ይልቁንም የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት የሚያገኟትን ገንዘብ በመቆጠብና ከመንግሥት የወሰዱትን ብድር ተጠቅመው ጥሪት ለማፍራት ሌት ተቀን እየታተሩ መሆኑን ይገልፃሉ።

‹‹በመጀመሪያው ዓመት ባለችኝ አነስተኛ እርሻ ላይ በማምረትና ዓሳ በማስገር የማገኛትን ገንዘብ በመቆጠብና 16ሺ ብር ተበድሬ ሁለት ላምና ሰባት ፍየል በመግዛት እያረባሁ ነው›› ይላሉ። በአሁኑ ወቅት ሁሉንም ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት መላክ ከመቻላቸውም በተጨማሪም አዲስ ዘመናዊ ቤት ሠርተው የቤተሰባቸውን ኑሮ ማሻሻል ጥረት እያደረጉ ነው።

የከብት እርባታቸውንም ሆነ የእርሻ ሥራቸውን የማስፋት እቅድ እንዳላቸው የሚናገሩት አቶ ዳዊት፤ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ከተረጂነት ለመላቀቅ እቅድ ይዘው እየሠሩ መሆኑን ያመለክታሉ።

ከግብርና በተጨማሪ በንግድ ሥራ የመሰማራት ሃሳብ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህም ከራሳቸው አልፈው ሌሎችም ከርዳታ ጠባቂነት እንዲወጡ እገዛ እያደረጉ ነው። እንደእርሳቸው ሁሉ ሌሎቹም የማህበሩ አባላት ከተረጂነት ለመላቀቅ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ነው የተናገሩት።

‹‹ጥራት ያለው ማርና ሰም ለገበያው ለማቅረብ ፍላጎት ያለን ቢሆንም እንደማር ማጣሪ ያሉ ግብዓቶችን ማግኘት ባለመቻላችን ፍላጎታችንን ማሳካት አልቻልንም›› ሲሉ ያነሳሉ።

የቆላ ሙላቱ ቀበሌው ግብርና ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዘካሪያስ ሻንካ እንደሚናገሩት፤ በቀበሌው 141 አባወራ አደረጃጀት ውስጥ የሚገኙ 600 ነዋሪዎች የሴፍኔት ተጠቃሚዎች ይገኛሉ። በመርሃ-ግብሩ ምንም አቅም የሌላቸውና መሥራት የማይችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በቀጥታ ድጋፍ የሚያገኙበት ሥርዓት ቢኖርም አብዛኞቹ በማህበረሰብ ሥራ ማዕቀፍ ተካተው የራሳቸውናን የቤተሰባቸውን ኑሮ እንዲያሻሽሉ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው።

‹‹በቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ መርሃ-ግብር 52 ተጠቃሚዎች ብድር እንዲያገኙና ወደ ሥራ እንዲገቡ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። ከእነዚም ውስጥ አስሩ ነፃ ብድር ያገኙ ሲሆን ቀሪዎች ሠርተው ከሚያገኙት ገንዘብ በረጅም ጊዜ የሚከፍሉበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸዋል›› ይላሉ። እያንዳንዳቸው በመረጡት ዘርፍ እንዲሠማሩ የብድር አቅርቦት ከመቻቸቱም ባሻገር የሙያና የቴክሎጂ እገዛ እየተደረገላቸው መሆኑን አቶ ዘካሪያስ ያነሳሉ። አብዛኞቹ በእንስሳት ማድለብ፤ በንብ ማነብና በመሰል የግብር ሥራዎች ላይ ተሠማርተው ጥሪት እያፈሩና የቤተሰባቸውን ኑሮ እያሻሻሉ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

በተለይም 42ቱ ተጠቃሚዎች ባለሙት ተፋሰስ ላይ በንብ ማነብ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ የቀፎ ድጋፍ የተደረገላቸው መሆኑን ይጠቁማሉ። ከዚህ ጎን ለጎን የምግብነት ይዘት ያላቸውን የተለያዩ የፍራፍሬ ችግኞች እንዲያለሙ መደረጉን ጠቅሰው፤ በአሁኑ ወቅት ፍሬ እያገኙ በመሆናቸው ለቤተሰባቸው የምግብ አቅርቦት እገዛ እያደረተገላቸው መሆኑን ያነሳሉ።

በተጨማሪም በፍየል ድለባ የተሠማሩ የፕሮግራሙ ተጠቃዎችም በየሶስት ወሩ ፍየል እየሸጡ የገቢ አቅማቸውን የሚያሳድጉበት ምቹ ሁኔታ እንደተፈጠረላቸው ያስረዳሉ።

በንብ ማነብ የተሠማሩ ተጠቃሚዎች የሚያነሱትን የቴክሎጂና የገበያ ትስስር ጥያቄ በሚመለከትም ‹‹ጥያቄያቸው ተገቢ ነው፤ በአሁኑ ወቅት ምርታማነታቸው እያደገ ቢመጣም ማር የሚያጣሩበት መሣሪያ የሌላቸው በመሆኑ ከሌላ ቀበሌ ከሚመረተው ማር ጋር በገበያ ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን እንቅፋት ሆኖባቸዋል›› ይላሉ።

ይህን የቴክኖሎጂ ጥያቄ ለሚመለከተው አካል የቀበሌው አስተዳደር ያቀረበ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ ችግር ከተፈታ ግን የገበያ ትስስሩ አብሮ የሚጠናከር በመሆኑ ስጋት አይሆንም ባይ ናቸው።

የቀበሌዋ አርሶአደሮች በአሁኑ ወቅት ምርታማነታቸውን እያሳደጉ ኑሯቸውን እያሻሻሉ መሆኑን አቶ ዘካሪያስ አመልክተው፤ በቀጣዮቹ ስድስት ወራት ሙሉ ለሙሉ ከመርሃ-ግብሩ እንደሚመረቁ አውቀውና አምነውበት ከተረጂነት ለመላቀቅ እየሠሩ መሆኑን ያነሳሉ። በተያዘው በጀት ዓመት 70 በመቶ የሚሆኑት ሙሉ ለሙሉ ለማስመረቅ እየተሠራ መሆኑን ነው የተናገሩት።

በጋሞ ዞን የምዕራብ አባያ ወረዳ ፅህፈት ቤት አደጋ ስጋት አመራር ዘርፍ ሃላፊ አቶ መላኩ ደአ እንደሚሉት፤ በወረዳው 21 ቀበሌ ያሉ ሲሆን ሁሉም ወረዳዎች በሴፍትኔት ታቅፈዋል። በማህበረሰብ ልማት ሥራ የተሰማሩ 13 ሺ 961 ተጠቃሚዎች ያሉ ሲሆን 2 ሺህ 44 ሰዎች ደግሞ በቀጥታ ድጋፍ እያገኙ ይገኛሉ። በማህበረሰብ ልማት ሥራ ተጠቃሚ የሆኑና እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ፣ የጤና እና የአቅም ችግር የሌለባቸው ነዋሪዎች በተፋሰስ ልማት ፣ በደንና ችግኝ ልማት፣ መኖ ልማት፣ በመንገድ ሥራ እንዲሠማሩ ተደርጓል።

‹‹አካባቢው በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን የደረሰበት ሲሆን፣ በተለይ የአፈር መሸርሸር ችግር በማጋጠሙ ምርታማነት ዝቅተኛ ነበር›› የሚሉት ኃላፊው፤ መርሃ-ግብሩ መተግበር ከጀመረ ወዲህ በ24 ተፋሰሶች ላይ በተሠራው ሥራ ከ3ሺህ ሄክታር በላይ ማልማትና ወደ ቀደሞ ይዞታው መመለስ መቻሉን ያመለክታሉ። በተጓዳኝም ህብረተሰቡ በአካባቢውን ያሉትን ፀጋዎች በመጠቀም ኑሮውን እንዲያሻሽል ጥረት እየተደረገ መሆኑን ያነሳሉ።

በዚህም አንድ ሺህ 300 አባዎራዎችን በመለየት በተለያዩ ገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ እንዲሠማሩ መደረጉን ጠቁመው፤ በተለይም ወረዳው በንብ ማነብ ሰፊ አቅም ያለው በመሆኑ ይህንን በመጠቀም 999 ቀፎችን ለሶስት ቀበሌዎች መሰራጨቱንና ከተፋሰስ ልማት ሥራ ጋር ማስተሳሰር መቻሉን ነው ያስገነዘቡት።

ከግብዓት አኳያ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት እስከ ክልል ድረስ ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ በተለይ ለንብ አንቢዎች የማር ማጣሪያና ሰም ማተሚያ መሣሪያ ድጋፍ እንደሚያሻቸው ታምኖበት በእቅድ መያዙን ይጠቁማሉ።

# የተረሳው የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር

ዋሰልኝ አየለ

**ዜና ሐተታ**

ትምህርት ሚኒስቴር ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር እንዲደረግ በትኩረት እየሠራ ነው። ሚኒስቴሩ የውድድር ደንብ አዘጋጅቶ ሰሞኑን ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂዷል ።

ትምህርት ሚኒስቴር ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ በትምህርት ቤቶች በዞን ደረጃ እና በ2018 ዓ.ም ደግሞ በሀገር አቀፍ ደረጃ በአዲስ መልክ የትምህርት ቤቶችን ስፖርት ውድድር ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅቶችን እያጠናቀቀ መሆኑን ሰነዱ ያሳያል።

በትምህርት ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ቦጋለ፤ እንደተናገሩት፤ ብዙ ሰው ስፖርት የአካል ብቃትና የአካል ጥንካሬ ብቻ ይመስለዋል። ስፖርት የአዕምሮ ብቃትና የአዕምሮ ጥንካሬ ነው። ትምህርት ቤቶች ላይ መሥራት ትውልድ ላይ መሥራት ነው። በአዕምሮ የዳበረ እና የነቃ ትውልድ የሚፈጠረው በአካላዊ ጤና የነቃ ሲሆን ነው። የትምህርት አቀባበላቸውም ሆነ ሥነ ምግባራዊ ሠብዓዊነታቸው የሚገነባው በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ነው።

እንደ ሥራ አስፈፃሚው ገለጻ፤ ትምህርት ሚኒስቴር ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴርና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ትውልድ የሚፈጠርበት ትምህርት ቤት ላይ ይህን እንቅስቃሴ መጀመሩ ከፍተኛ ሀገራዊ ፋይዳ ይኖረዋል። በትምህርት በኩል ጤናማ እና ሥነ ምግባር ያለው ትውልድ ከመፈጠሩ ባሻገር ሀገራቸውን ወክለው በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወዳደሩ ወጣቶች የሚፈጠሩት ከትምህርት ቤት ነውና ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሁሉም ወገን ድርሻውን መወጣት እንዳለበት አሳስበዋል።

የተለያዩ ትምህርት ቤቶችን፣ ወረዳዎችን፣ ክልሎችን እና ቀጣናዎችን ወክለው የመጡ ተወያዮች ባቀረቧቸው ሪፖርቶች የትምህርት ቤቶች ስፖርታዊ ውድድር ለማካሄድ እንቅስቃሴ መጀመሩ በትምህርት ቤቶች ውስጥ መነቃቃትን ፈጥሯል። የትምህርት ቤቱን ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን ወጣቶችና የሥራ ኃላፊዎች ጭምር አነቃቅቷል። በተማሪዎች መካከል የመተዋወቅና የማህበራዊ መስተጋብር ልምምድ እንዲያደርጉ ዕድል ፈጥሯል። ሆኖም በአንዳንድ ክልሎች ችግሮች እንዳሉም የገለጹ ነበሩ።

ከጋምቤላ ክልል ተወክሎ የመጣው እና የሥርዓተ ትምህርት ባለሙያ የሆነው መሐሪ ገብረእግዚአብሔር ባቀረበው ሪፖርት፤ በዚህ ረገድ በክልሉ ምንም እንዳልተሠራ ተናግሯል። በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በሰጠው አስተያየት፤ የአደረጃጀት ችግር እንዳለ አስረድቷል። ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ የማይንቀሳቀስ ቋሚ የሆነ ባለሙያ ያስፈልገዋል። ሪፖርት ከማቅረብ ይልቅ ተግባራዊ ክትትል ይፈልጋል። ስፖርት የትውልድን ሥነ ልቦና በማጠንከር ከፍተኛ ሚና ስላለው በቋሚነት የሚሠራ መሆን እንዳለበትም ያሳስባል።

‹‹ጋምቤላ ውስጥ በየሜዳው ኳስ የሚጫወት ነው የምታየው፣ ትምህርት ቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን በየወረዳው ብትገባ ኳስ የሚጫወት ታገኛለህ፤ ክልሉ ሜዳ ስለሆነ ለኳስ ምቹ ነው›› የሚለው መሐሪ፤ አሠራሩ ግን ችግር እንዳለበት ይናገራል። አሁንም እየተሠራ ያለው በልማዳዊ መንገድ ነው። ትኩረት የሚሰጠው ከዚህ በፊት በስፖርት የታወቁና የተለመዱ አካባቢዎች ላይ ብቻ ስለሆነ ይህ ልማድ መቀረፍ እንዳለበትም ያሳስባል።

በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት መሠረተ ልማትና አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ አቶ ታዬ ግርማ በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ የትምህርት ቤቶች የስፖርት ሊግ ውድድር ሕገ ደንብ ወጥቶለት ትኩረት የተሰጠው የስፖርት ትምህርት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ መሰጠቱ ውጤታማ ስለማያደርገው ነው። ትምህርት ቤት በሁሉም ዘርፍ ተተኪ የሚፈጠርበት ስለሆነ በአካልና በአዕምሮ የዳበረ ዜጋ ለመፍጠርና በስፖርቱም ዘርፍ ተተኪ ለመፍጠር ነው።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር አሠራር ደንብ ትምህርት ቤቶች ከክፍል ክፍል፣ ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት፣ ከቀጣና ቀጣና እና ከዚያም በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲወዳደሩ የሚያደርግ ነው። በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚያደርጉት ዝግጅትም በዘጠኝ ቀጣና ተደራጅተዋል።

‹‹በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሜዳ ብቻ ሳይሆን እንደ አጠቃላይ የደረጃ (የስታንዳርድ) ችግርም እንዳለ የሚታወቅ ነው›› ያሉት አቶ ታዬ፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተጀመረው ‹‹ትምህርት ለትውልድ›› መሠረት ባለሀብቶችና ታዋቂ ሰዎች ለትምህርት ቤቶች እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ መቅረቡንም ያሳስባሉ። ትምህርት ቤቶች ሲጠናከሩ ስፖርት በቀዳሚነት እየታሰበ መሆኑንም ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ ይህ የትምህርት ቤቶች ስፖርት ሊግ ውድድር መጀመር ተማሪዎችን ብቻ ሳይሆን የሥራ ኃላፊዎችንም አነቃቅቷል፤ ብዙዎች ጤናቸውንም እንዲጠብቁ አድርጓል ነው ያሉት።



ፎቶ፡ ሐዲስ አብርሃ

# በኢትዮጵያ 54 ሚሊዮን ሄክታር መሬት የተራቆተ ነው

## - የአረንጓዴ ዐሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ሊቋቋም ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ውስጥ 54 ሚሊዮን ሄክታር የሚገመት የተጎሳቆለ መሬት እንዳለ ጥናቶች ማመላከታቸውን ተገለጸ። የአረንጓዴ ዐሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ሊቋቋም መሆኑም ተጠቁሟል።

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 12ኛ መደበኛ ስብሰባው የአረንጓዴ ዐሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋሚያና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ትናንት በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።

በምክር ቤቱ የፕላን በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ደሳለኝ ወዳጆ የረቂቅ አዋጁን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ሲያቀርቡ እንዳሉት፤ በሀገሪቱ ውስጥ 54 ሚሊዮን ሄክታር የሚገመት የተጎሳቆለ መሬት እንዳለ ጥናቶች አመላክተዋል። ከዚህ ውስጥ 11 ሚሊዮን ሄክታር መሬቱ በፍጥነት እንዲያገግም ካልተደረገ በዘላቂነት ለጉዳት የሚዳረግ ይሆናል።

አዋጁ የሀገሪቱን የተጎሳቆለ መሬት እንዲያገግም፣ የደን ሽፋንን በማሳደግ ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ በኩል ጉልህ ሚና እንደሚያበረክት ጠቅሰው፤ እየተገበረ ያለውን የአረንጓዴ ዐሻራ ሥራ በወጥነት እና በልዩ ፈንድ ተደግፎ መተግበሩ ሪፎርሙን ትርጉም ባለው መንገድ ለማስቀጠል ያስችላል ብለዋል።

የሀገሪቱ የተጎሳቆለ መሬት እንዲያገግም እና የተሻለ የደን ሽፋን እንዲኖራት በማድረግ በደን ልማቱ በሚገኘው ዘርፈ ብዙ ተግባራት ለኢኮኖሚው አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ገልጸዋል።

የተራቆተ መሬትን ተቋማዊ በሆነ መንገድ እንዲመለስ መሥራት ይገባል ያሉት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ፤ ከሀገሪቱ የፌዴራል በጀት ከዜሮ ነጥብ አምስት እስከ አንድ በመቶ ለአረንጓዴ ዐሻራና የተጎሳቆለ መሬት መልሶ እንዲያገግም ለሚሠራው ሥራ ይመደባል ብለዋል።

አዋጁ ለአረንጓዴ ዐሻራ ሥራዎች ቋሚና ተቋማዊ ሥርዓት ያለው የፋይናንስ አቅም እንዲኖር ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ የተዘጋጀ መሆኑን አስታውሰው፤ በዘላቂነት የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም እና ከአየር ንብረት ብክለት የፀዳ ኢኮኖሚ ለመገንባት የተያዘውን ሀገራዊ ራዕይ እንዲሳካ አስተዋፅኦ ያደርጋል ነው ያሉት።

በተጨማሪም የተቀናጀ ቋሚና ዘላቂነት ያለው የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ በመመደብና በማሰባሰብ ሁሉም ክልሎች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሠራር መቀየስ ተገቢ እንደሆነ ገልጸው፤ ለዚህም የአረንጓዴ ዐሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ብለዋል።

በሀገራችን የተጎሳቆሉ አካባቢዎችን በደን ልማት እና በጥምር ደን ግብርና መልሰው እንዲያገግሙ ማድረግ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ እንዲያድግ ያግዛል ያሉት ሰብሳቢው፤ በአረንጓዴ ዐሻራ የተተከሉና ወደፊት የሚተከሉ ችግኞች ቀጣይነት ባለው መልኩ፣ በቋሚነት እና በተቀናጀ አግባብ የፌዴራል መንግሥት የበጀት ድጋፍ የሚያደርግበት እንደሆነ ጠቁመዋል።

ሀገሪቱ በደን ዘርፍ ከልማት አጋሮችና ከሌሎች ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስ ሰጪ ምንጮች እና ከካርበን ግብይት ሥርዓቶች የምታገኘውን ድጋፍና ጥቅም ለማሳደግ እንደሚያስችልም ተመላክቷል።

ምክር ቤቱ በቋሚ ኮሚቴው በቀረበው ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ ከተወያየ በኋላ የአረንጓዴ ዐሻራና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋሚያና

# «የሶማሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዶሎ ከተማ ለተፈጠረው ክስተት የኢትዮጵያን ኃይሎች ተጠያቂ ማድረጉ መሠረተ ቢስ ክስ ነው»

- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሶማሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዶሎ ከተማ ለተፈጠረው ክስተት የኢትዮጵያን ኃይሎች ተጠያቂ ማድረጉ መሠረተ ቢስ ክስ ነው ሲል የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ።

የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳለው፤ ኢትዮጵያ የሶማሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2017 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ አዝናለች። የሶማሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዶሎ ከተማ ለተፈጠረው ክስተት የኢትዮጵያን ኃይሎች ተጠያቂ ማድረጉ መሠረተ ቢስ ክስ ነው ብሏል ።

እንደ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ፥ ክስተቱ በሁለቱ ሀገራት መካከል የተፈጠረውን ሰላም ለማደፍረስ በሚሹ አካላት የተጠነሰሰ ነው። እነዚህ ሶስተኛ ወገኖች የአፍሪካ ቀንድን የማተራመስ ዓላማ ያላቸውና በየጊዜው የቀጣናውን ሰላም ለማወክ የሚሠሩ ልማደኞች ናቸው ብሏል መግለጫው።

እነዚህ ኃይሎች በአንካራው ስምምነት የተንፀባረቀውን የሁለቱን ሀገራት የሰላም ቁርጠኝነት እንዲገዳደሩት ሊፈቀድላቸው አይገባም ብሏል።

ተመሳሳይ ክስተቶች እንዳይፈጠሩ ለመከላከል የኢትዮጵያ መንግሥት ከሚመለከታቸው የሶማሊያ መንግሥት ተቋማት ጋር በትብብር መሥራቱን ይቀጥላል ሲል ገልጿል።

በአንካራው ስምምነት መንፈስ በሁለቱ እህትማማች ሀገራት መካከል የቆየውን ወዳጅነት ለማደስና ለማጠናከር ለሚደረገው ጥረት ኢትዮጵያ ትልቅ ግምት ትሰጣለች ብሏል የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በመግለጫው።

የሀገራቱ መሪዎች የሁለትዮሽ አጋርነትን ብሎም ቀጣናዊ ትብብርን ለማጠናከር የወሰዱት ቁርጠኝነት የተመላበት ርምጃም ተጠናክሮ ይቀጥላል ነው ያለው።

በተያያዘ ዜናም የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ከሶማሊያ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ኤጀንሲ ዳይሬክተር አብዱላሂ መሐመድ አሊ ጋር በኢትዮጵያና ሶማሊያ መካከል ስላለው ግንኙነትና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ውይይት አድርገዋል።

ሁለቱ ሀገራት ከአንካራው ስምምነት በኋላ ያሉ አደናቃፊዎችን ለመታገልና ወደ ፊት ለመጓዝ ቁርጠኛ መሆናቸውን በኤክስ ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት ገልጸዋል።

# የመረጃ ሥርዓቱ የሥራ እድል፤ ፍላጎት እና አቅርቦትን ማጣጣም የሚያስችል መሆኑ ተገለጸ

**ነፃነት አለሙ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት አካል የሆነው ብሔራዊ የሥራ መረጃ ሥርዓት የሥራ ዕድል ፍላጎትንና አቅርቦትን ማጣጣም የሚያስችል መሆኑን በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ፕሮጀክት ኃላፊ አቶ ብርሃኑ አለቃ ገለፁ።

አቶ ብርሃኑ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት ፤ብሔራዊ የሥራ መረጃ ሥርዓቱ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የትኛው የሥራ ዘርፍ ተፈላጊ ነው የሚለውን በመለየት የመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ ወዴት መሆን እንዳለበት የሚጠቁም ነው።

ብሔራዊ የሥራ መረጃ ብሔራዊ የሥራ መገበያያ ቦታ መሆኑን ያመለከቱት ኃላፊው፤ ሥርዓቱ የትኛው የሥራ መስክ ላይ ተፈላጊ ነው ፤ ሥልጠናዎቻችንስ በምን ላይ ያተኩሩ ፣ የሚለውን ለመለየት የሚያስችል መሆኑን ጠቁመዋል።

ሥርዓቱ በሰው ሠራሽ አስተውሎ ተደግፎ ፤ የወራትን ጨምሮ ከዓመታት በኋላ የሚኖረውን ፍላጎት መገመት እንደሚችል አመልክተው ፤ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር ያሉ የሥራ ዕድሎች ላይ ምን ያህል ሰው ፤ በምን ዘርፍ እንደሚፈለግ በመለየት ፖሊሲዎች እንዲስተካከሉ እንደሚረዳም ገልፀዋል።

በተለይም የሰው ሀብት ልማት ላይ የሚሠሩ ተቋማትን መስመር የማስያዝ ጠቀሜታ እንዳለው የገለፁት ኃላፊው፤ ውጤታማ የአቅርቦትና የፍላጎት መጣጣም እንዲኖር የተዘረጋ ሥርዓት መሆኑን አስረድተዋል። ሥርዓት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ክፍት ነው ፤ ኢትዮጵያዊ ሆኖ እድሜው ከ 15 እስከ 64 አመት የሆነ ሁሉ ሊጠቀምበት እንደሚችል አስታውቀዋል።

ሥርዓቱ ከ15 ዓመት ዕድሜ የተነሳበት ምክንያትም በዚህ የዕድሜ ክልል ያሉ ተማሪዎች ያሉበት የትምህርት ደረጃ ላይ ሆነው በምን ሙያ ብማር እና ብመረቅ የሥራ ዕድል አገኛለሁ የሚለውን እንዲያስተካክሉ ይረዳቸዋል በሚል እንደሆነ አመልክተዋል። ተመርቀው ወደ ሥራ ገበያው ለተቀላቀሉ ሥራ ፈላጊዎች ደግሞ ሶስት የሥራ ገበያ አማራጮች አሏቸው ብለዋል።

አንደኛው የሀገር ውስጥ የሥራ ዕድል ነው ያሉት ኃላፊው፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት የወጡትን ጨምሮ በየቀኑ የሚወጡትን የሥራ ማስታወቂያዎች በዚህ ሥርዓት ማየት እንደሚቻል የጠቆሙት ሃላፊው ፤ ሁለተኛው የውጪ ሀገር የሥራ ስምሪት መሆኑን ገልጸዋል።

በውጪ ሀገር ያሉ ድርጅቶች የሚያስፈልገውን ሂደት ሁሉ ጨርሰው ሠራተኛውን የሚወስዱበት መንገድ ነው። በዚህ የሥራ አማራጭ ከሶስት ሚሊዮን በላይ የሥራ ዕድሎች አምጥተናል ፤ በዚህ ዓመት ብቻ ከመቶ ስልሳ አምስት ሺህ በላይ ዜጎች በእድሉ ተጠቃሚ ሆነዋል ብለዋል።

ሶስተኛው የሥራ አማራጭ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው ኢንተርኔት በመጠቀም ለውጪ ድርጅቶች የሚሠራበት ዕድል እንደሆነ ገልጸው ፤ በዚህ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው በትንሹ ሁለት ሺህ አርባ ስምንት ዶላር ይከፈለዋል። በዚህ የሥራ አማራጭ ሰማንያ ስድስት ሺህ ሥራዎች አምጥተናል ፤ ወደ ሰላሳ አምስት ሺህ የሚጠጉ ዜጎች የእድሉ ተጠቃሚ መሆናቸውን ተናግረዋል።



አቶ ብርሃኑ አለቃ

ብሔራዊ የሥራ መረጃ ሥርዓት የኢትዮጵያ ሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ውስጥ ካሉ ሃያ ሶስት አገልግሎቶች አንዱ መሆኑን አስታውሰው፤ የሥራ ማስታወቂያዎችን በሙሉ ወደ አንድ ቋት የሚሰበስብ ብሔራዊ የሥራ መገበያያ መሆኑን ገልፀዋል። አስካሁን በነበረው ሁኔታ ሥራ ፈላጊዎች ሥራ አግኝተው እስከሚቀጠሩ ድረስ ያለው ምህዳር ምቹ እንዳልነበር አመልክተዋል።

ሂደቱን በማዘመንና ዲጂታላይዝ በማድረግ ከሃያ በላይ ድረገፆች ወደ አንድ ማዕከል እንዲመጡ አድርገናል። ባለፉት ሁለት ዓመታትም በሀገር ውስጥ ብቻ ወደ አራት መቶ ሃምሳ ሺህ የሥራ ማስታወቂያዎች በሥርዓቱ መካተታቸውን አስታውሰዋል። በዚህ ሥርዓት የተመዘገበ፣ አሻራ የሰጠ፣ የሠራተኛ መለያ ቁጥር ያለው ሁሉ የሥርዓቱ ባለቤት በመሆኑ መረጃውን እንደፍላጎቱ መጠቀም እንደሚችል አብራርተዋል።

አገልግሎቱን በተለያዩ ቋንቋዎች በ17 የማህበረሰብ ሬዲዮኖች፣ በመገናኛ ብዙሃንና በማህበራዊ ሚዲያዎች ዜጎች መረጃው እንዲኖራቸውና እንዲጠቀሙ ለማድረግ መሞከሩን ፤ ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ከሁለት ሚሊዮን ሰዎች በላይ ወደዚህ ሥርዓት መምጣታቸውን ገልፀዋል።

አብዛኞቹ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች የውጪ ሀገራት የሥራ ስምሪት ፈላጊዎች እንደነበሩ የጠቆሙት ኃላፊው፤ ሥርዓቱ ለሀገር ውስጥ ሥራ ፈላጊዎች ሁኔታዎችን እጅግ በጣም የሚያቀል አማራጮች እንዳሉት አስታውቀዋል።

ሃላፊው ፤ ዜጎች በዚህ ሥርዓት ተመዝግበው፣ ዐሻራ ሰጥተውና መለያ ቁጥር አውጥተው እያንዳንዱን አገልግሎቶች ምን ፋይዳ እንዳላቸው በመለየት ለሚፈልጉት ዓላማ እንዲጠቀሙበት ጥሪያቸውንም አስተላልፈዋል።

# የናይል ወንዝ ተፋሰስ ኮሚሽን…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ነበር። በኋላ ላይ ግን የእነዚያ ሀገራት መሠረታዊ ፍላጎታቸው ከኢትዮጵያ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ያሰቡት ሳይሳካ ቀርቷል።


ሰባቱም የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት በኢትዮጵያ እየተመሩ ግብጽና ሱዳን ደግሞ አንድ ላይ ሆነው ድርድሩ ወደመቋጨቱ ሲቃረብ፤ ግብጽና ሱዳን ያቀዱት ስላልተሳካላቸው ስምምነቱን ጥለው እንደወጡ የሚናገሩት አቶ ፈቅአሕመድ፣ በስምምነቱ ውስጥ ከተካተቱ ከዘጠኙ ተደራዳሪ ሀገራት ሁለት ሶስተኛ ሀገሮች ከፈረሙ ወደመጽደቅ እንደሚሔድ ይታወቃልና ድርድሩ ለፊርማ ክፍት መደረጉን ያስታውሳሉ፤ በዚህም የመጀመሪያ ቀን የመጀመሪያ ፊርማዋን ያኖረችው ኢትዮጵያ ስትሆን ቀጥሎ ዑጋንዳ፣ ታንዛንያና ሩዋንዳ እንደሆኑ ጠቅሰው፤ በሶስተኛው ቀን ኬንያ ስትፈርም ከዚያ ከአስር ወር በኋላ ብሩንዲ መፈረሟን ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ የማጽደቅ ሒደቱ ሲጀመርም በመጀመሪያ ያጸደቀችው ኢትዮጵያ ነች። ቀጥሎም በተከታታይ ሩዋንዳ፣ ታንዛንያ፣ ዑጋንዳና ብሩንዲ ሲሆን፣ በዚያን በድርድሩ ወቅት ደቡብ ሱዳን ነጻ ሀገር ባለመሆኗና በሱዳን ውስጥ በመሆኗ ያልተደራደረች ሀገር ብትሆንም ነጻ ከወጣች በኋላ ግን ስድስተኛ አጽዳቂ ሀገር በመሆኗ ሕግ ለመሆን በመብቃቱ ፤ የአፍሪካ ኅብረትም ተፈጻሚ መሆኑን አሳውቋል።

ይሁንና ይላሉ የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያው፣ ስምምነቱ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ ግብጾች እንቅልፍ አልወሰዳቸውም። ያልፈረሙ ሀገራት እንዳይፈርሙ፣ የፈረሙ ሀገራት ከፊርማው እንዲወጡ፣ የፈረሙ ሀገራት ደግሞ እንዳያጸድቁ በማድረግና በዓመት እስከ አስር ሚሊዮን ዶላር ድረስ ወጪ በማውጣት ስምምነቱን ለማጣጣል ሲተጉ እንደነበር ያብራራሉ።

ግብጾች፣ በአብዛኛው የሚያደርጉት ነገር አንደኛ፤ ስምምነቱ የሁሉንም ሀገር ይሁንታ እስካላገኘ ድረስ ስድስት ሀገራት ብቻ የፈረሙት ስምምነት ሕገ ወጥ ነው የሚል ነው። ሁለተኛው ደግሞ የናይል ተፋሰስ ውሃን አያስተዳድርም የሚል ሲሆን፣ ሶስተኛ ደግሞ እኛን አይመለከተንም የሚሉ ነው ይላሉ። ይህን ሃሳባቸውን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማስተጋባት እየተንቀሳቀሱ እንደሆኑም ያስረዳሉ።

ለእኛ ትልቁ ስኬት የሚባለው ግን የማሕቀፉ ሕጋዊ መሆን ቀድሞ የነበሩ ሕጎችን መሻሩ ላይ ነው የሚሉት ደግሞ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) ናቸው። ለአብነትም የ1959ኙን ሁለት ሀገሮች ብቻ ወስነው እንዳሻቸው የሚያደርጉትን አካሔድ መለወጡ ለኢትዮጵያ ትልቅ ስኬት እንደሆነ ያስረዳሉ። በቀጣይ ደግሞ ኮሚሽኑ እንደሚመጣ አስታውቀው ይህን ኮሚሽን ኢትዮጵያ የምትደግፈው እንደሆነ ይናገራሉ።



ኮሚሽኑ ለኢትዮጵያ ሰላም የሚሰጥና ለሁሉም የሚጠቅም መሆኑንም ይገልጻሉ።

የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን በሕግ ተቋቁሟል። አሁን የሚቀረው መዋቅሩን አዘጋጅቶ ተግባርና ኃላፊነቱን ወስኖ በሰው ኃይል፣ በማቴሪያልና በፋይናንስ አጠናክሮ ሥራ የማስጀመር ሥራ ነው ያሉን ደግሞ አቶ ፈቅአሕመድ ሲሆኑ፣ ይህ እንዳይሳካ ግን ግብጾች ጥረት እያደረጉ ነው ብለዋል።

ይህን ለመቋቋም ኢትዮጵያ የሚጠበቅባት ከላይኛው የናይል ተፋሰስ ሀገራት ጋር በመሆን ኮሚሽኑ በአስቸኳይ ተቀቋቁሞ ወደሥራ እንዲገባ ማድረግ ነው። ኮሚሽኑን ወደሥራ ማስገባት ሲባል በሁለንተናው ጠንካራ እንዲሆን ማድረግንም ያካትታል። ደከም ያለ፣ ውሳኔ የማይሰጥ፣ በቂ ፋይናንስና አቅም የሌለው ከሆነ አንደኛ ለውጥ አያመጣም፤ ሁለተኛ ተመልሶ የሚወድቅበት ሁኔታ ይፈጠራል። ስለዚህ በጣም ጠንካራና ትልልቅ ውሳኔዎችን መወሰን የሚችል ኮሚሽን መሆን አለበት፤ ሀገራቱም በቂ የገንዘብ መጠን ሊያቀርቡለት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ለዚህ ምክንያታቸውን ሲዘረዝሩ አእንዳሉት፤ ሀገራቱ ገንዘብ ካላቀረቡ ኮሚሽኑ የልማት አጋሮችን ገንዘብ መጠየቅ ይጀምራል፤ ገንዘብ መጠየቅ የጀመረ ዕለት ደግሞ የልማት አጋሮችን አጀንዳ እንጂ የተፋሰሱ ሀገራትን አጀንዳ ማስፈጸም አይችልም። ስለሆነም በቂ የፖለቲካ ድጋፍ የተሰጠውና ከፍተኛ የዲፕሎማሲ አቅም እንዲኖረው የተደረገ ኮሚሽን ማቋቋምና ከኮሚሽኑ ጋር ደግሞ ጠንክሮ መሥራት ያስፈልጋል።

የተፋሰሱ ሀገራት፣ ኮሚሽኑ የሚያወጣቸውን እቅዶች ከተገበሩና ወገባቸውን አስረው ወደልማት ከገቡ የግብጽን ጫና መቋቋም ብቻ ሳይሆን ግብጽ ራሷ ተመልሳ ወደ ስምምነቱ እንድትመጣ ሊያደርጋት የሚችል ነው። የኮሚሽኑ ጠንካራ መሆን ጥቅሙ ለኢትዮጵያ ብቻ አይደለም፤ የተፋሰሱ ሀገሮች ጭምር ነው ይላሉ።

የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያው እንደሚያብራሩት፤ ኢትዮጵያ የሚጠበቅባት ነገር ቢኖር መምራት ነው። ቀደም ሲልም ወደ ድርድሩ ሲገባም ኢትዮጵያ ትልቅ ሚና ተጫውታለች፤ አሁንም ኮሚሽኑን በማቋቋሙ ላይ የመሪነቱን ሚና መጫወት አለባት። ሀገራቱ ግን ሲፈርሙና ሲያጸድቁ በራሳቸው ላይ የዓለም አቀፉን ግዴታ ጥለው ነውና ወደኋላ የሚሉበት ምንም ምክንያት የለም፤ ይህ የጋራ ኃላፊነት ነው።

ሚኒስትሩ በበኩላቸው፤ በአሁኑ ወቅት ብዙ ሀገሮች ስለማሕቀፉም ሆነ ስለኮሚሽኑ ግንዛቤውን ስላገኙ ተፈጻሚነቱ እንዲፋጠን በማድረግ ላይ መሆናቸውን ይናገራሉ። ኢትዮጵያ የምትፈልገው ይህንኑ እንደሆነ አስረድተው፤ ቀደም ሲል ግን ስለፍትሃዊነት ስንጮህ የነበረው ብቻችንን ነበር ሲሉ አስታውሰዋል። ስለሆነም ኢትዮጵያ በአሁኑ ውቅት አጋዥ ማግኘቷንም አስረድተዋል።

በዚያው ልክ ደግሞ ፈተናዎች አሉብን። የታችኞቹ ሀገሮች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ፤ ሚዲያዎችንም በመጠቀም ጭምር ኮሚሽኑ ስኬታማ እንዳይሆን ይጥራሉ። በተለይ ግብጾች የትብብር ማሕቀፉን ማጣጣልን ሥራዬ ብለው ተያይዘውታል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ምንም አይነት ገንዘብም ሆነ ድጋፍ እንዳይገኝ በተለያየ ቦታ በመንቀሳቀስ የማከላከል ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ። በመሆኑም እኛ ኢትዮጵያውያን ጉዳዩን በአግባቡ መግለጽና ማስገንዘብ ይጠበቅብና ሲሉ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

የኮሚሽኑ ዋና ሥራ የሚባሉት አንደኛው ስምምነቱን ማስፈጸም ሲሆን፣ ስምምነቱ ደግሞ የውሃ አጠቃቀምን፣ የውሃ ጥበቃን፣ የውሃ እንክብካቤን እንዲሁም የውሃ አስተዳደሩንም የሚመለከት ነው የሚሉት የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያው ናቸው። ስለዚህ ተፋሰሱ ጠንካራ ከሆነ ውሃውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ይህ ደግሞ የሁሉም ሀገራት ፍላጎት ነው። እንዲያውም ኮሚሽኑ ለሀገራቱ እስከ ውሃ መደልደል ድረስ የመሄድ ሥልጣን ይኖረዋል ብለዋል።

እንደ አቶ ፈቅአሕመድ ገለጻ፤ ሌላኛው ጉዳይ በሀገራቱ መካከል ያለውን ትብብር ማጠናከር ነው። እንደሚታወቀው የናይል ተፋሰስ ሀገራት በአብዛኛው ለብዙ ዘመናት ለእርስ በእርስ ግጭት፣ ድርቅ፣ ረሃብ ሲጋለጡ የቆዩና እንዳያድጉም ከፍተኛ ደባ ሲደረግባቸው የነበረ ስለሆነ አቅማቸው የዚያን ያህል የጎለበተ አይደለም። ለብቻቸው ግዙፍ የሆኑ ልማቶችን ማካሔድ አይችሉም። ስለዚህ ኮሚሽኑ ሀገራቱ የገንዘብ፣ የእውቀት እና የፖለቲካ ጉልበታቸውን አቀናጅተው በተለይ የጋራ ልማታቸውን እንዲያካሂዱ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ይሆናል።

እንዲሁም ኮሚሽኑ፣ በየተፋሰሱ ደግሞ እንደየ አግባቡ ሌሎች የልማት ተቋማት እንዲቋቋሙ የማድረግ ሥራ ይኖረዋል። ስለዚህ ያንንም ሥራ በመሥራት ሀገራቱ ወደ ሥራ እንዲገቡ ከሌሎች ሀገሮች ደግሞ ጫና ሲመጣ ሀገራቱን የመከላከል ሥራ የመሥራት ሁኔታዎችም ይኖራሉ። ስለዚህ ኮሚሽኑ በጣም በርካታ ድጋፍ የሚሰጥ ነው ሲሉ ያመለክታሉ።

መረጃዎች እንደሚያመክቱት፤ የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ድርድሩ የተጀመረው በዘጠኝ ሀገራት መካከል እኤአ በ1997 ነው። ለ13 ዓመታት ድርድር ላይ ከቆየ በኋላ የተፈረመው እኤአ በ2010 ነው።

ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ ግብጾች የቱንም ያህል ቢሯሯጡ አይሳካላቸውም። ይሁንና ሁሌም ከመሞከር አይቦዝኑም። እኛ ግን የሚጠበቅብን መሥራትና እውነትን ይዘን አሸናፊ መሆን ችለናል። እኛ ዓባይ ላይ ባለማነው ኢነርጂ፣ በቀጣይም በምናለማው ኢነርጂ ኬንያ ተጠቃሚ ናት። ዛሬ ኢትዮጵያ ለኬንያ ኢነርጂ ትልካለች። በተመሳሳይ ጅቡቲም ሱዳንም ከኢትዮጵያ ተጠቃሚ ናት። ለየሀገራቱ ኢነርጂ እየሸጥንላቸው ነው።

አቶ ፈቅአሕመድ በበኩላቸው፤ ግብጽ ሴራዋን ማራመድ ትችላለች፤ ዋናው ነገር ሀገራቱ ያንን የግብጽ ጫና የመቋቋም አቅምን ማሳደግ መቻል አለባቸው ይላሉ። ሀገራቱ የግብጽን ጫና የመቋቋም አቅም የገነቡ ጊዜ የግብጽ ሩጫ ትርጉም አይኖረውም ብለዋል።

# ለኢትዮጵያ የባሕር በር…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል መምህርና የትምርት ክፍሉ ሃላፊ አቶ ሙሉዓለም ኃይለማርያም እንደሚያስረዱት፤ የኢትዮጵያና የፈረንሳይ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በተለይም ከ18ኛው ክፍለዘመን መጨረሻ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ተጠናክሮ የዘለቀ ነው።

ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱ ነባር፣ ጥብቅና ተጨባጭ ውጤቶች የታዩበት ነው፤ ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ የተዘረጋው የባቡር ሃዲድም የተሠራው በፈንሳይ ነው። ዛሬም ድረስ አብዛኛው የሀገሪቱ የወጪ ገቢ ንግድ የሚካሄደው በዚሁ ኮሪደር ነው። ይህ በኢትዮጵያና በጅቡቲ መካከል ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትና ወዳጅነት ቀደምትና ጠንካራ መሆኑን የሚያሳይ ነው ይላሉ ምሁራኑ።

አቶ ሙሉዓለም ከዓድዋ ድል በኋላ ኤምባሲያቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ ከከፈቱ ሀገራት የመጀመሪያዋ ፈረንሳይ እንደሆነች ጠቅሰው፤ በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ፈረንሳይ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ስታደርግ እንደቆየች ያመለክታሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዓለምሰገድ (ዶ/ር) በባንክ፣ በቴሌፎን፣ በትምህርት፣ በጤና ፣ በሆቴሎች ግንባታ ፣ በንግድ (በጦር መሣሪያ ንግድ) ኢትዮጵያን ከማዘመን አንጻር ፈረንሳይ ውለታ እንደሠራችና ዛሬም ደረስ ድጋፏ እንዳልተለየ ይገልጻሉ።

አቶ ሙሉዓለም በዚሁ ላይ ተጨማሪ ሲያደርጉ፤ ፈረንሳይ ከዓመታት በፊት ኢትዮጵያ ለምታቋቁመው የባሕር ኃይል ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገብታለች፤ አሁንም ቅርሶችን በማደስ ረገድ የፋይናንስና የሙያ ድጋፍ እያደረገች ትገኛለች። የሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲዊ ግንኙነት ዘመናትን ተሻግሮ የመጣና ዛሬም ድረስ ያልደበዘዘ ነው ይላሉ።

ፕሬዚዳንት ማክሮን ከባለፉት ስድስት ዓመታት ወዲህ ሁለት ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፤ በሰሞኑ ጉብኝታቸው ከጠቅላይ ሚኒስት ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጋር ባደረጉት ንግግር የአንካራውን ስምምነት አድንቀዋል። ለስምምነቱ እውቅና መስጠታቸው ኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄዋ በዓለም ማህበረሰብ ዘንድ ጎልቶ እንዲታይ ያደርጋል ሲሉ ያብራራሉ።

ስምምነቱ ከወረቀት አልፎ መሬት ላይ እንዲያርፍም ጫና ያሳድራል፤ ፈረንሳይ በቀጣናው ካላት የረዥም ጊዜ ቆይታዋ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፍላጎቷ አንጻር በጅቡቲ ላይ ብቻ ሳይሆን በቀጣናው ካሉ የቀይ ባሕርም ይሁን የሕንድ ውቅያኖስ ወሰንተኛ ሀገራት ላይ የዲፕሎማሲ ጫና በማሳደር ኢትዮጵያ በሊዝ ወይም በኮንትራት የባሕር በር አማራጮችን እንድታሰፋ ልታደርግ ትችላለች ይላሉ።

ፈረንሳይ በቀጣናው ላይ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነት አላት የሚሉት አቶ ሙሉዓለም ተጽዕኖዋም በዚያው ልክ ስለሆነ የሚያዳምጧት ሀገራት ይኖራሉ። ሌሎች ዓለም አቀፍ ሀገራትም ጭምር የዲፕሎማሲ፣ የፋይናንስና የሎጂስቲክ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጫና ማሳደር እንደምትችልም ይናገራሉ።

ዓለምሰገድ (ዶ/ር)፤ ይህንኑ ሃሳብ ሲያጠናክሩ፤ የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ የሚመለሰው ከጎረቤት ሀገራት ጋር ትብብር እና መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ሲፈጠር ነው፤ ይሁንና እንደፈረንሳይ አይነቶቹና በቀጣናው ተጽዕኖ መፍጠር የሚችሉ ሀገራትን መያዝ ደግሞ የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል።

ሁለቱም ምሁራን እንደሚያስረዱት ፈረንሳይ በቅኝ ግዛት የያዘቻቸውን የምእራብ አፍሪካ ሀገራት ከለቀቀች በኋላ በቀይ ባሕር አካባቢ ጦሯን በማስፈር ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ አልማ እየሠራች ነው። ፈረንሳይ ከራሷ ተጠቃሚነት አንጻር በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት እንዲኖርም ትፈልገዋለች፤ ተጽዕኖም መፍጠር ትችላለች። በቀጣናው ያላትን የረዥም ጊዜ ቆይታና ልምድ በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ የተረጋጋና ሰላማዊ መስተጋብር ያለው እንዲሆን ማድረግ ትችላለች።

ኢትዮጵያም ትልቅ አቅም ያላት ሀገር ስለሆነች ፈረንሳይ ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር መሥራት ትፈልጋለች። ፈረንሳይ ከሶማሊያ፣ ከጅቡቲ ፣ ከኤርትራና ከሌሎችም የአፍሪካው ቀንድ ሀገራት ጋር ጥሩ ግንኙነት ስላላት ኢትዮጵያ የባሕር በር እንድታገኝ የማግባባት ሚና ልትጫወት ትችላለች ይላሉ ምሁራኑ።

ኢትዮጵያ የባሕር በር እንዳይኖራት በሚመስል መንገድ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሀገራት እጃቸውን ሰብስበው እንዲቀመጡ ከማድረግ አንጻር ፈረንሳይ የነቃ ተሳትፎ ታደርጋለች ተብሎ ይታመናል ይላሉ። የፈረንሳይን ተጽዕኖ ፈጣሪነት አጥብቆ በመያዝና ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖረውን የዲፕሎማሲ ግንኙነት አጠናክሮ በመቀጠል በወደብ ጉዳይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ምሁራኑ ይስማማሉ ።

# “የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ተወካዮች…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ያላሳወቁ እንደ ሃይማኖት እና ፖለቲካ ፓርቲዎች ያሉ ተቋማት በኮሚሽኑ አሠራር መሠረት በቀጣይ በተቋማቸው በኩል ተወካዮቻቸውን እንደሚያሳውቁ ጠቁመዋል።

የሴቶች ተሳትፎ 30 በመቶ እንዲሆን ኮሚሽኑ ካስቀመጠው ግብ አኳያ የተሳካ እንደነበረ ጠቁመው ፤ የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎም በጥንካሬ የታየ መሆኑን አመላክተዋል። የሚዲያ አካላት የኦሮሚያ አጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክን ለሕዝብ በማድረስ ላበረከቱት አስተዋጽኦም ምስጋናቸውን ያቀረቡት ዋና ኮሚሽነሩ፤ የምክክሩ ሂደት የተሳካ እንዲሆን ተገቢውን ትብብር እና ድጋፍ ያደረጉ ሌሎች አካላትንም አመስግነዋል።

በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲሳተፉ የተመረጡ የተለያዩ የማህበረሰብ ወኪሎች የተሰጣቸውን አደራ መወጣት እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አዋጁ የሀገር ውስጥ ባንኮችን ለማነቃቃት ተጨማሪ አቅም ነው!

ባንኮች አነስተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚታይባቸው አካባቢዎች የገንዘብ ፍሰት ሥርዓትን አስጠብቀው ወደ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲሸጋገሩ በማድረግና በአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊና ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት እንዲመዘገብ የሚያደርጉ ወሳኝ አቅሞች ናቸው፡፡

በፋይናንስ ተቋማት ውስጥ የባንኮች ጥንካሬና ድክመት በአንድ ሀገር የወደፊት ዕድገት ላይ ከሚኖራቸው አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚመነጭ ነው፡፡ አጠቃላይ ሀገራዊ የኢኮኖሚያዊና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት እንዲመዘገብ የሚኖራቸውም ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

ከውጭ የሚገኝ ብድርና ርዳታ መሠረት ያደረገ የሀገር ኢኮኖሚ እንዳይኖር፤ ካለም ቀስ በቀስ ራስን ለመቻል በሚደረግ የመዋቅራዊ የለውጥ ሂደት ፤ ባንኮች የሀገር ውስጥ አቅምን በመጠቀምና የብድርና ቁጠባ አገልግሎትን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በመስጠት ኢንቨስትመንቱ እንዲጎለብትና የሀገር ውስጥ ልማት እንዲፋጠን የላቀ ሚና ይጫወታሉ፡፡

የታሪክ መዛግብት እንደሚያመለክቱት ፤ በኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ ከተጀመረ ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ ዕድሜ አለው። የመጀመሪያው ባንክ በ1905 ዓ.ም በዳግማዊ አፄ ምኒልክና በእንግሊዝ ይዞታ ስር በነበረው የግብፅ ብሔራዊ ባንክ መካከል በተደረሰ ስምምነት መሠረት እ.ኤ.አ. የካቲት 16/1906 በአዲስ አበባ ከተማ በንጉሠ ነገሥቱ ተመርቆ ሥራ ጀምሯል፡፡

አገልግሎቱ በተጀመረ በአጭር ጊዜ ውስጥ በወቅቱ ከፍተኛ የንግድ እቅስቃሴ በነበረባቸው ድሬዳዋ፣ ጎሬና ደሴ ከተሞች ቅርንጫፎችን መክፈት ተችሎ ነበር፡፡ በወቅቱም በተለይ አዲስ አበባ የሚገኘው ዋናው አቢሲኒያ ባንክ የኢትዮጵያን ገንዘቦችና ሣንቲሞች ከማተም ጀምሮ ለመንግሥት ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ይሰጥ እንደነበር በታሪክ ተመልክቷል፡፡

እ.አ.አ በ1931 ዓ.ም በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሙሉ በሙሉ በእንግሊዞች ቁጥጥር ስር የነበረውን ባንክ ሕጋዊ በሆነ መንገድ የኢትዮጵያ ባንክ ወደሚል ስያሜ እንዲቀየርና በአዲስ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ይህም ሀገር በቀል እና ከቅኝ ገዢዎች ነፃ በሆነ ሀገር የተቋቋመ የመጀመሪያው አፍሪካዊ ባንክ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የባንኩ ዘርፍ በየወቅቱ ያጋጠሙትን መልካም ዕድሎች እና ፈተናዎች ተሻግሮ ዛሬ ላይ ደርሷል። የዛሬ ቁመናውም ቢሆን የዕድሜውን ያህል እንዳልሆነ በዘርፉ የተሠማሩ ምሁራን በስፋት የሚናገሩት የአደባባይ እውነታ ነው።

የሀገራችን ባንኮች በአብዛኛው የሚገኙት በከተሞች አካባቢ ነው። የብድር አገልግሎት የሚሰጡትም ማስያዣ ማቅረብ ለሚችሉ ጥቂት ባለሀብቶች ነበር። እሱም ቢሆን በብዙ ችግሮች የተሳሰረ ስለመሆኑ በብዙ ሲነገር የሚሰማ ነው። ከዚህም ባለፈ የቁጥራቸውን ያህል አቅም የገነቡ አይደሉም።

ለዚህም ሲባል በተለያዩ ወቅቶች አቅማቸውን አቀናጅተው ለተሻለ ተወዳዳሪነት ዝግጁ እንዲሆኑ ምክረ ሃሳብ ሲሰጣቸው ቆይተዋል። አንዳንዶች በአሁኑ ወቅት ይህን ምክረ-ሃሳብ ለመተግበር እንቅስቃሴ እያደረጉ ስለመሆናቸውም አንዳንድ መረጃዎች ያመላክታሉ።

በመንግሥትም በኩል በየጊዜው ራሳቸውን በተሻለ መልኩ አብቅተው በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ ተደጋጋሚ ጥሪዎች ሲደረጉ ተሰምቷል። በፖሊሲ ደረጃም ዘርፉ ለውጪ ሀገር ባለሀብቶች ዝግ ሆኖ እንዲቆይም ተደርጓል ።

በዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ውስጥ ባንኮቻችን በቴክኖሎጂ ፣ በአሠራር ሥርዓት እና በሀብት ራሳቸውን የተሻለ ደረጃ ላይ አድርሰው፤ እንደ ሀገር ለተጀመረው የብልጽግና ጉዞ የሚጠበቅባቸውን ማበርከት የሚያስችል ሁለንተናዊ ቁመና መፍጠር አልቻሉም። ዛሬም ቢሆን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸውን የሚያጸና በራስ መተማመን አልገነቡም።

ይህም ሆኖ ግን እንደሀገር የተጀመረው የፋይናንስ ዘርፉን ሊበራላይዝድ የማድረግ የፖሊሲ አቅጣጫን መሠረት በማድረግ ሰሞኑን የውጪ ባለሀብቶች በፋይናንስ ዘርፍ እንዲሠማሩ የሚፈቅደው ረቂቅ ሕግ ጸድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል። ሕጉ የሀገሪቱን የፋይናንስ ኢንዱስትሪ በማነቃቃት ሂደት ትልቅ አቅም እንዳለው በዘርፉ ባለሙያዎች እየተነገረለት ነው።

በተለይም ወደ ሀገሪቱ የሚመጡ ባንኮች ሀገሪቱ ለቀጣይ ልማቷ የምትፈልገውን ሀብት እና ቴክኖሎጂ ወደ ሀገር ውስጥ ለማምጣት የጎላ ጠቀሜታ አላቸው ፤ በዘርፉ ያላቸውን የካበተ ልምድ ለሀገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት በማጋራት ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ እንደሚረዳቸው ይታመናል።

ለሥራ ፈጣሪዎችም ሆነ ፣ ለሜጋ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን ሀብት በተሻለ መልኩ በማቅረብ ፤ ለሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ተጨማሪ መነቃቃት የሚፈጥሩ ከመሆናቸው በተጨማሪ ፤ በባንኩ ዘርፍ ተጠቃሚ ያልሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ከዘርፉ የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መልካም ዕድል ይዘው እንደሚመጡም ይታመናል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአዳዲሶቹ የአትሌቲክስ መሪዎች ቁልፍ የቤት ሥራዎች

ብርሃን ፈይሳ

እአአ 1960 በፊት የዓለም አትሌቲክስ ገጽታ አሁን ከምናውቀው የተለየ ነበረ። በተለያዩ የአውሮፓ ከተሞች የሚካሄዱ ውድድሮች አፍሪካውያን አትሌቶች የድል ቦታ አልነበራቸውም። ተሳትፏቸውም እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም።

እኤአ የ1960ው ሮም ኦሊምፒክ ግን ይህን ታሪክ እስከወዲያኛው የቀየረ ክስተት ይዞ መጣ። ጀግናው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ የዓለም አትሌቲክስን ገፅታ የለወጠውን ታሪክ በሮም ኦሊምፒያድ የማራቶን የባዶ እግር ድል የማይፋቅ ዐሻራ አኖረ። ይህም የዓለማችን ጥቁር አትሌቶች ተወዳድረው ማሸነፍ እንደሚችሉ ያሳየና ተነሳሽነትን የፈጠረ ነበር። ከዚያ ጊዜ አንስቶ የአበበን ዱካ ተከትለው ጥቁር አትሌቶች በተለይም በረጅም ርቀትና በማራቶን ውድድሮች የበላይነቱን ተቆጣጥረው ዛሬም ድረስ ዘልቀዋል።

የአበበ ቢቂላ ዘመን አይሽሬ የአትሌቲክስ ጀብዶች በታሪክ ማህደር የተፃፉት በወቅቱ ስፖርቱን በብቃትና በእውቀት በሚመሩ ሰዎች አስተዋፅኦም ጭምር ነው። አትሌቲክስ ዛሬ ላይ የኢትዮጵያ ኩራት እንዲሆን ልክ እንደ እንቁ አትሌቶቻችን ታሪክ የሚዘክራቸው ብዙ አርቆ አሳቢ የስፖርቱ አመራሮች የጣሉት መሠረት ትልቅ ነው። እነዚህ ጉምቱ የስፖርቱ አመራሮች ኢትዮጵያውያን ሮጠው ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ዘርፉን ከሀገር ተሻግሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ መምራትና ማስተዳደር እንደሚችሉ አስመስክረዋል። ለዚህም ይድነቃቸው ተሰማ እና ፍቅሩ ኪዳኔን የመሳሰሉ ታላላቅ ሰዎች ከአፍሪካ ተሻግረው እስከ ዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ድረስ የነበራቸው ተፅዕኖና ተሰሚነት ህያው ምስክር ነው።

ስፖርት በባህሪው ከዘመን ጋር እየተራመደ የሚዘምን ነውና በዚያው ልክ አብሮ መራመድ የሚችል ወቅቱን የዋጀ አመራር ግድ ይላል። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በአትሌቲክሱ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም የስፖርት አይነቶች አልታደለችም። ዛሬም ድረስ የዓለም ከዋክብት አትሌቶች መፍለቂያ ብትሆንም ይህን ፀጋዋን በሚገባው ደረጃ የሚያስተዳድርና የሚመራ ሰው ከፊት ማምጣትና ይበልጥ ውጤታማ እንድትሆን ማድረግ አልተቻለም። ይህም ስፖርቱን እጅከወርች አስሮ አላራምድ ሲለው በየጊዜው እየታዘብን እንገኛለን።

ኢትዮጵያ በዓለም አትሌቲክስ ያላት ተጽእኖ ፈጣሪነት በአትሌቶቿ ድል ብቻ የተወሰ ነው ቢባል ትክክል ነው። እንኳን በዓለም አትሌቲክስ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ተፅዕኖ የሚፈጥር የሀገሩ ውስጥ የስፖርቱን ችግሮች ማስተካከል የሚችል ሰው አጥታለች። በእርግጥ ሰው አጥታ አይደለም፣ ትክክለኛውን ሰው ማን ከፊት ያምጣው ነው ጉዳዩ።

ሌላው ዓለም በቴክኖሎጂ ተራቆ ስፖርቱን ሳይንስ አድርጎታል። ትናንት በአትሌቲክስ የማይታወቁ ሀገራት ዛሬ ላይ ችግሮቻቸውን በሳይንስና ምርምር እየቀረፉ የእኛ የምንላቸውን ድሎች ወደ መሻማት ተሸጋግረዋል። እኛ ደግሞ አትሌቲክስን አንድ ብሎ እንደሚጀምር ዓለም አቀፍ ውድድር በደረሰ ቁጥር በአትሌቶች መምረጫ መስፈርት ውዝግብ ውስጥ እንዳክራለን። አሁንም መነሻችንን ዞር ብለን ከማየት ይልቅ በቆምንበት መቅረታችን ከሌላው ዓለም ምን ያህል ወደ ኋላ እየጎተተን እንደሚገኝ መረዳት ካልቻልን ከገባንበት አዙሪት ልንወጣ አንችልም።

በርካታ ሀገራት በተለይም ምዕራባውያኑ በምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በረጅም ርቀትና ማራቶን ውድድሮች የተወሰደባቸውን የበላይነት መልሰው ለማግኘት የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ ባለፉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት ታዝበናል። በእኛው አስተዳደራዊ ስንክሳሮች የተማረሩና ቅር የተሰኙ ብርቅዬ አትሌቶችን አስኮብልለው ዜግነት በመስጠት ባንዲራቸውን በታላላቅ ዓለም አቀፍ መድረኮች ማውለብለብ ችለውበታል። የእኛን የአትሌቲክስ ስኬት ሚስጥር አጥንተውና ተመራምረው አትሌቶቻቸውን በእኛው የአየር ንብረት አሰልጥነው ጭምር ወደ ውጤት እየተመለሱ እንደሚገኙም የተደበቀ አይደለም። ለዚህም ኢትዮጵያና ኬንያ ለረጅም ዓመታት እየተፎካከሩ ውጤታማ የሆኑባቸውን ርቀቶች ባለፉት ዓመታት እያሸነፉ መገኘታቸው ማሳያ ነው።

ስኬታማ ባልሆኑባቸው የመም ረጅም ርቀት ውድድሮችን ቁጥር በመቀነስ ወይም በማጥፋት በኦሊምፒክ እና የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ብቻ እንዲወሰን የሚያደርጉትም ጥረት ይታወቃል። የአስርና አምስት ሺ ሜትር ውድድሮችን ከኦሊምፒክና ከዓለም ቻምፒዮና የመሰረዝ እንቅስቃሴ የጀመሩበትም ወቅት የሩቅ ታሪክ አይደለም።

የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ለመምራት ኃላፊነቱን የሚረከቡ ሰዎች በሀገር ውስጥ የሚታየውን አስተዳደራዊ ችግሮች የማራገፍ ብቻ ሳይሆን ከዚያ የገዘፈ ዓለም አቀፍ የቤት ሥራ የሚወጡ መሆን ይገባቸዋል። ለራሳቸው እንደሚመቻቸው አካሄዳቸውን የሚቀያይሩትን የዓለም አትሌቲክስ መሪዎችን በመሞገት መሰል ውሳኔዎችን የማስቀልበስ ተገዳዳሪ አቅም መፍጠር የሚችሉ መሆን አለባቸው።

በእርግጥ ይህ የቤት ሥራ የኢትዮጵያን አትሌቲክስ የሚመሩ ሰዎች ብቻ አይደለም። ኬንያና ዩጋንዳን ከመሳሰሉ በዓለም አትሌቲክስ ተፅዕኖ ያላቸው ሀገራት አትሌቲክስ መሪዎች ጋር መታገል አለባቸው። ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ የዓለምን አትሌቲክስ ገፅታ በመቀየር ፈር ቀዳጅ እንደሆነችው ሁሉ በዚህም ጉዳይ ከፊት መሰለፍ ይጠበቅባታል። ይህ ካልሆነ ግን ኢትዮጵያን ጨምሮ በእነዚህ ርቀቶች ስኬታማ የሆኑት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በትብብር አለመሥራታቸው እንዲሁም ማሳመንና ተጽእኖ መፍጠር የሚችል የአትሌቲክስ ባለሙያ አለማግኘታቸው ዋጋ እያስከፈላቸው መጓዙን ይቀጥላል።

ከስልሳና ሰባ ዓመታት በፊት እስከመኖሯም የተዘነጋችውን አህጉረ አፍሪካ በአትሌቲክስ ውጤት በማስመዝገብ ይቻላልን ያስተዋወቀችው ኢትዮጵያ መሆኗን ደግሞ ማስታወስ ተገቢ ነው። ወትሮውንም የስፖርቱ ፊት አውራሪ አብዮተኛ ናትና አሁንም የአትሌቲክሱን ዓለም የፖለቲካ ጎዳና በመጥረግ አርዓያነቷን ማስቀጠል ይጠበቅባታል። ስለዚህም በዓለም አትሌቲክስ ተሰሚ ለመሆንና በስራ አስፈጻሚው አፍሪካን ወክሎ ወንበር ለማግኘት የሚችሉ ግለሰቦችን ማፍራት የግድ ይለናል።

ኢትዮጵያ የይድነቃቸው ተሰማ እና የፍቅሩ ኪዳኔ ሀገር መሆኗን ዛሬም የሚያስመሰክሩ በዕውቀትና በዲፕሎማሲ ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎች የሏትም ለማለት አይቻልም። ነገር ግን ከሀገር ውስጥ አንስቶ ወደ አመራርነት እንዲመጡና ሃሳባቸውንም እንዲያንጸባርቁ ለስፖርቱ ስብራትም መፍትሄዎችን እንዲያመነጩ በማድረግ ረገድ የሚታየውን ክፍተት መጠገን ላይ ነው ችግሩ።

ከዚህ ቀደም በአህጉር አቀፍና በቀጣናዊ የስፖርት ማህበራት ውስጥ በአባልነትና በኃላፊነት የመመረጥ ዕድልን ያገኙ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ አመራሮች አንዳችም አበርክቶ ሳይኖራቸው የሥራ ዘመናቸውን ጨርሰው ከስፖርቱ ይገለላሉ። ይህ ከዚህ በኋላ መደገም የለበትም።

በመሆኑም አዲሱ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሥራ አስፈጻሚ ያገኘውን ዕድል እንዲሁ ከማባከን ይልቅ ከሀገራዊ ሥራው ጎን ለጎን ኢትዮጵያ የሚገባትን እንድታገኝ ሩቅ ዓላሚ ሊሆን ይገባል። አሁን ላይ እየተነሱ ያሉትን መሠረታዊ የአትሌቲክስ ችግሮች ዘመናዊ አካሄዶችን በመቀየስ፣ አደረጃጀትን በማስተካከል እንዲሁም ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር እጅና ጓንት ሆነው በመሥራት ሊቀርፉ ይችላሉ። ጠንካራ ጽህፈት ቤት፣ የቴክኒክ ኮሚቴ፣ የራሳቸውን መብት የሚጠይቁና ለስፖርቱ እድገት የሚታትሩ የሙያ ማህበራትን በማደራጀትና የየራሳቸውን ድርሻ አውቀው እንዲሠሩ ማድረግምን ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

ከምንም በላይ ሕግን ማስከበርና ዘመኑን የዋጀ አስተዳደርን ሥራ ላይ ማዋል የኢትዮጵያን አትሌቲክስ መጻኢ እድል ለመወሰን ቁልፍ ጉዳይ ነው። ራዕይ ያለውና የኢትዮጵያን አትሌቲክስ እንደጀግናው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ ከፍ አርገው ባስቀመጡት የክብር ማማ የማስቀመጥ ፍላጎት ያለው መሪ እይታው ዓለም አቀፋዊ ሊሆን ይገባል።

ሥራ አስፈጻሚው ከመመረጡ አስቀድሞ በነበረው የምረጡኝ ቅስቀሳ የተናገሯቸውና ያቀረቧቸው እቅዶች ወደመሬት ለማውረድ የሚጠበቅባቸው ቅንነት ብቻ ነው። የኢትዮጵያውያን ክብር ምክንያትና መገለጫችን ለሆነው አትሌቲክስ ከመሥራት የሚቦዝን ባለሙያ ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም። በተለያዩ ምክንያቶችና መልካም አስተዳደር ችግሮች ያኮረፉትም ቢሆኑ በሀገር ጉዳይ አይጨክኑምና በአንድነት ለተነሳ መሪ ተገዢ መሆናቸው አያጠራጥርም። ስለዚህም የሀገር ውስጡን የአትሌቲክስ ችግር ለመፍታት ከመሥራት እኩል ዓለም አቀፋዊነትን ማሰብና በተገኘው አጋጣሚ መጠቀም ያስፈልጋል። በዓለም ላይ ተጠቃሽ ከሆኑ ጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ እንደመሆኗ በገነባችው ስም ልክ ተጠቃሚ እንድትሆን ለማድረግ ከባለሙያዎች ጋር በምክክር መሥራትም የግድ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ስመጥርና ለሌሎችም ምሳሌ ሊሆን የሚችል ፌዴሬሽን መገንባት የአዲሱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዓላማ ሊሆንም ይገባል።

# ተጠየቅ

# «የትራንስፖርት አገልግሎቱን ሥርዓት የማስያዝ ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል እንጂ የሚላላ አይሆንም»

**አቶ ያብባል አዲስ**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ**



ፎቶ- በገባቦ ገብሬ

**ሞገስ ተስፋ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በከተማዋ ደህንነቱ የተጠበቀ ቀልጣፋ እና ተስማሚ አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል የተቋቋመ ነው::

አዲስ አበባ የሀገሪቱ ከዛም አልፎ የአፍሪካ ርዕሰ መዲና፣ ሶስተኛዋ ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ከተማ ነች። በየጊዜው እየሰፋች ያለች፣ ሰፊ ቁጥር ያለው ሕዝብ መኖሪያ ነች። ይህንን ተከትሎም ከፍ ያለ እና እያደገ የሚሄድ የትራንስፖርት አገልግሎት የምትፈልግ ከተማ ናት። ይህም የከተማዋን ፍላጎት ለማሟላት በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ አማራጮች ተግባራዊ ተደርገዋል፣ ከችግሩ ስፋት እና ውስብስብነት አኳያ ግን ችግሩ አሁንም ከተማዋን እየተፈታተነ ይገኛል።

በመዲናዋ ከትራንስፖርት መሠረተ ልማት፣ ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ ሕግ እና ሥርዓትን በአግባቡ ካለመተግበር ጋር በተያያዙ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እየተፈተነች ነው። ችግሩን ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶችም የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት አልቻሉም።

እኛም ከተማዋ በትራንስፖርት ዙሪያ እያጋጠሙ ስላሉ ችግሮች፣ ችግሮቹን ለመሻገር እየተደረጉ ስላሉ ጥረቶች እና እያስገኙ ስላለው ውጤት የአስተዳደሩን የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ያብባል አዲስን አነጋግረን እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል::

**አዲስ ዘመን፡- የከተማዋን የትራንስፖርት ችግሮች ለመፍታት ምን እየሠራችሁ ነው?**

**አቶ ያብባል፡-** የትራንስፖርት ቢሮው የ2017 ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድ አቅዶ ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት በ2016 ዓ.ም የበጀት ዓመት ሥራ ክንውን ወቅት ያጋጠሙ መሠረታዊ ችግሮችን በጥናት በመለየት፣ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ዕቅድ አውጥቶ ተግብሯል::

በጥናቱም የከተማ አስተዳደሩ ያለውን የብዙሃን ትራንስፖርት በብቃት የመጠቀም ችግር እንዳለበት፤ የብዙሃን ትራንስፖርት የአቅርቦትና የፍላጎት አለመጣጣም መኖሩን፤ የትራፊክ መጨናነቅ ከፍተኛ መሆኑ በአጠቃላይ ለትራንስፖርት አገልግሎቱ እንቅፋት መሆኑ በዝርዝር ተቀምጧል:: ከዚህ በተጨማሪ ዘርፉ የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዳሉበት ተመልክቷል። ችግሮቹን በ2017 በጀት ዓመት በመሠረታዊነት ማቃለል እንደሚገባ በመገንዘብ ችግሮቹን ሊፈታ የሚችል ዕቅድ አዘጋጅተን ወደ ሥራ ገብተናል::

ያለውን የብዙሃን ትራንስፖርት አቅም በተሟላ ሁኔታ ከመጠቀም አኳያ፣ ለከተማችን አገልግሎት የሚያቀርበው የከተማ አውቶብስ ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅትን ያሉበትን ችግሮች ለመፍታት ተቋሙን በአደረጃጀት፤ በአሠራር፤ በመመሪያ፤ በሰው ኃይል፤ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ራሱን እንዲያሻሽል የሪፎርም ሥራ እየተሠራ ነው::

ከማሻሻያ ሥራው ጎን ለጎን ያሉትን አውቶብሶች ወደ ስምሪት በማስገባት አገልግሎቱን እንዲያሻሽል የሚያደርግ ሥራ ተሠርቷል:: በዚህም በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድርጅቱ ካሉት አውቶብሶች በተጨማሪ 149 አውቶብሶችን ወደ ስምሪት እንዲገቡ አድርጓል:: በቀን 900 ሺ በላይ ሕዝብ እንዲያጓጉዝ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ እንዲሻሻል ተደርጓል::

የከተማ አስተዳደሩ የትራስፖርት ዘርፉን ለማሻሻል 80 አውቶብሶቹ ያሉት አደይ አበባ የሚባል የግል ትራንስፖርት ድርጅት ወደ አገልግሎት እንዲገባ ተደርጓል:: በተመሳሳይ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር አገልግሎት የነበረበትን የመለዋወጫ እቃ እጥረት ችግር በመፍታት ባለፈው ዓመት በየቀኑ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ባቡሮች ቁጥር ከ13 በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ወደ 16 ማሳደግ ተችሏል:: ይህም ለዘርፉ አገልግሎት መሻሻል ከፍተኛ አቅም ፈጥሯል::

**አዲስ ዘመን፡- በዘርፉ ከሚታዩ ችግሮች በተለይ ወደ ሥራ መግቢያና ከሥራ መውጫ ሰዓት ከፍተኛ የትራንስፖርት ችግር ይስተዋላል፤ ቢሮው ችግሩን ለምን መፍታት አልቻለም?**

**አቶ ያብባል፡-** ከብዙሃን ትራንስፖርት ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር በጊዚያዊነት ለማቃለል ከፌዴራል ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በጊዜያዊነት መናኸሪያ ላይ የሚገኙ ሀገር አቋራጭ አውቶብሶች ማታ ማታ ከፍተኛ የሆነውን ሰልፍ እንዲያነሱ እየተደረገ ነው:: በዚህም በየቀኑ ከ120 እስከ 150 የሚደርሱ ሀገር አቋራጭ አውቶብሶች በተመረጡ አካባቢዎች የሚታየውን ሰልፍ እንዲያነሱ ተደርጓል::

በሌላ በኩል የሕዝብ ትራንስፖርት የሚባሉት ኮድ አንድና ኮድ ሶስት ታክሲዎች ከታሪፍ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ቅሬታ ነበረባቸው:: የነዳጅ ድጎማ መነሳቱ፤ ቀድሞ ከተደረገው የታሪፍ ማሻሻያ በኋላ አምስት ጊዜ የነዳጅ ዋጋ ለውጥ መደረጉ እና ይህን ተከትሎ ታሪፉ ያልተሻሻለ መሆኑ ለቅሬታው ምንጭ ሆኗል:: ከዚህ የተነሳም ጠዋትና ማታ ከስምሪት ሲደበቁ ነበር:: የከተማ አስተዳደሩ ጉዳዩን በዝርዝር ገምግሞ የሕዝብ ትራስፖርትን ከማሻሻል እና አቅርቦቱን ከማሳደግ አኳያ ከፍተኛ በመሆኑ ታሪፋቸው እንዲሻሻል አድርጓል::

በሩብ ዓመቱ እነዚህንና መሰል ርምጃዎችን በመውሰዳችን በየቀኑ ለማጓጓዝ ያቀድነው 3 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሕዝብ ሲሆን በተደረገው የማሻሻያ ሥራ 3 ነጥብ 46 ሚሊዮን ሕዝብ በየቀኑ ትራንስፖርት እንዲያገኝ ተደርጓል:: በዚህም የመጀመሪያውን ችግር ከመፍታት አኳያ በጣም መሠረታዊ ለውጥ አምጥተናል::

ሌላው በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል የነበረውን ልዩነት የማጥበብ ሥራ መሥራት ነው። የከተማ አስተዳደሩ ቀደም ብሎ ግዥ የፈጸመባቸው መቶ የኤሌክትሪክ አውቶብሶች ወደብ ላይ ደርሰዋል:: ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው በሶስት አራት ወር ውስጥ ተገጣጥመው ወደ አገልግሎት የሚገቡበት ሁኔታ ይፈጠራል::

መንግሥት በነደፈው የኮሪደር ልማት ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው ለትራንስፖርት ዘርፉ ነው:: በዚህም ቅድሚያ የሚሰጠው የእግረኛ እና የብስክሌት ትራንስፖርት ነው:: ይህ ለከተማ አስተዳደሩ የትራንስፖርት መቀላጠፍ ከፍተኛ ሚና አለው:: ምቹ የእግረኛ መንገድ ሲኖር ቅርብ ሰፈር የሚጓዙ ሰዎች በእግራቸው ወደ ቤታቸው ይጓዛሉ:: ብስክሌት ያላቸውም በተመሳሳይ በተሠራላቸው የብስክሌት መንገድ ይጠቀማሉ::

የታክሲና የአውቶብስ ተርሚናሎች፤ የመኪና ፓርኪግ መሠረታቸው የትራፊክ መጨናነቁ ላይ ከፍተኛ መሻሻል እንዲመጣ አድርጓል:: እንደ አደይ አበባ የመሳሰሉ አደባባዮች እየፈረሱ ወደ ትራፊክ ምልክት እንዲቀየሩ ተደርጓል:: ዲያስፖራ፤ ቀበና፤ ጀርመን አደባባይ፤ ሳሊሀተ ምህረትና መሰል አደባባዮች ተጠቃሽ ናቸው::

እነዚህ መሠረተ ልማቶች በመሠራታቸው አገልግሎቱ በከፍተኛ ሁኔታ ተሻሽሏል:: ከዚህ በተጨማሪም የትራስፖርት ቢሮ ተቆጣጣሪዎች፤ የትራፊክ ማኔጅመንት፤ በትራፊክ ፖሊስ ተቆጣጣሪዎች የአዲስ አበባ ከተማን የትራፊክ መጨናነቅ ለመቀነስ ሰፊ ሥራ እየሠሩ ነው:: በአንዳንድ መንገዶች ጠዋትና ማታ መኪና ማቆም ተከልክሏል:: ይህንና መሰል ርምጃዎች በመወሰዳቸው በሩብ ዓመቱ የትራፊክ መጨናነቅ በመቀነስ ረገድ የሚታይ ሥራ ተሠርቷል::

**አዲስ ዘመን፡- በትራንስፖርት ታሪፍ በሚታዩ ጭማሪዎች ተገልጋዩ ቅሬታ እያነሳ ነው፣ በዚህ ላይ የእርስዎ ምላሽ ምንድን ነው?**

**አቶ ያብባል፡-** ታሪፍ በዝቷል የሚል ሃሳብ ይነሳል:: ነገር ግን ታሪፍ የሚጨምረው አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ተከትሎ ነው:: የነዳጅ ድጎማ ሲነሳ እና ዋጋ ማሻሻያ ሲደረግ ታሪፉ አብሮ ይሻሻላል:: ትልቁ የትራንስፖርት ወጪ ነዳጅ በመሆኑ የሳንቲም ጭማሪ በተደረገ ቁጥር የታሪፍ ጭማሪ መደረጉ የማይቀር ነው:: ታሪፉ የበዛ መስሎ የታየው በተከታታይ አምስት ጊዜ የነዳጅ ዋጋ ሲጨምር ታሪፍ አለመሻሻሉ ነው።

በየጊዜው ታሪፉ እየተሻሻለ ቢመጣ ኖሮ ጭማሪው ዝቅተኛ ይሆን ነበር:: ተከማችቶ አንድ ጊዜ ስለተተገበረ የበዛ ይመስላል:: ነገር ግን የታሪፍ አጨማመር የራሱ የሆነ ቀመር አለው:: አስተዳደራዊ እና የመለዋወጫ እቃዎች ወጪዎች እና ሌሎች ጉዳዮች ታይተው ዓለም አቀፋዊ የጭማሪ ስታንዳርድን ተከትሎ የተደረገ ነው:: የትራንስፖርት ታሪፉ በኪሎ ሜትር ሲሆን አጭር፤ መካከለኛ እና ረጅም ኪሎ ሜትሮችን ታሳቢ ተደርጎ ነው:: ጭማሪው በመገናኛ ብዙሃን በዌብሳይት እንዲጫንና እንዲደርስ እንዲሁም አገልግሎት በሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ውስጥ በሚታይ ቦታ እንዲለጠፍ ተደርጓል::

እያንዳንዱ የታክሲ ተጠቃሚ የታሪፉን ዋጋ እንዲያውቅ መነሻ እና መድረሻው መሠረት ተደርጎ ታሪፍ በየታክሲው ተቀምጧል:: የቢሮው ትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ትራፊክ ፖሊስ እና የትራፊክ ማኔጅመንት ተቆጣጣሪዎች ከታሪፍ ውጭ እንዳይጭኑ የቁጥጥር ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል ግንዛቤ ተፈጥሮላቸዋል::

በየቀኑም የቁጥጥር ሥራ እየተሠራ ነው:: ነገር ግን በተግባር ስናየው ሁሉም አካባቢ ጉዳዩን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ጉድለቶች አሉ:: አሁንም ቢሆን ከታሪፍ በላይ ተገልጋዩን የሚያስከፍሉ ታክሲዎች፤ ከታሪፍ በላይ እንዲከፈል ግፊት የሚያደርጉ የተራ አስከባሪዎች እንዳሉ ገምግመናል:: ችግሩን የምንፈታው በየጊዜው የተገልጋዩን ግንዛቤ በማሳደግ ከታሪፍ በላይ አልከፍልም ብሎ ራሱ መብቱን እንዲያስከብር የማድረግ ሥራ በመሥራት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ዘርፉ የመልካም አስተዳደር ችግር ያለበት ነው፤ ችግሩን ለመፍታት ምን እየሠራችሁ ነው?**

**አቶ ያብባል፡-** በዘርፉ ላይ ያለው የመልካም አስተዳደር ችግር ከፍተኛ ነው:: ከሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ጋር፤ ከአሽከርካሪ ተሽከርካሪ አገልግሎት ተያይዞ፤ ከተራ አስከባሪዎች፤ ከትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች ጋር በዘርፉ የሚነሱ ከፍተኛ የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮች አሉ:: ቢሮው በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጀንዳው በዘርፉ ያሉ ተቋማት በጋራ የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር እቅድ አቅደው እንዲሠሩ ተደርጓል::

በሩብ ዓመቱ መሠረታዊ የሚባሉ መሻሻሎች እንዳሉ ታይቷል:: የተቋሙ ዋናው የመልካም አስተዳደር ችግር ጠዋትና ማታ ሕዝባችን በቂ የትራንስፖርት አገልግሎት አለማግኘት ነው:: ችግሩን በመፍታት በኩል በመሠረታዊነት ለውጥ አምጥተናል:: ነገር ግን የአዲስ አበባ ሕዝብ በየጊዜው እየጨመረ ስለሚሄድ መሻሻሉ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግም ገና ብዙ መሥራት እንዳለብን አይተናል::

**አዲስ ዘመን፡- አውቶብሶችም ሆኑ ታክሲዎች በተገቢው መንገድ አገልግሎት ሲሰጡ አይታይም:: ለዚህም የቁጥጥር ማነስን እንደ ምክንያት የሚያነሱ አሉ፤ በእናንተ በኩል የችግሩ ምንጭ ምንድነው ትላላችሁ?**

**አቶ ያብባል፡-** ከሕዝብ ትራንስፖርት ጋር ተያይዞ የእኛ ተቆጣጣሪዎች ምሽት ላይ እና በበዓል ቀን ቅዳሜና እሁድ የማይገቡበት ሁኔታ ነበር:: እነሱ በማይኖሩበት ጊዜ ቁጥጥሩ ስለሚላላ እንደ ታክሲ፤ ሀይገር፤ ቅጥቅጥ የሚባሉ የትራስፖርት ዓይነቶች ከታሪፍ በላይ የሚያስከፍሉበት፤ ከመስመር ውጭ የሚሠሩበት እና ሥራ የሚያቆሙበት ሁኔታ ነበር:: ቢሮው ይህን ለማስተካከል በሁሉም መስመሮች ባይሆንም ማታ ማታ እና ቅዳሜ እና እሁድ የትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች እንዲኖሩ አድርገናል::

ጠዋትና ማታ ላይ የትራፊክ ፍሰቱ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ አንዳንድ ታክሲዎች ወደ ስምሪት የማይገቡበት ሁኔታ ነበር:: ችግሩን ለመፍታት ቁጥጥሩን ለማጥበቅ የቁጥጥር ሥራውን በማጥበቅ እንዲሁም በመግባባት ችግሩን ለመፍታት እየተሞከረ ነው:: ከታክሲ ማህበራትና ባለንብረቶች ጋር ተግባብቶ ለመሥራት ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ በዚህም የሕዝብ አገልጋይ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ተደርጓል::

እነሱ በሚፈጥሩት ውስን ችግር ሕዝቡ ላይ እየደረሰ ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ እና የመልካም አስተዳደር ችግር ከፍተኛ ነው:: በመግባባትና በመነጋገር ችግሩን ለማሻሻል ጥረት የተደረገ ቢሆንም ሁሉም ችግር በመግባባት ስለማይፈታ የትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎችን ቁጥጥር የማጠናከር ሥራ ተሠርቷል::

በዚህም በየቀኑ ከ400 በላይ ታክሲዎች በተለያየ መንገድ ይቀጣሉ:: የታክሲ ባለንብረቶች አደረጃጀት ችግር አለበት:: በቀጣይ አደረጃጀቱን በማሻሻል አገልግሎቱ በካምፓኒ የሚሰጥ እንዲሆን ይሠራል:: አሁን ባለው ሁኔታ ግን ክትትልና ቁጥጥሩን አጠናክረን ለማሻሻል ጥረት እያደረግን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የአንበሳ አውቶብስ አገልግሎት ምቾት እና ንጽህና የጎደለው ስለመሆኑ ተገልጋዮች ቅሬታ ያነሱበታል፣ ቢሮው ችግሩን ለመቅረፍ ምን እየሠራ ነው?**

**አቶ ያብባል፡-** የከተማ አውቶብስ ድርጅት በአሠራር፤ በአደረጃጀት፤ በሰው ኃይል፤ በቴክኖሎጂ እና በንጽህና ሪፎርም እየተደረገ ነው:: የከተማዋን ትልቁን የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጠው የከተማ አውቶብስ ድርጅት ነው:: በዚህ በጀት ዓመት በሁሉም መንገድ መሠረታዊ ለውጥ የምናመጣበት ነው::

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## ‹‹የትራንስፖርት አገልግሎቱን...

**ከ6ኛ ገፅ የዞረ**

ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን የመተግበር ሥራ የተጀመረ ሲሆን ሲጠናቀቅ ድርጅቱ የሚሰጠውን አገልግሎቱን ወደ ተሻለ ደረጃ ያሳድገዋል የሚል እምነት አለን።

እንደሚታወቀው በብዙሃን ትራንስፖርት ላይ የግል ባለሀብቱ ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው። ይህን ለማሳደግ እየሠራን ነው። አሁን ላይ በዘርፉ የሚንቀሳቀሱ የመንግሥት አገልግሎት ሰጭ ኦፕሬተሮች ናቸው። ይህም ሆኖ ብዛት ያላቸው የግል ዘርፉ ኦፕሬተሮች መፈጠር አለባቸው። ከተማ አስተዳደሩ በዘርፉ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶችንም እያነጋገረ ነው፤ ከተሳካለት 100 የሚሆኑ የኤሌክትሪክ አውቶበሶች ይዞ የሚሠራ የግል ባለሀብት ወደ ሥራ እንዲገባ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው። በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የማበረታቻ ሥርዓት እየተጠናም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የቢሮው ተራ ተቆጣጣሪዎች ባሉበት በተራ አስከባሪ ስም የተደራጁ ግለሰቦች የተራ በሚል የሚያስከፍሉትን ገንዘብ ቢሮው ያውቃቸዋል? ከአሽከርካሪዎች የሚቀበሉት የብር መጠን ከፍ ለማድረግ ታክሲዎች ትርፍ እንዲጭኑ፤ ከታሪፍ በላይ እንዲያስከፍሉ ሲገፋፏቸው ይስተዋላል፤ እነዚህንና መሰል ችግሮች ለማስቆም ቢሮው ምን እየሠራ ነው?**

**አቶ ያብባል፡-** ልክ ነው። አንዳንድ ሕገ ወጥ ተራ አስከባሪዎች አሉ። ከሕገ ወጥ አሽከርካሪዎች ጋር ሆነው ተጨማሪ ክፍያ የሚያስከፍሉ፤ መስመር የሚያስቀይሩ እና ከአቅም በላይ እንዲጫን የሚያደርጉ አሉ። በተለይ የቢሮው ስምሪት ተቆጣጣሪዎች በሌሉበት ጊዜ ይህ ልምምድ ሰፋ ይላል። ተራ አስከባሪ ያስፈለገው ሰልፍ ላይ የመንገደኛውን ደህንነት እንዲጠበቅ እና ታክሲዎች ሥርዓት እንዲይዙ ነው። አሁን ላይ የእርምት ርምጃዎችን በመውሰድ መሻሻሎች አሉ። በሁሉም አካባቢ ተራው እስከሚደርሰው ድረስ የሚፈጠር ትርምስ የለም፤ ሥርዓት ይዞ፤ ተሰልፎ ትራንስፖርት እየተገለገለ ነው። አሽከርካሪዎችም ሥርዓት ይዘው በተራቸው አገልግሎት እየሰጡ ነው።

አገልግሎት ሰጭዎች የመነሻውን ታሪፍ መሠረት አድርገው ከመነሻ እስከ መድረሻ የታሪፉን መሠረት ያደረገ ሕጋዊ ክፍያ እያገኙ ነው። ነገር ግን ከዚህ ሕጋዊ አሠራር ውጭ ከታሪፍ በላይ እንዲከፈል፤ ከመቀመጫው በላይ ትርፍ እንዲጫንና መስመር እንዲቆራረጥ የሚያደርጉ ተራ አስከባሪዎች አሉ። በዚህ ላይ ጥብቅ የሆነ ርምጃ እየወሰድን ነው። በቀጣይ የተራ አስከባሪዎችን የአሠራርና የአደረጃጀት ከመሠረቱ ለማሻሻል እና ከንክኪ ነፃ ለማድረግ አሠራር እያዘጋጀን ነው። አሠራሩ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል።

አጠቃላይ የትራንስፖርቱን ዘርፍ ምቹ ከማድረግ አኳያ ብዙ ጉድለት አለ። በተለይ ኮድ አንድ የሚባሉ ታክሲዎች በጣም ለተሳፋሪ ምቹ ያልሆኑ አሮጌ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በተደጋጋሚ አገልግሎት ላይ እያሉ የሚቆሙ፤ ጋራዥ የሚገቡ፤ መንገድ ላይ የሚገፉ፤ የካርቦንዳይኦክሳይድ ልቀታቸው ከፍተኛ ነው። መቀመጫቸው የማይመች ሲሆን ቴክኖሎጂ ለመቀበል አስቸጋሪ ናቸው።

የከተማ አስተዳደሩ የትራስፖርት ዘርፉ አቅርቦት ችግር ስላለበት እንጂ ተሽከርካሪዎቹ ከአገልግሎት ውጭ መሆን ነበረባቸው። ባለቤቶችም ታክሲዎቻቸውን ወደ አዲስ የመቀየር ሥራ መሥራት አለባቸው። ይህን ለማድረግ የሚያስችል ሥራዎች ተጀምረዋል። የታክሲ ማህበራትና ባለንብረቶች አሮጌ ታክሲዎችን ከመንግሥት ብድር እና የታክስ ቀረጥ ነጻ ድጋፍ ካገኙ ወደ አዲስ መቀየር አለባቸው የሚል ስምምነት ላይ ተደርሷል። ስለዚህ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግላቸው ከሆነ በአጭር ጊዜ ዘመናዊ ታክሲ ይዘው አገልግሎት የሚሰጡበት ሁኔታ ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡-የቢሮው የስምሪት ተቆጣጣሪዎች በተለይም እሁድና ቅዳሜ ባለመሥራታቸው በአንድ በኩል ሰዎችን የሚጠራ ታክሲ ፤ በሌላ በኩል ታክሲ የሚጠባበቅ ረጃጅም የተሳፋሪ ሰልፍ ይታያል። ይህን ዓይነት ችግር የምትፈቱት መቼ ነው?**

**አቶ ያብባል፡-** የሕዝብ የትራንስፖርት ፍሰቱ በየጊዜው የሚቀያየር ስለሆነ ስምሪቱ በየጊዜው ይከለሳል። ለምሳሌ ፒያሳ አካባቢ የነበረው ነዋሪ በኮሪደር ልማቱ ምክንያት ወደ ሌላ አካባቢ ተዛውሯል። ስለዚህ በሄደበት አካባቢ የትራንስፖርት ፍላጎት ይጨምራል። ቀድሞ ከተነሳበት አካባቢ ላይ ደግሞ የትራስፖርት ፍላጎቱ ይቀንሳል። በዚህ ሳቢያ በየሩብ ዓመቱ የታክሲዎችና የአውቶብሶች የስምሪት ክለሳ ይደረጋል። የተሽከርካሪ የአቅርቦት መጠን የተጠቃሚውን ብዛት መሠረት ተደርጎ ለማጣጣም ጥረት ይደረጋል።

አንዳንድ ጊዜ የሳሳ አንዳንድ ጊዜ የበዛ ይመስላል፤ ነገር ግን ስምሪቱ በጥናት ተመስርቶ የሚከናወን ነው። የሕዝብ ክምችት የሚታይባቸው ላይ ችግሩን ለመፍታት በአውቶብስ አማካኝነት ጥረት እየተደረገ ነው። አሁን ላይ የታክሲ አገልግሎት ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የብዙሃን ትራንስፖርት የምንለው አገልግሎት ባለመስፋፋቱ ነው። ችግሩን ለመቅረፍ የከተማ አስተዳደሩ ዋና ትኩረት የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ማስፋፋት ነው። የሌሎች ሀገራት ተሞክሮም የሚያሳየው የታክሲ ትራንስፖርት ሳይሆን የሕዝብ ትራንስፖርት ነው። በእኛ ሀገር ግን የአውቶብስ ትራንስፖርት፤ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት፤ የፈጣን አውቶብስ አገልግሎት ገና ስላልተስፋፋ ታክሲ ላይ ጥገኛ ነን።

ከተማ አስተዳደሩ እየሠራ ያለው የብዙሃን ትራንስፖርትን ለማሳደግ ነው። ብዙሃን ትራንስፖርት የታሪፍ፤ የስምሪት ጉዳይ አይነሳም። የታክሲ አገልግሎትን ስንመለከት ግን ባለንብረቱ ቁርስ ሲባላ፤ ቤተእምነት ሲሄድ፤ ሲታመም እና መሰል ጉዳዮች ሲገጥመው ይቆማል። ይህ ሁኔታ ባለበት ተቆጣጥሮ ለማሠራት ከፍተኛ የሆነ ፈተና ነው።

የቢሮው የትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች ባሉበት አካባቢ ቁጥጥር አለ። ነገር ግን ሁሉም ቦታ ላይ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ማድረግ አይቻልም። ቁጥጥር በሌለበት ቦታ ላይ ሕገ ወጥ ድርጊት ሲፈጽሙ ይታያል። ችግሩን ለመቅረፍ በምንችለው ልክ የሰው ኃይል አሰማርተን እየተቆጣጠርን ነው።

የትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች ገና በሁሉም ቦታ ሳይሆን የማታ ሰልፍ ባለባቸው የተመረጡ ቦታዎች ላይ ብቻ እየሠሩ ነው። በተመደቡበት ቦታ ላይ እስከ ምሽቱ ሁለት ሶስት ሰዓት ድረስ ትኩረት አድርገው ይሠራሉ። ሥራው የተጀመረው በቅርብ ጊዜ ቢሆንም ተቆጣጣሪዎች ማታም ትርፍ ጊዜያቸውን ተጠቅመው ቁጥጥሩን እንዲያጠናክሩ ተደርጓል።

**አዲስ ዘመን፡-የታክሲና የራይድ ሹፌሮች ጥፋት ሳንሠራ እየተቀጣን ነው እያሉ ቅሬታ ያቀርባሉና ከትራፊክ ማኔጅመንት ጋር ያላችሁ ቅንጅታዊ አሠራር እስከምን ድረስ ነው?**

**አቶ ያብባል፡-** በእኛ ሀገር ሁለት የተለያየ ሃሳብ አሉ። ቁጥጥር ሲጠበቅ በዛ፤ ሲላላ ደግሞ ቁጥጥር የለም ይባላል። ከዚህ የተነሳ “እንቀጣለን” የሚለው ሃሳብ በሚዛኑ ማየት ያስፈልጋል። እንደ አዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ከሆነ ቁጥጥሩ ዝቅተኛ ነው። ምክንያቱም አገልግሎቱን ለመከታተል የምንጠቀመው ቴክኖሎጂ የለም። ቴክኖሎጂ በሚጠቀሙ ሀገሮች የትኛውም ተሽከርካሪ ከተፈቀደለት ቦታ ውጭ መቆም አይችልም።

እኛ ሀገር ግን ሁሉም አሽከርካሪ መንገድ ላይ ሰው ይጭናል፤ ያወርዳል፤ መኪና ያቆማል። ይህ ልምምድ ትክክል አይደለም። በኮሪደር ልማቱ ችግሩን ለመፍታት ሥፍራዎች ተለይተው ተገንብተዋል፤ ከተፈቀደው ቦታ ውጭ መጫንና ማውረድ፤ መኪና ማቆም አይቻልም። ለዚህም አሠራርና ሕግን በተከተለ መንገድ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረጋል። ስለሆነም እንደ ከዚህ ቀደሙ የትም ቦታ ላይ ማውረድና መጫን አይቻልም። ሕግን በተከተለ አግባብ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል ከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው።

ለመጫኛና ማውረጃ ከተዘጋጀው ቦታዎች ውጭ መኪና አቁሞ ማውረድና መጫን ፈጽሞ የተከለከለ ነው። ክልከላውን ተላልፎ የተገኘ አሽከርካሪ ይቀጣል፤ ቅጣቱም ጨምሯል። በቀጣይም የትራንስፖርት አገልግሎቱን ሥርዓት የማስከበር ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል እንጂ የሚላላ አይሆንም።

ታክሲዎችም ይህንን ማወቅ እና ሕጉን መጠበቅ አለባቸው። የትራፊክ ማኔጅመንት ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል። ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር መሻሻሎች አሉት። ቢሮውና የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን፤ የትራፊክ ማኔጅመንትና የትራፊክ ፖሊስ በቅንጅት እየሠሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከተማዋን በማዘመን ሂደት ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡ አብሮ እንዲዘምን ከማድረግ አኳያ በቀጣይ ምን አስባችኋል?**

**አቶ ያብባል፡-** የከተማ አስተዳደሩ በኮሪደር ልማት የከተማዋን ገጽታ እየቀየረ ነው። ዓላማው አዲስ አበባን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ከተማ ማድረግ ነው። ከዚህ አኳያ ትልቅ ትኩረት የተሰጠው የትራንስፖርት ዘርፉ ነው። ከትራንስፖርት አገልግሎት አኳያ ቅድሚያ የሚሰጠው የእግረኛ ትራንስፖርት ነው። በሌሎች ሀገራት ያለው ተሞክሮ የሚያሳየው ይህን ነው።

> **አጠቃላይ የትራንስፖርቱን ዘርፍ ምቹ ከማድረግ አኳያ ብዙ ጉድለት አለ። በተለይ ኮድ አንድ የሚባሉ ታክሲዎች በጣም ለተሳፋሪ ምቹ ያልሆኑ አሮጌ ናቸው**

ሞተር አልባ ትራንስፖርት የሚበረታታ ነው። ከዚህ አንጻር አዲስ አበባ በመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት መቶ ኪሎ ሜትር የሚጠጋ የእግረኛ መንገድ፤ ከመቶ ኪሎ ሜትር በላይ የብስክሌት መንገድ ገንብታለች። ግንባታው የሞተር አልባ ትራንስፖርት በማበረታታት በኩል ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። እስካሁን ባለው ሁኔታ እግረኞች እየተበረታቱ ነው።

የብስክሌት ትራንስፖርትን ስንመለከት በግለሰቦች ደረጃ እንጂ በአማራጭ ትራንስፖርትነት ወደ ሥራ የተገባበት አይደለም። አሁን ላይ እንደ ከተማ የብስክሌት ኦፕሬተር አልተፈጠረም። ለዚህም ቢሮው የብስክሌት ኦፕሬተሮችን መፍጠር የሚያስችል የአደረጃጀትና የአሠራር መመሪያ አዘጋጅቷል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ የአደረጃጀትና የአሠራር መመሪያ ተግባራዊ ሲሆን በከተማ አስተዳደሩ የብስክሌት መጋራት የትራንስፖርት ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል።

ይህ ሲሆን ከፍተኛ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ኦፕሬተር ይኖራል። ለምሳሌ ከሃያት ወደ ሲኤምሲ፤ ከሜክሲኮ ወደ ሳር ቤት፤ ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ ስንሄድ የምናየው የእግረኛ መንገድ ከፍተኛ መኪና ተጠቃሚ ነበር። አሁን ላይ ግን ማህበረሰቡ መንገዱ በመሠራቱ አጫጭር መንገዶችን የሚጓዘው በእግሩ ነው። ይህ ሲሆን የትራንስፖርት እንቅስቃሴውን ያሻሽላል።

በኮሪደር ልማቱ መንገዶች የመጫኛና የማውረጃ ቦታ እንዲኖራቸው ተደርጓል። ይህም ትናንት ያልነበረ ዛሬ ላይ የሚታይ ነው። ይህ የትራንስፖርት ዘርፉን ወደ ዘመናዊነትና ተወዳዳሪነት የሚያመጣ ነው። ስለዚህ ከተፈቀደው ቦታ ውጭ መጫንና ማውረድ ስለማይቻል የትራንስፖርት እንቅስቃሴው ሰላማዊና የተቀላጠፈ ይሆናል።

ከ185 በላይ የታክሲና የአውቶብስ መጫኛና ማውረጃ ቦታዎች በመጀመሪያው የኮሪደር ምዕራፍ ተሰርተዋል። በተጨማሪም ከተማዋ ካሁን በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ ተርሚናሎችና ፓርኪንጎች አልነበሩም። በለውጡ መንግሥት የመስቀል አደባባይ፤ አንድነት ፓርክ፤ ዓድዋ ድል መታሰቢያ የመሳሰሉ ፓርኪንጎች ተገንብተዋል።

በሁለተኛውም ምዕራፍ ኮሪደር ልማት በርካታ ፓርኪንጎች እየተገነቡ በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። መውጫ መግቢያ ላይ ቴክኖሎጂ የሚጠቀም፤ መኪና የሚያቆም ሰው ደግሞ ከገንዘብ ንክኪ ነፃ በሆነ መንገድ በሞባይል ባንኪንግ እና በስማርት ስልክ አማካኝነት የሚከፈልበትን ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እየሠራን ነው።

በመጀመሪያው የኮሪደር ልማት ብቻ 32 ፓርኪንጎች ለምተዋል። በህንጻ መልክ ጭምር በሁለተኛ መሠረት እና ከዚያ በላይ መሠረት ያላቸው ፓርኪንጎች እየተሠሩ ነው። በሁለተኛው ኮሪደር ልማት ከ58 በላይ ፓርኪንጎች ይሠራሉ። ይህ ለከተማችን ዘመናዊነትና ተወዳዳሪነት ብሎም ለተቀላጠፈ የትራንስፖርት አገልግሎት እና የትራፊክ ፍሰት መሻሻል ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

በአንድ ጊዜ ከ600 በላይ አውቶብሶችና ታክሲዎች ማስተናገድ የሚችሉ ተርሚናሎች ተሠርተዋል። በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ፕሮግራም ሰፋፊ የተርሚናል ግንባታ እቅዶች አሉ። ዘመኑ የትራንስፖርት ዘመን ነው። አዲስ አበባ የብስክሌት፤ የእግረኛ መንገድ፤ ተርሚናሎችን እያሰፋች በሄደች ቁጥር የአዲስ አበባ ትራንስፖርት አገልግሎት ይሻሻላል።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና እንደመሆኗ መጠን ዘርፉን በቴክኖሎጂ መምራትን ይጠይቃል፤ ከዚህ አንጻር ቢሮው በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት እንዲሰጥ ከማድረግ አኳያ ምን ሠርቷል?**

**አቶ ያብባል፡-** አጠቃላይ የትራንስፖርት ዘርፉ በቴክኖሎጂ መመራት አለበት። በኮሪደር ልማቱ አንዱ ትኩረት የተሰጠው «ITS» የተባለ የኢተለጀንስ ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲኖር የሚያግዝ ቴክኖሎጂ አልምቶ ወደ ሥራ ማስገባት ነው። ቴክኖሎጂው በኮሪደር ልማቱ በቀኝና በግራ ልክ እንደ ቴሌ እንደ ውሃ መስመር አብሮ እየተዘረጋ ነው። በተጨማሪም መገናኛ ላይ የትራፊክ ማኔጅመት ሲስተም የሚመራበት ህንጻ ተገንብቷል።

በአጠቃላይ የከተማዋን ትራንስፖርት ማኔጅመንት የምንቆጣጠርበት ማዕከል በህንጻ ደረጃ ተገንብቶ ተጠናቋል። ከዚህ በኋላ የሚቀረው ቴክኖሎጂ ሲሆን ግዥ እየተካሄደ ነው። ሲጠናቀቅ በየኮሪደር ከተዘረጋው አይቲኤስ ጋር እንዲገናኝ በማድረግ የትራንስፖርት ዘርፉን በቴክኖሎጂ መቆጣጠር የሚቻልበት ሥርዓት ይፈጠራል። ከቅርብ ጊዜ በኋላ የትራፊክ ማኔጅመንቱን በቴክኖሎጂ የምንቆጣጠርበት ሥርዓት ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡- ከቅርብ ጊዜ በኋላ ሲባል መቼ ማለት ነው?**

**አቶ ያብባል፤-** ይህ የሚሆነው በሂደት ነው። ለምሳሌ ሞዴል የሚሆን ሥራ ከእንግሊዝ ኢምባሲ ወደ ጎላጎል እየተሠራ ነው። ግንባታው ሲጠናቀቅ ከማዕከሉ ጋር በማገናኘት ኮሪደሩን በቴክኖሎጂ መቆጣጠር እንጀምራለን። ይህ ምናልባትም በሚቀጥለው ዓመት ተግባራዊ ይደረጋል። ሥራው በዚህ መልኩ እየሰፋ አጠቃላይ የአዲስ አበባን ትራንስፖርት በቴክኖሎጂ የምንቆጣጠርበት ሥርዓት ይፈጠራል።

የባቡር፤ የአውቶብስ ትራንስፖርት በቴክኖሎጂ በመደገፍ የትኛው አውቶብስ በየትኛው መስመር ገብቷል፤ በስንት ኪሎ ሜትር እየሄደ ነው፤ በስንት ሰዓት እየተነሳ እንደሆነ እና ምን ያህል አገልግሎት እየሰጠ ስለመሆኑ ቢሮ ላይ ሆኖ በቴክኖሎጂ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ተግባራዊ እየተደረገ ነው። አሽከርካሪና ተሽከርካሪም የሚሰጡት አገልግሎት በመንጃ ፈቃድ እና መሰል ሥራዎች በቴክኖሎጂ በመደገፍ እየተሠራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የቢሮው የስምሪት ተቆጣጣሪዎች በብር የስምሪት አቴንዳንስ ይሞላሉ የሚል ቅሬታ ይነሳልና ዘርፉን እንደሚመራ ተቋም ሠራተኞችን የምትከታተሉበት አግባብ ምን ይመስላል?**

**አቶ ያብባል፡-** እውነት ለመናገር የትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች በጣም እየደከሙ ነው። 12 ሰዓት ወደ ሥራ ገብተው የሚሠሩት አምሽተው ነው። የሚሠሩት ጸሐይ ላይ ብርድ፤ አቧራ ላይ እና ጭስ ላይ ነው። የእኛ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች ብቻ ሳይሆን የትራፊክ ማኔጅመንት ተቆጣጣሪዎች፤ የትራፊክ ፖሊስ ተቆጣጣሪዎች ለትራንስፖርት ዘርፉ ዋጋ እየከፈሉ ነው።

በአጠቃላይ በዘርፉ ለተሰማሩ አገልግሎት ሰጭዎች ክብርና ምስጋና ይገባቸዋል። ነገር ግን ጉድለቶችም አሉ። ጉድለቶችን እንዲያርሙ በየጊዜው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ይሠራል። ከዚህ አልፎ ብልሹ አሠራር ውስጥ የሚገባ የቢሮው ሠራተኛ ከማባበር ጀምሮ ጥብቅ ርምጃ ይወሰድበታል።

በከተማ አውቶብስ የሚባረረው ሠራተኛ ከትኬት ቆራጭ እስከ ሹፌር ቀላል አይደለም። ይህም ከአገልግሎት አሰጣጥና ከብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ ማንንም አንታገስም። ያም ሆኖ ግን ያልተደረሰባቸው አሉ። በቀጣይ ከተጠቃሚ በሚመጣው ጥቆማና መረጃ መሠረት እያስተካከልን እንሄዳለን። ለሥራው ውጤታማነት የተገልጋዩ ህብረተሰብ ጥቆማ በመስጠት መተባበር አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ምላሽ እና ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**አቶ ያብባል፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ነፃ ሃሳብ

# የአያቴ «ሰጥተህ» ታዘበኝ ነገር

በመቅደስ ታዬ (ፒ ኤች ዲ)

ተወልጄ ያደኩት አንድ ትንሽ ከተማ ነው:: እናቴ እኔን ስትወልድ ልጅ ስለነበረች የማሳደግ እና የመንከባከብ አቅምም፤ ጊዜም አልነበራትም:: በመሆኑም አያቴ እና ቅድመ አያቴ በስስት እና በወግ ልጅ ከሚያገኘው በላይ ሰው እንድሆን አድርገው አሳደጉኝ:: ያ የልጅነት ጊዜ በሕይወቴ ትልቅ ዋጋ ነበረው እና ሰዎች እስኪገረሙ ብዙ ነገሮችን በደንብ አስታውስበታለሁ:: በደማቁ በልቤ ከተፃፉ እልፍ ጉዳዮች ውስጥ የአያቴ ፀሎት እና ልመና ከነቅደም ተከተሉ ከነፍሰቱ ዛሬም በጆሮዬ ያቃጭልብኛል:: አቤት አያቴ::

ራት በልተን ዕቃውን አሰናድተን ከጨረስን በኋላ ወደ መደባችን እንወጣና የእመዬን ፀሎት ማጣጣም ልምድ ሳይሆን ግዴታ ነበር:: መቁጠሪያዋን እያቃጨለች ኤሎሄ... ኤሎሄ... የአቡነ ዘበሰማያት... ቋሚ ፀሎት ከተጠናቀቀ በኋላ በየቀኑ ከሚገጥሟት ጉዳዮች ላይ መሠረታቸውን ያደረጉ ተማፅኖዎች ይቀርባሉ:: አንድ ቀን ግን ከተለመደው የተለየ ፀሎት ይሁን ትዕዛዝ አሁንም ያልገባኝን ጉዳይ ለፈጣሪዋ አቀረበች:: አምላኬ «ሰጥተህ» ታዘበኝ፤ እባክህ... በቃ «ሰጥተህ» ታዘበኝ:: ዓይኗን ጣሪያው ላይ ሰክታ ወዲያው እንደሚመልስላት ጠየቀችው:: ግን «ሰጥተህ» ታዘበኝ ምን ማለት ነው...

«ሰጥተህ» ታዘበኝ የጎረበጠችኝ ሀረግ ስለነበረች ብዙ ቀን ስጠይቃት እንደነበር አስታውሳለሁ:: አያቴ በጣም አዛኝ ከመሆኗ የተነሳ የተቸገረ ሰው ስታይ ያላትን ሁሉ ትሰጥ ነበር:: አምላክም የእውነት ሊታዘባት ፈልጎ ወይም ልቧ ውስጥ የተሞላው እምነት እና ርግጠኝነት አስደስቶት ባላውቅም ያሻችውን በረከት ሰጣት:: አባቷ ብዙ ሀብት አወረሷት:: አያቴ በማያልቀው ምስጋናዋ ደምቃ የቻለችውን ሁሉ አድርጋ በዙሪያችን የነበሩ ምስኪኖችን ትጋብዝ ነበር:: የተሰጣትን ለትዝብት ሳታስቀር በተግባር አውላ አሳየችኝ::

በነገራችን ላይ አያቴ ሰው እያየት ለሰው በፍፁም ስትሰጥ አይቻት አላውቅም:: የጓሮ በር ከፊት አድርጋ ስጦታ ካስቀመጠች በኋላ በፊት ለፊት በር ገብታ እንደ አዲስ እንግዳ ሰላም ስትላቸው አይቻለሁ:: በዘመኔ ግን ካሜራ ካልተደቀነ ታዛቢ ካልተሰበሰበ ስጦታ አይሰጥም፤ ሲሰጥም ሂደቱ ፍጥነቱን ቀነስ አድርጎ እየተሽኮረመመ ነው ወደ ተቀባዩ የሚሄደው:: እናም አያቴ «ሰጥተህ» ታዘበኝ የምትለው አምላኳ የሚያያት በድብቅ ብቻ ከሆነ ይመስለኝ ነበር:: ግን እኮ ሊሆንም ይችላል:: በአደባባይ እየሰጠን እና እየተቀበልን ይሆን የተሰጠን የማይበረክተው፤ የምንሰጠውስ የምናጣው...።

ዛሬ ላይ «ሰጥተህ» ታዘበኝ ለማለት ብቃቱ፣ ዝግጅቱ፣ ቀናነቱ፣ ቻይነቱ ብዙ ብዙ አስፈላጊ ጉዳዮችን በበኩሌ ስላላሟላሁ ደፍሬ ስጠኝ አልልም:: በድፍረት ጠይቀው ይሁን ወይ እሱ ፈጣሪ እስኪ ሰጥቼ ልታዘባቸው ብሏቸው ምንም ባላውቅም ብዙዎች ሳይሰጣቸው ተሰጠው ሰጪውን ሲያሳዝኑ አያለሁ:: የሰው ልጅ ሲፈጠር በሳይንሱም ሆነ በሃይማኖት ቢመሳከር የማይካደው ነገር ወደዚች ምድር ሲመጣ ለራሱ ብቻ የተሰጠው ልዩ ማንነትና ችሎታ አለው:: ያን ችሎታ በትምህርት፣ በሥራ ወይም በሰዎች እገዛ ማወቅ እና መለየት ሲችል ስኬታማ ሥራ ሰርቶ ውጤት ያሳያል:: ጥሩ ገበሬ መሆን የሚችል ሰው አስተምራለሁ ብሎ ቢሞግት ራሱም አይደሰት ወይም የሚታይ ውጤት አያመጣ እንዲሁ እድሜውን በንጭንጭ እና በምሬት መፍጀት ብቻ ይሆናል::

ኃላፊነት፣ አደራ፣ ሕዝብ ከሁሉም በላይ ሀገር ሥራልኝ ወይም ሥሪልኝ ብሎ ተዘጋጀህም አልተዘጋጀህም እጅህ ላይ ቁጭ ሊል ይችላል:: እነዚህ ጉዳዮች ከራስ ጥቅም እና ፍላጎት በላይ ናቸው እና ከራስህ እንዳስበለጥካቸው እና እንደረጋገጥካቸው ትዝብት ላይ ሊጥሉህ በተግባር ይፈትኑሃል:: ይሄ ቃላዊ ትውልድ ይላሉ አንዳንድ ሰዎች... በቃል አልፈክ በተግባር ዘጭ ስትል ኃላፊነቱን የሰጠህ ፈጣሪ አደራ ያለህ ሕዝብ ከማፈር ጋር ይታዘብሃል::

በእኔ አረዳድ ኃላፊነት ወይም ወንበር እንደ ትምህርት ዝግጅታችን፣ ብቃታችን እና ብሎም አስተዋጽኦ ማሳደር መቻላችን ከሌሎች ሰዋሰዋዊ እይታዎቻችን ጋር ተዳምረው ወደ አገልግሎት መስጫ ወንበር ሊያመሩን ይችላሉ:: አያቴ በልበሙሉነት «ሰጥተህ» ታዘበኝ እንዳለችው እኛም ለወንበሩ ብቁ የሚያደርጉንን መስፈርቶች አሟልተን «ሰጥተህ» ታዘበኝ ካልን ውጤታማነት ከደስተኝነት ጋር እናሳያለን:: አሁን አሁን ላይ ግን በኔ አረዳድ ወንበሩ ከእኛ ብቃት እየበለጠ ባለበት እኳኋን ማስቀጠል አቅቶን ወንበሩን ስንነቀንቅ ከሰው በፊት ወንበሩ እራሱ ስንቴ እንደታዘበን ወንበሩ እራሱ ይታዘበው::

ከላይ ከተጠቀሱት አመክንዮዎች ባንዱ ወይም በሁሉም ምክንያት ወንበር ላይ ተቀምጠው ስንቱን ብልሹ አሠራር እንደ መርህ አፀደቁ አስፀደቁ ብቻ ወንበሩ ይቁጠራቸው:: በኔ አመለካከት መንግሥት የትኛውንም ሥራ እና ኃላፊነት በሕግ ከመደንገግ እና ለክትትል የሚበጅ ፖሊሲ ከማርቀቅ ባሻገር የሚያምንባቸውን ባለወንበሮች አደራ መስጠት እና ማመን ግድ የሚሆንበት ብዙ አጋጣሚ አለ::

ከብዙ የመረጃ ምንጮች እንዳነበብኩት እና በታሪክም በተግባር ከሀገራት ታሪክ እንዳየሁት ብዙ ጊዜ መንግሥት እንደ መርህ የሚያወጣው ሕገ ደንብም ይሁን ፖሊሲ በተቀመጠው ልክ ካልተፈፀመ የሕጉ ወረቀት ላይ መኖር ብቻውን ከመገምገም እና ከመተቸት አያድነውም:: ለዚህም ይመስላል በመንግሥት ሕገ እና ፖሊሲ እምነት እና ቀና አመለካከት የሌላቸው ሰዎች ወደ ወንበሩ የማይጋበዙት:: ችሎታ እና የትምህርት ዝግጅት ከተጠቀሰው ጉዳይ ጋር ተጣምሮ ከተገኘ የተሻለ አሠራር ቢያንስ በሃሳብ ደረጃ ይሳካ ይሆናል::

ሀቅም እና ቀናነት ወይም ሕግን በተገቢው ሁኔታ ለመፈፀም ችሎታ ያነሳቸው አጋጣሚ ወንበሩ የጠራቸው አረሞች መንግሥት እና ሕዝብን ለመነጠል ብሶት እና ጉስቁልናን ለማፋጠን ብቻ በየቢሮው ተሰግስገው ማየት ለእኛ አፍሪካዊያን ብርቅ አይደለም:: በፖለቲካ እና ማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ያሉ ምሁራን በጥናታቸው እንዳስቀመጡት ማህበረሰባዊ ስሪታችን በተለይ የታዳጊ ሀገራት ከኢኮኖሚያዊ ችግሮቻችን ጋር እጅግ የተሰናሰሉ ስለሆኑ አስተዳደጋችን እና አመለካከታችን ከዚህ የድህነት ችግር የምንወጣበትን የተዛባ አመለካከት በባሕል ቅርፅ ይዞ እናገኘዋለን::

ለምሳሌ «ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል....» የሚል የቆየ አባባል አለ:: በዚህ አባባል ስር ሁለት ነጥቦችን መረዳት ይቻላል:: አንደኛው አንድ ሰው ወደሆነ ኃላፊነት ሲመጣ በታማኝነት ከማገልገል ይልቅ የራሱን ጥቅም እና መደላድል ማስተካከል የሚደገፍ ነው የሚል ብልሹ አሠራርን የሚያበረታታ ሃሳብ አለው:: ይሄ ማለት የተሰጠው ኃላፊነት ላይ ሆኖ ግዴታውን ባይወጣ ያን ያህል ወቀሳም ሆነ ቅጣት አያገኘውም ማለት ይሆን የሚል ነጥብም ያስነሳል::

ለምን ቢባል መጠየቅ ቢኖረውማ ኖሮ ከአባባሉ ጋር ተደራቢ የሆነ ማረሚያ አገላለጽ ይኖር ነበር የሚል መከራከሪያ አለ:: ሁለተኛው ጉዳይ አንድ ሰው ወደ ሥልጣን የሚመጣው በሆነ አመክንዮ እንጂ በመክሊት ባለመሆኑ አንዴ ያን ቦታ ካጣሁ ሌላ መግቢያ አጋጣሚ የለውም የሚል ተርጓሜ ያነገበ አገላለጽ አለው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ:: ምክንያቱም ሲሻር ይቆጨዋል ይላልና:: ያም ሆነ ይህ ግን ማህበረሰባዊ ስሪታችን ትርክታችን መሻሻል ይፈልጋል እላለሁ::

እነዚህ ባለወንበሮች ታምኖባቸው አደራው ከብዷቸው የተጣለባቸውን ግዴታ እና ኃላፊነት ለባለቤቱ ማለትም ለሕዝቡ አድርሰዋል..... ወንበርዬ እስኪ ሹክ በለኝ... መንግሥት ሥርዓት ዘርግቶ በዚህ በኩል አድርጋችሁ ሕዝቤን አገልግሉ ብሏቸው አደራውን በተገቢው ሁኔታ አድርሰው ምስጋን የተቸሩ ወንበሩም በኩራት የሚቀበላቸው እፁብ ድንቅ የሀገሬ ልጆች እንዳሉ አውቃለሁ:: ማመስገን የመሰልጠን ምልክት ነው እና ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ አገልግሎት ሰጭ መሥሪያ ቤቶች በአንፃራዊነት መልካም ሊባል የሚችል አሠራር በመተግበር ላይ እንደሆኑ በግሌ አይቻለሁ:: ጥሩ ሲሠራ በማመስገን ለበለጠ ቀልጣፋ አሠራር በር መክፈት ቢለመድ መልካም ነው::

የኔ ትውልድ ካላየሁ አላምንም የሚል ሆኖ ነው ወይስ ድርጊት ከቃል በላይ ይናገራል ስለሚባል፤ ብቻ ተግባር እልፍ ቃላትን እና ትርጓሜዎችን ይይዛል:: እናም በተለይ እኩይ ትግበራዎች ከመልካሞቹ በበለጠ ትኩረት ይስባሉ:: ያም ብቻ አይደለም ሰዎች በተፈጥሮ ይሁን በልምድ በግልጽ አላውቅም አንድ ሰው ከቦታው ከተነሳ ደግም ይሥራ ጥሩ በጅምላ ከማመስገን ይልቅ መኮነን እና ማጣጣል ሲቀናቸው አያለሁ::

በእኔ አስተሳሰብ ግን ሰዎች ባሉበት ሁኔታ ከመታዘባችንም በፊት የሚቃኑበትን መንገድ በመጠቆም የተሰጠው ጊዜ ሳያልፍ እና ሳንተዛዘብ የተሻለ ሥራ እንዲሠሩ ማድረግ ይቻላል:: እዬዬም ሲደላ ነው እንዲሉ አንዳንድ ሰዎች ግን ለራሳቸው ከሚሰጡት የተሳሳተ ግንዛቤ በሚመዘዝ አመክንዮ ካለ እነሱ አዋቂ ካለ እነሱ ሠራተኛ ካለ እነሱ ወሳኝ የለም ብለው ስለሚያምኑ ለወንበሩም ለሰውም ለፈጣሪውም አስተዛዛቢ ሆነው ይታያሉ:: ከላይ እንደጠቀስኩት ማህበረሰባዊ ሥነ ልቦናችን እና አወቃቀራችን በተለይ በተነሳው ጉዳይ ላይ ትንሽ ማስተካከያ ያስፈልገዋል የሚል እምነት አለኝ:: አንድ ግለሰብ ሕዝብን እንዲያገለግል አደራ ሲቀበል ተጠያቂነቱ ለሚያገለግለው ሕዝብ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ራሱን ማዘጋጀት፤ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠር ይጠበቅበታል ባይ ነኝ::

> **አንድ ግለሰብ ሕዝብን እንዲያገለግል አደራ ሲቀበል ተጠያቂነቱ ለሚያገለግለው ሕዝብ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ራሱን ማዘጋጀት፤ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠር ይጠበቅበታል ባይ ነኝ**

ከዚህ አኳያ በአብዛኛው በታዳጊ ሀገራት እንደሚታየው ወንበር ትርጓሜው የተዛባ በመሆኑ ሥራውም ውጤቱም እንደ እሳቤው የተዛባ ነው:: ከላይ በቀረበው ማህበራዊ ስሪት እና ትርክት ያደገን ዜጋ ከተረቱ ለማሻገር ማገዶ መፍጀቱ ቢታወቅም በሥልጣኑ ከምንተዛዘብ የፈጀውን ማገዶ ይፍጅ ከሚሉት ጎን ብቆም ይሻለኛል:: በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚወጡ ሕጎች፣ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች እና የተለያዩ ማሻሻያዎች የማህበረሰቡን ህልውና እና ቀጣይ እጣ ፋንታ የሚያሳልጡ በብዙ ወጪ እና ልፋት የሚዘጋጁ እንደሆነ ይታወቃል::

ነገር ግን እነዚህ የተደከመባቸው ረቂቆች ሕዝቡም በጉጉት እየጠበቃቸው መንግሥትም የሚገባወን የማጽደቅ ሥራ ሰርቶባቸው አሻጋሪ በትር ወይም ፈፃሚ አካላት ከሀቅም ወይም ከቀናነት ወይም ደግሞ የተለየ አጀንዳ ከማራገብ አንፃር መሰናከል ሲሆኑ እታዘባለሁ:: እነዚህ አካላት ከሥራ ይልቅ በሴራ የተካኑ በመሆናቸው የሚያስጨንቃቸው የራሳቸው መውጫ መንገድ እንጂ የሥራቸው ውጤታማነት ባለመሆኑ ብዙ ጊዜ ተጠያቂ ሳይሆኑ አበላሽተው እና ዘርፈው ሲሾልኩ እናውቃለን:: ይሄ ከሁሉም የከፋ ምሳሌ በመሆን ትውልዱንም የሚበርዝ እጅግ ጥንቃቄ የሚፈልግ ጉዳይ ነው:: ይሄ ምልክትን የሚሻ ትውልድ ሲዘርፍ፣ ሲበድል፣ ሲያጎድል ያየውን ባለወንበር በነፃነት ሲፈነጭ ካየው በየትኛው አመክንዮ ይሄን ትውልድ አንተ መልካም እና ታማኝ አገልጋይ ሁን ብለን ልንቀርጸው እንችላለን...

ፍየል ወዲያ ... የሚለው እሳቤ ብዙ ጊዜ ለባለወንበሮች የሚሠራ ይመስለኛል:: ፍፁም የማይመጥኑ ሕዝብ እና መንግሥትን ሆድ እና ጀርባ እንዲሆን የሚያደርጉ አሉ:: የአገልጋይነት ትርጉም ገብቷችሁ በተግባር ተገልጣችሁ ዋጋ እየከፈላችሁ ያላችሁ ባለወንበሮች ከምሥጋና ባለፈ ትውልዱን በሥራችሁ እየሰበካችሁ ለጠንካራ እና ሀቀኛ አሠራር እያዘጋጃችሁ ስለሆነ በመልካም ታዝቤያለሁ::

«ሰጥተህ» ታዘበኝ.... የሚሉ እልፍ ችሎታዎች ያሉበት ቦታ ሆነው ሲያንፀባርቁ ውጤት እና መልካም ከባቢ ይፈጠራል:: ይህም ከፍ ሲል የተደሰተ እና ነገን በተስፋ የሚቀርጽ ትውልድ እና ማህበረሰብ እየተገነባ ሀገርም እያደገ ይመጣል:: «ሰጥተህ» ታዘበኝ ብሎ በድፍረት ለመጠየቅ ግን ራስን መመርመር እና መገምገም ይጠይቃል:: ሲሾምም ሲወርድም ትችቱም ሆነ ምስጋናው ለራሱ ለግለሰቡ ነው እና::

# ንግድና ግብይት

# የምሽት ግብይትን - ለመዲናዋ ኢኮኖሚ መነቃቃት

- *የንግድ ፈቃዳቸውን ላላደሱ የንግድ ተቋማት ማሳሰቢያ ተሰጥቷል*

**በኃይሉ አበራ**



ያደጉት ሀገራት እና የአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ከተሞች የንግድ ተቋማት ግብይት ቀን ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ በምሽት ጭምር ይገበያያሉ:: በዚህም የንግድ ተቋማቱንና በምሽት ጭምር መገበያየት የሚፈልገው የህብረተሰብ ክፍል የሚገበያዩበትን እድል በማስፋት ሁለቱም ወገኖች ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ በአጠቃላይ ግብይቱ እንዲኅለብት የከተሞችም የሀገሮችም ኢኮኖሚ ይበልጥ እንዲነቃቃ ለማድረግ ያስችላል::

በአዲስ አበባ ይህ ግብይት አለ በሚባል ደረጃ ላይ አይገኝም:: በአንዳንድ የከተማዋ አካባቢዎች ከሚስተዋል የምሽት ግብይት ውጭ፣ ትልቁን የአፍሪካ ገበያ መርካቶን ጨምሮ የአብዛኛዎቹ አካባቢዎች ነጋዴዎች ገና ጀንበር ስታዘቀዝቅ መደብሮቻቸውን ዘግተው ወደየቤታቸው ያቀናሉ።

በከተማዋ መሀል አካባቢዎች እስከ ምሽት በመገበያየቱ ልምድ ያካበቱ የንግድ ተቋማት የግብይቱን ፋይዳ ተገንዝበው ተጠቃሚ ሲሆኑ ቢቆዩም፣ ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህ ግን የንግድ ተቋማቱም ሆኑ በምሽት የሚገበያየው ማህበረሰብ በጊዜ ወደቤቱ ሲገባ ይስተዋላል። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ሲቀርቡ ይደመጣል። የመንገድ መብራት አለመኖር፣ የትራንስፖርት አገልግሎቱ የምሽት ዋጋ ከፍተኛ መሆን፣ በዚህ የተነሳም ተገቢውን አገልግሎት እንደልብ ማግኘት አለመቻል፣ የሸገር እና አንበሳ አውቶቡሶችም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በኋላ የማይሠሩ መሆናቸው ከምክንያቶቹ መካከል ይጠቀሳሉ።

አሁን መዲናዋ የኮሪደር ልማት በተከናወነባቸው አካባቢዎች ምሽቱ ቀን እስኪሚመስል ድረስ የንግድ ሥራዎችን ጨምሮ ለየትኛውም እንቅስቃሴ አመቺ ሆናለች። ከጸጥታም፣ ከመንገድ መብራትና ከመሳሰሉት መሠረተ ልማቶች አኳያ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፤ ይሁንና ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ በርካታ የንግድ ተቋማት በመነሳታቸው በዚህ ምቹ በሆነው መሠረተ ልማት አካባቢ ያለው የንግድ እንቅስቃሴ እምብዛም ሆኖ ይታያል።

የከተማ አስተዳደሩም በቅርቡ ይህንን ሁኔታ ለመቀየር እና የመዲናዋን የንግድ እንቅስቃሴና ኢኮኖሚ ለማነቃቃት ይረዳል ያለውን ውሳኔ አሳልፏል። የንግድ ተቋማት እስከ ምሽት ሶስት ሰዓት ተኩል እንዲሁም የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ጨምሮ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች እስከ ምሽት አራት ሰዓት እንዲያገለግሉ ወስኗል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ እንደተናገሩት፤ ባለፈው ሳምንት የከተማዋ የንግድ ተቋማት እስከ ምሽት ድረስ መሥራት ባለባቸው ሁኔታ እንዲሁም በንግድ ፍቃድ ምዝገባና አሰጣጥ ላይ ያለውን አሠራር አስመልክተው ለብዙኃን መገናኛ መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንዳሉት፤ ከአፍሪካ ሀገራት እንደ ኬንያ፣ ሞሮኮ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ የመሳሰሉት ሀገራት አብዛኛውን ግብይታቸውን በምሽት ያካሂዳሉ። ይህን ዓይነት የንግድ ግብይት በአዲስ አበባም ተግባራዊ ማድረግ ይገባል:: የብዙኃን መገናኛዎቹም በዚህ ላይ ግንዛቤ በማስጨበጥ በኩል መሥራት ይኖርባቸዋል::

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ሁለት የትኩረት መስኮች ላይ ይሠራል ያሉት ኃላፊዋ፣ በአንደኛው የትኩረት መስኩ የከተማው ነዋሪ በኑሮ ውድነት የሚደርስበትን ጫና ለማቃለል የተሳለጠ የንግድ ሥርዓት እንዲኖር አቅርቦትንና ፍላጎትን በማጣጣም ጤናማ የሆነ የንግድ ሥርዓት መፍጠር ላይ የሚሠራው ነው ብለዋል።

በሁለተኛው የትኩረት መስኩ ደግሞ የንግድ ሕጎቹን ተግባራዊ ለማድረግ በቁጥጥር ዘርፉ ላይ አተኩሮ እንደሚሠራ አስገንዝበዋል። ማንኛውም የንግድ ተቋም እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ተኩል አገልግሎት እንዲሰጥ፣ በተመሳሳይም የትራንስፖርት ዘርፉ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት እንዲያገለግል በከተማ አስተዳደሩ መወሰኑን አስታውቀዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ያሳለፈው ውሳኔ የንግዱ ማህበረሰብ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን እንዲያሳድግ የሚያደርግ፣ የማህበረሰቡንም ሆነ ከተማውን ኢኮኖሚ የሚያነቃቃ መሆኑን አብራርተው፣ የንግዱ ማህበረሰብም በዚህ ላይ ግንዛቤ ወስዶ የትኛውንም የንግድ ተቋም እስከ ምሽት ሶስት ሰዓት ተኩል ድርጅቱን ክፍት ሆኖ እንዲሠራ ጥሪ አስተላልፈዋል።

መዲናዋ የከተማ አስተዳደሩ የኮሪደር ልማት በፈጠራቸው ምቹ ሁኔታዎች ሰላሟ የተጠበቀ ከተማ ሆናለች ሲሉም ጠቅሰው፣ ይሁንና እነዚህ ሁሉ ሥራዎች ተከናውነው ከ12 ሰዓት ጀምሮ በርካታ የንግድ ተቋማት በከተማዋ ተዘግተው እንደሚታዩ አስታውቀዋል። ይህ ሁኔታ መቀየር እንዳለበት አስገንዝበው፣ የንግዱ ማህበረሰብ የንግድ ተቋማቱን ክፍት በማድረግ የግብይት ሥራው እንዲቀጥል ማድረግ እንዳለበት ገልጸዋል:: የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮም በዚህ ላይ ክትትል በማድረግ፣ ለተፈጻሚነቱ ድጋፍ ለማድረግ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

የቢሮ ኃላፊዋ የንግድ ፈቃዳቸው ያላሳደሱ የንግድ ማህበረሰቡ አባላት እስከ ታኅሣሥ 30 ድረስ የንግድ ፍቃዳቸውን እንዲያሳድሱም ጥሪ አቅርበዋል:: በከተማዋ የንግድ ፍቃድ ምዝገባና አሰጣጥ በወረዳና በክፍለ ከተማ ደረጃ ይሰጥ እንደነበረ ጠቅሰው፣ ከተማ አስተዳደሩ በዚህ ላይ ማሻሻያ ማድረጉን አመልክተዋል:: የንግድ ፈቃድ በኦንላይን እየተሰጠ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከሐምሌ 1 ቀን 2016 ጀምሮ በቢሮ ደረጃ አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል ብለዋል።

ይህ አገልግሎት ሲሰጥም በአምስት ወር የተገኘው ውጤት እና ማሻሻል በሚገባው ላይም ማብራሪያ ሰጥተዋል:: እንደ ወይዘሮ ሀቢባ ገለጻ፤ ከሐምሌ 1 ጀምሮ ወደ 47 ሺህ 707 ያህል ነጋዴዎች አዲስ የንግድ ፍቃድ አውጥተዋል። ይህም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር አገልግሎቱ በማዕከል መስጠት ከጀመረ ወዲህ የ10 በመቶ ብልጫ አሳይቷል። በተመሳሳይ ወደ 15 ሺህ 99 የሚሆኑ ነጋዴዎች ከንግድ ሥርዓቱ ወጥተዋል። ይህም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ከንግድ ፍቃድ የወጡት 17 በመቶ ያህል ቅናሽ ያሳየ ነው። ከንግድ ሥርዓቱ የሚወጣው ነጋዴ እየቀነሰ ወደ ንግድ ሥርዓቱ የሚመጣው መጨመሩን የአምስት ወር ዳታ ያመላክታል።

ኃላፊዋ እንደተናገሩት፤ ከሐምሌ 1 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ 30 ቀን 2017 ዓ.ም የንግድ ፍቃድ የሚታደስበት ወቅት ሲሆን፣ ባለፉት አምስት ወራት 211 ሺህ 720 ያህል ነጋዴዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው ንግድ ፍቃዳቸውን አድሰዋል። የንግድ ፍቃድ የማደሻው ቀን ሊጠናቀቅ ሁለት ሳምንት ብቻ ይቀሩታል:: እስከ አሁን የንግድ ፍቃዳቸውን ያላደሱ 184 ሺህ ያህል ነጋዴዎች አሉ:: እነዚህ ነጋዴዎች በተቀሩት ቀናት ማደስ ይጠበቅባቸዋል::

ቢሮው የንግዱ ማህበረሰብ ለቅጣት እንዳይዳረግ እድሳቱ እንዲካሄድ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮ እየጠበቀ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከእነዚህም አንዱ የሥራ ሰዓቱን ማራዘም መሆኑን ጠቁመዋል:: ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል እስከ ምሽት አንድ ሰዓት ድረስ የንግዱ ማህበረሰብ ፈቃዱን እንዲያድስ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን አመልክተዋል::

መገናኛ ብዙኃን ለኃላፊዋ ጥያቄዎችን አንስተዋል:: ከጥያቄዎቹ መካከል የንግድ ፍቃድ እድሳቱ ሊጠናቀቅ ጥቂት ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለምን ተጠበቀ? አስቀድሞ ማሳሰብ አይቻልም ነበር ወይ? የሚል ጥያቄ አንስተዋል:: ኃላፊዋ ለጥያቄዎቹ ምላሽ በሰጡበት ወቅት እንዳስታወቁትም፤ የንግዱ ማህበረሰብ ንግድ ፍቃዱን በወቅቱ እንዲያድስ በክፍለ ከተማ ደረጃ ቅስቀሳ ሲደረግ ቆይቷል። በዘርፉ በቢሮው የማህበራዊ መገናኛ ገፁ ላይም በየጊዜው መልዕክት ተላልፏል። እነዚህ 184 ሺህ የሚሆኑት ቀንም ማታም በየትኛውም ሰዓት በኦንላይን ማመልከቻ ቢያቀርቡ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ተቀብሎ ለማስተናገድ ዝግጁ ነው።

የቢሮ ኃላፊዋ የንግድ ተቋማት የሥራ ሰዓት ማራዘምን በተመለከተ ከፀጥታ፣ ከትራንስፖርት አገልግሎት ጋር ተያይዞ ከብዙኃን መገናኛ ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል። በምላሻቸውም የንግድ ተቋማት የሥራ ሰዓት በከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ሲወሰን ደንቦች፣ የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ባሉበት መሆኑን ገልጸዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በዚህም የሥራ ድርሻ ክፍፍል ተደርጓል። በዋናነትም የኮሪደር ልማቱ በለማባቸው ዋና ዋና ጎዳናዎች እነዚህ የንግድ ተቋማት እስከ ምሽት ሶስት ሰዓት ከሰላሳ ክፍት ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ መወሰኑን አስገንዝበዋል። የንግድ ተቋማቱ በተባሉት ሰዓቶች ክፍት ሆነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው ጠቅሰው፣ በዚህም ላይ ክትትልና ድጋፍ እንደሚደረጉ አመላክተዋል።

ወይዘሮ ሀቢባ እንዳስገነዘቡት፤ የንግድ ተቋማቱም ይሄንን እንደሚፈልጉት ቢሮው ይገነዘበዋል። ውሳኔው የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያሳድግ፣ የንግድ እንቅስቃሴውንም የሚጨመር ነው።

በታክሲ አገልግሎት ሰዓት ላይ ለተነሳው ጥያቄም አያይዘው በሰጡት ምላሽ አጠቃላይ የከተማ አውቶቡስን የሚመራው አካል እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት አገልግሎት እንዲሰጥ መወሰኑን አመልክተው፣ ከተማ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ማንኛቸውም የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችም እንዲሁ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

እነዚህን የትራንስፖርት አገልግሎቶች በእነዚህ ሰዓቶች እንዲሠሩ ማድረግ ካልተቻለ ይህ ሁሉ መሠረተ ልማት ተዘርግቶ፣ ከተማውም ውብ ሆና፣ ማህበረሰባችን ከምሽቱ 12 ሰዓት ወደቤቱ የሚገባ ከሆነ ከተሜነቱም አጠያያቂ ይሆናል ሲሉም አስታውቀዋል:: የብዙኃን መገናኛውም በዚህ ላይ ግንዛቤ እንዲሰጥ አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ነጋዴው አምሽቶ ሲሠራ፣ ነዋሪውም በዚያ ምሽት ሰዓት ወጥቶ ሲገበያይ የከተማዋንም ውበት እንዲያይ፣ እንዲንሸራሸር ኢኮኖሚውንም እንዲያሳድግ ይፈለጋል። መንግሥት በበኩሉ ለከተማዋ ደህንነት እና ሰላም መጠበቅ ኃላፊነቱን ወስዶ እየሠራ ይገኛል፤ ሕዝቡን ለመጠበቅ፣ ነጋዴውን ማህበረሰብ ለመጠበቅ ኃላፊነቱን ይወስዳል።

በኮሪደር ልማቱ የንግድ ተቋማት የሚሠሩባቸው ህንጻዎችና መደብሮች ሲፈርሱ ምርጫቸው ተጠብቋል ያሉት ኃላፊዋ፣ በተለይ የመንግሥት ቤት ወይም የቀበሌ ቤት ውስጥ ሲሠሩ የነበሩ ሰዎች አማራጭ እንደተጠበቀላቸው አስታውቀዋል። ከተማ ውስጥ መሥራት የሚፈልጉ በሚፈልጉት መንገድ ተደራጅተው ቦታ እየተሰጣቸው እንደሚገኝ ገልጸው፣ ከካዛንቺስ የተነሱ የንግድ ተቋማት ወደ ገላን ጉራ ሄደው እንዲሠሩ የተደረገበት ሁኔታ እንዳለም አመልክተዋል።

ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ 15 ሺህ 99 ሰዎች ከንግድ ሥርዓቱ መውጣታቸውንም ጠቅሰው፣ ይሄንንም ኦንላይን ላይ በሚደረገው ምዝገባ ያመለከቱ፣ ከንግድ ፍቃድ የወጡ፣ አዲስ የንግድ ፍቃድ ያወጡ እንደሚታዩ ተናግረዋል፤ ይህን ለማወቅ ተጨማሪ ጥናት ማድረግ እንደማይፈልግ ጠቁመዋል።

መደበኛ ያልሆነ ንግድን በተመለከተ ሲያብራሩ እንደገለፁት፤ በመዲናዋ እንደ ሌባና ፖሊስ ጨዋታ ከደንብ ማስከበር ጋር ሲሯሯጡ የሚውሉ ዜጎች አሉ። ይህንን ሥርዓት ለማስያዝ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ የኢመደበኛ ንግድ ደንብ ወጥቷል።

ደንቡ በቅርብ ቀን ለካቢኔ ቀርቦ ይጸድቃል። ከፀደቀ በኋላም ሥርዓት ባለው መንገድ የንግድ እንቅስቃሴው እንዲከናወን ይደረጋል።

እስካሁን ቢሮው ባለው ዳታ በኢመደበኛ ተመዝግበው ያሉት ወደ 4ሺ800 አካባቢ ናቸው:: ከዚያም ውጭ ነጋዴዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ሁሉንም መልክ በማስያዝ እንደ ማንኛውም ዜጋ ሰዓታቸው ተገድቦ፣ የሚሠሩበት የሥራ ቦታ ተወስኖ የንግድ ፍቃድና መታወቂያ ተሰጥቷቸው፣ የሚሠሩበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ጠቁመዋል:: በዚህ ላይ የሚሠራ የሥራ ክፍል መዋቀሩንም ጠቁመዋል።

በኮሪደር ልማቱ ከፈረሱ የነዳጅ ማደያዎች ጋር ተያይዞም በብዙኃን መገናኛዎቹ ጥያቄ ተነስቷል፤ የቢሮ ኃላፊዋ ለእዚህ በሰጡት ምላሽ እንዳብራሩት፤ በመዲናዋ ካሉት ጠቅላላ 126 አካባቢ ማደያዎች ሰባት ያህሉ በኮሪደር ምክንያት ተነስተዋል። እነዚህን ለመተካት እየተሠራ ነው። ባለሀብቶቹ በጠየቁት ልክ ሚዲያዎችን ለመተካት ይሠራል።

በሌላ በኩልም የንግድ ቢሮውም ሆነ የከተማ አስተዳደሩ አቅጣጫ ነዳጅ ማደያ ማስፋፋት ላይ ሳይሆን ታዳሽ ኃይል የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎችን ማበረታታት ላይ መሥራት መሆኑን አስታውቀዋል:: በከተማዋ በጥናት በተረጋገጠው መሠረት 260 አካባቢ ነዳጅ ማደያዎች ያስፈልጋሉ ሲሉም ገልጸው፣ አሁን በመንግሥት ፖሊሲ በብዛት ለማስገባት እየታሰበ ያለው የኤሌክትሪክ መኪናዎችን መሆኑን ገልጸዋል:: ለዚህም ከተማዋ የኤሌክትሪክ ቻርጅ ማድረጊያ ቦታዎችን በብዛት ማመቻቸት ላይ አተኩራ እንደምትሠራ አመልክተዋል::

**ከአፍሪካ ሀገራት እንደ ኬንያ፣ ሞሮኮ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ የመሳሰሉት ሀገራት አብዛኛውን ግብይታቸውን በምሽት ያካሂዳሉ። ይህን ዓይነት የንግድ ግብይት በአዲስ አበባም ተግባራዊ ማድረግ ይገባል**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የሐኪም ውለታ

**ዋስልኝ አየለ**

ከሁለት ሳምንታት በፊት (ታኅሳስ 2 ቀን) «ወደ ሕክምና ተቋም መሄድ ለምን እንፈራለን?» በሚል ርዕስ በሕክምና ተቋሞቻችን ውስጥ ያለውን አሰልቺ እና ተስፋ አስቆራጭ፣ ይባስ ብሎም ለሌላ ህመም የሚዳርግ ወከባ መኖሩን በትዝብት ዓምዳችን አይተናል።በዚህ ሁሉ ውስጥ ያለውን የሐኪሞች ውለታ ራሱን በቻለ ክፍል እንደምናየው በገለጽነው መሠረት እነሆ ዛሬ ደግሞ የሐኪሞችን ውለታ እናያለን።

የሰው ልጅ ከፈጣሪ ቀጥሎ የሚተማመነው በሐኪም ይመስለኛል፤ ከፈጣሪ ቀጥሎ ሕይወቱን አደራ የሚሰጠው ለሐኪም ነው።ፈጣሪ የፈጠረው ፍጡር መላ ገመናውን የሚያሳየው ለሐኪም ነው።ከሐኪም የሚደበቅ ነገር የለም።

የሐኪሞችን የሕይወት ውለታ እንዳስታውስ የሚያደርጉኝ ወደ ሆስፒታል ጎራ የምልባቸው አጋጣሚዎች ናቸው።ከወር በፊት ደግሞ ሆስፒታል ውስጥ በመዋል እና በማደር ሰፋ ባለ ሁኔታ ለማስተዋል ችያለሁ።ምንም እንኳን የሙያቸው ባህሪ ግልጽ እና ተገማች ቢሆንም፤ ማየት ደግሞ የበለጠ በሁኔታዎች ለመገረም ያስገድዳል፡፡

የሕክምና ሥራ እንጀራ ነው ከማለት ይልቅ በጎ አድራጎት ወይም ለሰዎች ውለታ የመዋል የህሊና ሥራ ነው ማለት ይሻላል።ምክንያቱም እንደኔ አይነቱ ሰነፍ «እንዲህ ሆኜ ከፍተኛ ደሞዝ ከማገኝ ለምን የቀን ሥራ እየሠራሁ አልኖርም!» ሊል ይችላል።ሥራው የሙያ ሥራ ብቻ ሳይሆን የህሊና፣ የትዕግስት፣ የአስተዋይነትና የምሉዕነት ሥራ ነው።ከሕክምና ሙያ የተረዳሁት ነገር፤ የተዋጣለት ስፔሻሊስት ሐኪም የሚያደርገውን ቴክኒካል ሙያ መቻል ብቻውን በቂ አለመሆኑን ነው።ሐኪሞች የሞት አፋፍ የደረሰን ሰው ከማዳናቸው በላይ የሚገርመኝ የሚጠቀሙት አዕምሯዊ ጥበብ ነው።አዕምሯዊ ጥበብ ደግሞ የሰውነት ከፍታ መለያ ነው፡፡

የህክምና ሙያን ከሌላው ሙያ ጋር አነፃፀሩት።የሚያስተናግዱት ታማሚ ሰው ነው።የታመመ ሰው ደግሞ የሚኖሩትን ባህሪያት መገመት ቀላል ነው።በራሳችንም፣ በዙሪያችን ባሉ ሰዎችም የምናየው ነገር ነው።እንደ ህመሙ ሁኔታ ቢለያይም የታመመ ሰው ነጭናጫ እና ቁጡ መሆኑ የሚጠበቅ ነው።በትንሽ ትልቁ ሆድ የሚብሰው እና ተስፋ ቆራጭ የሚሆን ያጋጥማል።እንደ ሌላው አገልግሎት በመደበኛ ኮምኒኬሽን ሳይሆን በልዩ ጥንቃቄ እና ታጋሽነት የሚያዝ ነው።ሐኪሞች ይሄን ነው በጥበብ የሚወጡት፡፡

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ሲሆን ደግሞ አስቡት! ሰዎች ወደ ሕክምና ተቋም የሚሄዱት ህመሙ አደገኛ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ ነው።ለሕይወት አስጊ ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው።በዚያ ላይ ደግሞ የተማረ የሚባለው የህብረተሰብ ክፍል ሳይቀር ባህላዊ መድኃኒቶችን እና ሌሎች ልማዳዊ ነገሮችን ይጠቀማል።ከእነዚህ ሁሉ ነገሮች አልፎ ህመሙ አደገኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው ወደ ሕክምና ተቋም የሚሄደው።በዚህን ጊዜ ለሐኪሞች ሌላ ፈተና ይሆናል ማለት ነው።

አንደኛው ችግር፤ ህመሙ ገና ሳይጠነክር አለመሄዱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ችግር ደግሞ በልማዳዊ መንገድ የተሞከረው መድኃኒት ሌላ ጣጣ ይዞ ሊመጣ ይችላል።ሁለቱም ችግሮች ሕክምናውን አስቸጋሪ ሊያደርጉት ይችላሉ።በልማዳዊ መንገድ የተሞከረው መድኃኒት ምናልባትም የጀመሪያውን ህመም ወደ ሌላ ደረጃ ሊወስደው ይችላል።

እርግጥ ነው የባህል መድኃኒቶች የዘመናዊው መድኃኒት መቀመሚያ ግብዓቶች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ፈውሰው የሚያውቁም ይኖራሉ።ችግሩ ግን አስተማማኝ አይደለም፤ የሚዘጋጀው በልማዳዊ መንገድ ነው።ብዙ ቤተ ሙከራ አልፎ የተረጋገጠ አይደለም።

በነገራችን ላይ የሕክምና ባለሙያዎች እንደሚሉት፤ አንድ መድኃኒት ሙሉ ሂደቱን ጨርሶ፣ በዓለም ጤና ድርጅት ተረጋግጦ፣ በመድኃኒት መልክ መሰጠት እስከሚጀምር ቢያንስ እስከ 7 ዓመት ሊወስድ ይችላል።ለእኛ ሩቅ በሆነ በብዙ አይነት መንገድ ሲጠና እና ሲረጋገጥ ነው የሚቆየው።ዋናው መድኃኒት በዚህ ሁኔታ የሚዘጋጅ ከሆነ፤ ከጓሮ በተቀጠፈ ቅጠላቅጠልና ሥራሥር እርግጠኛ መሆን አደገኛ ሊሆን ይችላል።

ህመሙ እንደጀመረ ወደ ሕክምና ተቋም ባለመሄድ፣ ወይም በልማዳዊ መንገድ በተሞከረ መድኃኒት ህመሙ አደገኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ የመጨረሻው አማራጭ ሐኪም ቤት መሄድ ነውና ታማሚው በሰዎች እገዛ ይሄዳል።ይህኔ ሕመሙ ብዙ ሒደት የሚጠይቅ ይሆናል።በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው እንግዲህ የሐኪሞች ሥራ አስቸጋሪና ውስብስብ የሚሆንባቸው ማለት ነው።ታማሚው ለሕይወት አስጊ ሁኔታ ላይ ስለሚሆን የቤተሰብ ጭንቀት፣ ባስ ሲልም ለቅሶ እና ጩኸት ይኖራል።ይህኔ ሐኪሞች ሥራቸውን ለመሥራት ይቸገራሉ።እርግጥ ነው ህመሙ ሲብስ አስታማሚ እንዳይገባ ይደረጋል።ሆኖም ግን ቤተሰብ ናቸውና ጋዎን የለበሰ ሐኪም ባዩ ቁጥር እግሩ ላይ እየወደቁ ማልቀስና መጮህ የተለመደ ነው።

አንዲት እናት ልጇ ሊሞት ፃር ላይ እያለ «ዝም በይ!» ብትባል የማይሆን ነገር ነው።አንድ ሰው እናቱ ወይም አባቱ ሊሞቱ እያጣጣሩ «ዝም በል!» ቢባል የማይሆን ነገር ነው።ታማሚው ያለበት ክፍል አካባቢው ለቅሶ በለቅሶ ይሆናል።አንዳንዶቹ ሐኪሞችን እንደ ፈጣሪ በማየት የተማጽኖ ድምጽ ያሰማሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ሐኪሞችን በመሳደብ እና በመራገም «ትገሉብኛላችሁ!» ወይም ደግሞ «እናንተ ናችሁ እንደዚህ ያደረጋችሁት!» በሚል ያዙኝ ልቀቁኝ ይላሉ።ያው እንግዲህ ጭንቅ ነውና ምንም ሊሉ ይችላሉ፡፡

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ሐኪሞች ሁሉንም ነገር ለምደውታልና ቀጥ ብለው ሥራቸውን ነው የሚሠሩት።በተሳዳቢዎች ግንዛቤ ልክ ወርደው አይሰዳደቡም፤ ደረጃቸውንና የሙያቸውን ክብርነት ያውቃሉ።ጥድፊያቸው የማዳን ሥራው ላይ እንጂ ተሳዳቢዎች ላይ አይደለም።

ሌላው ከሐኪሞች ጥበብ ቀልቤን ገዝቶት የነበረው ታማሚን የሚጠይቁበት እና የሚንከባከቡበት መንገድ ነው።እዚህ ላይ መደበኛው የሐኪምነት ሥራቸው ብቻ ሳይሆን ሰዋዊ ሥብዕናቸውም ይታያል።ማታ ፈረቃ ሲቀያየሩ ቀን በሙያ ልብሱ (ጋዎን) ያየነው ሐኪም ማታ ሌላ ልብስ ለብሶ (ሊወጣ ሲል ማለት ነው) በየአልጋ ክፍሉ እየዞረ ይጠይቃል።እዚህ ላይ የሚጠይቀው በሁለት ነገር ይመስለኛል።አንደኛ፤ እንደ ሰው «ፈጣሪ ይማራችሁ» ለማለት፤ ሁለተኛ፤ እንደ ሙያ ሲሠራው የዋለውን ሁኔታ አይቶ መሄድ ስላለበት፣ ደህና ሆነው ሲያይ የሚሰማው የህሊና እርካታ ስለሚኖረው ነው።ምናልባትም ማታ ስትወጡ መጠየቅ አለባችሁ ከተባሉም፤ የሙያ ታማኝነትንና የህሊና ተገዥነትን ያሳያል።

በሥራ ላይ እያሉ የሚሰጣቸው አልጋ (ታማሚ) ይኖራል።የሚጠይቁት ግን ክፍሉ ውስጥ ያለውን ሁሉንም ታማሚ ነው (ምናልባት የሙያው ባህሪ ሊሆን ይችላል)።ሲጠይቁ ታዲያ በማሳሳቅ እና በመቀለድ ጭምር ነው።ሥነ ልቦናዊ ጥበብ ያልኩት ይህንን ነው።እንኳን የታማሚውን የአስታማሚውን እንኳን ቀልብ ያረጋጋሉ።ታሞ የተኛ ቤተሰቡን ወይም ጓደኛ የሚያስታምም ሰው የሚኖረውን ጭንቀት ማንም መገመት የሚችለው ነው።ሐኪሞች እየዞሩ ሲጠይቁ፤ ታማሚውን እየቀለዱ፣ አንዳንድ ቀለል ቀለል ያሉ ሰዋዊ የሆኑ ነገሮችን እየጠየቁ... ታማሚውንም አስታማሚውንም ያረጋጋሉ።

ያም ሆኖ ግን ቁጡ እና ነጭናጫ የሚሆኑ ፈፅሞ የሉም ማለት አይደለም።ማየት ያለብን ግን ጥቂቶችን ሳይሆን ብዙዎችን ነውና የሐኪሞችን ውለታ እናስብ! የሐኪሞችን ውለታ የምናስበው ደግሞ ሕመም ሳይጠነክር እና ከቁጥጥር ውጭ ሳይሆን በመሄድ መሆን አለበት!

# ዓለም አቀፍ

## እስራኤል የሐማሱ መሪ ኢስማኢል ሀኒዬን መግደሏን አመነች

የእስራኤል መከላከያ ሚኒስትር የሐማስ የፖለቲካ ክንፍ መሪ ኢስማኢል ሀኒዬ ባለፈው ሐምሌ ቴህራን ውስጥ በእስራኤል መገደላቸውን አመኑ። ሚኒስትሩ እስራኤል ካትዝ በኢራን የሚደገፉ የሁቲ መሪዎችን ዒላማ እንደሚያደርጉ በሰጡት መግለጫ ወቅት ነው ይህን ያሉት። ሀኒዬ በኢራን መዲና ቴህራን በሚገኝ መኖሪያ ቤታቸው ሳሉ ነው የተገደሉት። እስራኤል ግድያውን መፈፀሟን ባታምንም ብዙዎች ግን ከጥቃቱ ጀርባ እጇ አለበት ሲሉ ቆይተዋል።

የሁቲ አማፂያን እስራኤል ላይ የድሮን እና የሚሳዔል ጥቃት እያደረሱ ይገኛሉ። እስራኤል የሁቲ አማፂያን ላይ "ከፍተኛ ርምጃ" ትወስዳለች፤ የቡድኑ መሪዎችን ጭንቅላት "ትቀላለች" ሲሉ ካትዝ ተናግረዋል።"ልክ ሀኒዬን እንዳደረግነው፣ [ያህያ] ሲንዋርን፣ እና [ሐሰን] ናስራላሕን በቴህራን፣ ጋዛ እና ሊባኖስ እንዳደረግነው በተመሳሳይ በሆዴይዳ እና ሰንዓ እናደርጋለን" ብለዋል።

የ62 ዓመቱ ሀኒዬ በሐማስ እንቅስቃሴ ትልቅ ቦታ ያላቸውን በጋዛ ሰርጥ የተኩስ አቁም እንዲደረግ ብዙ የጣሩ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል። ሀኒዬ ከተገደሉ በኋላ ሐማስ ያህያ ሲንዋርን በጋዛ የቡድኑ መሪ አድርጎ መረጠ። ሲንዋር ሐማስ በአውሮፓውያኑ ጥቅምት 7/2023 እስራኤል ላይ ያደረሰውን ጥቃት ካቀነባበሩ ሰዎች መካከል አንዱ ናቸው።

ሲንዋር ባለፈው ጥቅምት 2024 እስራኤል ጋዛ ላይ ባደረሰችው ጥቃት መገደሉ ይታወሳል። ቡድኑ እስካሁን አዲስ መሪ አልመረጠም። በኢራን የሚደገፈው የሊባኖሱ ቡድን ሄዝቦላህ መሪ የሆኑት ሐሰን ናስራላሕ ባለፈው መስከረም ነው ቤይሩት ውስጥ የተገደሉት።

ባለፈው ዓመት ጥቅምት እስራኤል በጋዛ የከፈተችውን ጦርነት ተከትሎ የየመን ሁቲዎች በቀይ ባሕር የሚመላለሱ የእስራኤል እና ሌሎች ዓለም አቀፍ መርከቦችን ማጥቃት ጀመሩ። ሰሜን-ምዕራብ የመንን የሚቆጣጠሩት የሁቲ አማፂያን እስራኤል በጋዛ ያለውን ጦርነት እስካላቆመች ድረስ ጥቃታቸውን እንደሚቀጥሉ አስታውቀዋል።

ባለፈው ቅዳሜ የየመን አማፂያን የተኮሱት ሚሳኤል በእስራኤል መዲና ቴል-አቪቭ የሚገኝ አንድ ፓርክ ላይ ወድቋል። የሁቲ ቃል-አቀባይ በበኩላቸው በሀይፐርሶኒክ ባለስቲክ ሚሳኤል ወታደራዊ ዒላማ መምታቸውን አስታውቀዋል።

በተያያዘ ዜና በጋዛ የተኩስ አቁም ለማድረግ የሚደረገው ውይይይት ቀና መንገድ እንደያዘ የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታኒያሁ ተናግረዋል። ነገር ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስምምነቱ መቼ ሊደረስ ይችላል የሚለውን ከመናገር ተቆጥበዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።



የ62 ዓመቱ ሀኒዬ በሐማስ እንቅስቃሴ ትልቅ ቦታ ነበራቸው

## ትራምፕ ከዓለም ጤና ድርጅት አባልነት ለመውጣት እቅድ እያዘጋጁ እንደሆነ ተገለጸ

የተመራጩ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የሽግግር ቡድን አባላት አሜሪካን ከዓለም ጤና ድርጅት አባልነት ለማስወጣት እቅድ እያዘጋጁ እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡ ፕሬዚዳንቱ በመጀመርያ ቀን የሥልጣን ቆይታቸው ከሚያስተላልፏቸው ቁልፍ የፖሊሲ ውሳኔዎች መካከል ከድርጅቱ አባልነት መውጣት አንዱ ሊሆን እንደሚችል ተነግሯል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ግዙፉ የጤና ኤጀንሲ ወረርሽኞችን እና ሌሎች ዓለምአቀፋዊ የጤና ቀውሶችን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ዋሽንግተንን በማግለል ተወቅሷል፡፡ በተጨማሪም በመሰል ዓለም አቀፋዊ የጤና ጉዳዮች ከአሜሪካ ይልቅ ወደ ቻይና አድልቷል በሚልም በትራምፕ የሽግግር ቡድን ውንጀላ ቀርቦበታል፡፡

በመጀመርያ የሥልጣን ዘመናቸው ትራምፕ ከድርጅቱ አባልነት ለመውጣት ለአንድ አመት ያህል በሂደት ውስጥ ከዘለቁ በኋላ በአዲሱ የጆ ባይደን አስተዳደር ውሳኔው መሻሩ ይታወሳል፡፡ በወቅቱ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በመከሰቱ ድርጅቱ ቻይናን ተጠያቂ ለማድረግ ወደ ኋላ ብሏል። "ድርጅቱ የቻይና አሻንጉሊት ነው" በሚል በትራምፕ ተደጋጋሚ ወቀሳ ሲቀርብበት ቆይቷል፡፡

ከሳምንታት በፊት የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ቴዎድሮስ አድሀኖም በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ትራምፕ ከድርጅቱ አባልነት ለመውጣት ባሰሙት ዛቻ ዙርያ ተጠይቀው፤ አሜሪካ በአስተዳደር ሽግግር ውስጥ ስለምትገኝ ጊዜ ያስፈልጋታል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ዳይሬክተሩ "የትራምፕ አስተዳደር በድርጅቱ አሠራር ዙሪያ በሚያነሳቸው ቅሬታዎች ላይ ተቀምጦ ለመነጋገር እድል ይሠጠናል ብለን እናምናለን" ብለዋል፡፡ የተለያዩ የጤና ባለሙያዎች የአሜሪካ መውጣት የድርጅቱን አቅም እንደሚያዳክመው ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን የዓለም ጤና ድርጅት የአሜሪካን ክፍተት ለመሙላት በክትባት እና በዓለም አቀፍ የወረርሽኝ ቁጥጥር ጉዳዮች ዙርያ ወደ ቻይና የሚያዘነብል ከሆነ በጤናው ጉዳይ የዋሽንግተንን ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ሊጎዳው እንደሚችል መግለጻቸውን አል ዐይን ዘግቧል፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# የአፍሪካ አንድነት ቻርተር አርቃቂ

ክብረአብ በላቸው



ኢትዮጵያ የብዙ ስመጥር ግለሰቦች ሀገር መሆንዋ የታወቀ ቢሆንም ታሪካቸው በአግባቡ በወረቀት ላይ ተፅፎ የተመዘገበው የጥቂቶቹ ብቻ ነው:: በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችና ባገኙአቸው ዕድሎች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ዕውቀት የቀሰሙ ኢትዮጵያውያን ያገኙትን ዕውቀት ለወገኖቻቸው ለማድረስና አዳዲስ አሠራርንና አስተሳሰብን በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ለማስረጽ፣ አብዝተው የደከሙና ሕይወታቸውን አሳልፈው እስከ መስጠት የደረሱ ፋና ወጊ ምሁራን እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል።

ሀገራቸውን ከውጭ ወራሪና ጠላት በመከላከል አኩሪ ታሪክ የሠሩ፣ የሕዝባቸውን ደኅንነትና አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ መስዋዕትነት የከፈሉና አንፀባራቂ ታሪክ የሠሩ ጥቂቶች አልነበሩም:: በውትድርና፣ በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በስፖርት፣ በታሪክ፣ በሳይንስና በእምነት አስተምሮ፣ የኪነ ጥበብና የምርምር ሥራዎችም ኢትዮጵያን በዓለም የበለጠ እንድትታወቅ ያደረጉ ትናንትናም ዛሬም ደምቀው የሚታዩ ኢትዮጵያውያን ብዙዎች ናቸው::

ከላይ ለተነሳው ሃሳብ ትክክለኛው መስፈርት የሚያሟሉት መሆናቸውን ደግሞ ክቡር አቶ ተሾመ ገብረማርያም መሆናቸውን ታላላቅ ቤተሰቦቻቸው፣ ወዳጆቻቸው፣ የቅርብም የሩቅም የሥራ ባልደረቦቻቸው ይመሰክራሉ፤ እንዲሁም ታሪካቸውን ያነበበ ሁሉ የሚረዳው ነው። የክቡር አቶ ተሾመ ገብረማርያም ታሪክ እጅግ ሰፊ እና ትልቅ በመሆኑ በዚህ ተርከን የምንጨርሰው አይደለም። ነገር ግን ታላላቆች የሄዱበት፣ የሠሩት ሥራ፣ ትዕግሥት፣ ሙያ፣ ሀገርን መውደድ እና ለሕግ (እውነት) መቆምን ለቀጣዩ ትውልድ ትምህርት እና አርአያ በመሆኑ ዛሬ ልናነሳቸው ወደድን።

ክቡር አቶ ተሾመ ገብረማርያም ከአባታቸው ከባላምባራስ ገብረ ማርያም ቦካን እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ላቀች አብቹ በአዳማ ከተማ ልዩ ስሙ ሰቀቀሎ ተብሎ በሚታወቀው ስፍራ በ1923 ዓ.ም ተወለዱ::

ህፃኑ ተሾመ ከተወለደ ከአምስት ዓመት በኋላ ሀገራችን የኢጣልያ ወረራ ስለገባ የፋሺስቶችን ግፍና ጭቆና ለማምለጥ ወላጆቹ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ አብረው በመንከራተት የህፃንነት ጊዜያቸውን አሳልፈዋል:: የፋሽስት ጦር ድል ተመትቶ በኢትዮጵያ ነፃነት ሲመለስ አባታቸው የሲዳሞ ገዢ ሆነው በተሾሙበት በራስ አደፍርሰው ሥር በመመደባቸው ህፃን ተሾመም ከ1935ዓ.ም ጀምሮ ሲዳማ ይርጋ ዓለም በምትባለው ቦታ መኖር ጀመረ::

በ1937ዓ.ም ቀ.ኃ.ሥ የሲዳሞን ጠቅላይ ግዛት በሚጎበኙበት ወቅት በአቶ ቦጋለ ዋለሉ አቅራቢነት 12 ታዳጊዎች በግርማዊ ጃንሆይ ለትምህርት ወደ አዲስ አበባ እንዲሄዱ ሲወሰን አቶ ተሾመም ከተመረጡት ውስጥ አንዱ ነበረ:: በዚሁ መሠረት ዕድለኞቹ ተመራጮች በቀጥታ ቤተ መንግሥት ተወስደው ለተወሰኑ ቀናት እዚያው ከተቀመጡ በኋላ ለሁሉም አልጋ፣ ፍራሽ እና አልባሳት ተሟልቶላቸው በአዳሪነት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ወደ ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ተልከዋል::

ወጣቱ ተሾመ በተፈሪ መኮንን ት/ቤት ትምህርቱን በትጋት ከመከታተሉም በተጨማሪ በስፖርት ጭምር ታዋቂነት ካተረፉት ከነአቶ ንጉሤ ፍትህ አወቀ እና ፕሮፌሰር መስፍን ከመሳሰሉት ግንባር ቀደም ተማሪዎች መካከል አንዱ ነበረ:: ወጣቱ ተሾመ በተፈሪ መኮንን ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን በተከፈተው ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከገቡት የመጀመሪያ ተማሪዎች መካከል አንዱ በመሆን የባችለር ዲግሪውን በአስተዳደር ዘርፍ በማዕረግ ተቀብሏል::

ጠላት ሀገራችንን ወሮ ኢትዮጵያ ነጻ ከወጣች ከዘጠኝ ዓመት በኋላ በሀገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲ ለመክፈት ላይ ታችትል ነበር:: ያኔም ተፈሪ መኮንን ፤ ከጄኔራል ዊንጌት፤ ከዳግማዊ ምኒልክ ከሌሎችም የተውጣጡ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እንዲገቡ ተደርጎ ነበር:: አብዛኞዎቹ ከተፈሪ መኮንን ነበሩ::

ከተፈሪ መኮንን በጊዜው ወደ ዩኒቨርሲቲ የገቡ ተማሪዎች ቁጥር 72 ይጠጋ ነበር:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ወይም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አቶ ተሾመ በተመረቁበት ጊዜ 13 ተማሪዎችን አስመርቆ ነበር:: አቶ ተሾመን ጨምሮ እነዚህ 13 ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በመመረቅ የመጀመሪያዎቹ ሲሆኑ ተማሪዎቹ የተመረቁት በ1946 ነበር::

ከመጀመሪያዎቹ ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፦ ዶክተር አክሊሉ ሀብቴ፤ ዶክተር መንገሻ ገብረህይወት፤ ዶክተር ሀብተማሪያም ማርቆስ፤ ጌታቸው መድሃኔ፤ መሐመድ አብዱራህማን ፤ መሐመድ ሃሚድ ፤ ጌታቸው ክብረት፤ በላቸው አስራት እና ራሳቸው አቶ ተሾመ ገብረማሪያም ነበሩ::

በመቀጠል ለሁለተኛ ዲግሪ ወደ ካናዳ በመሄድ በታዋቂው የመጊል ዩኒቨርሲቲ ኤም ሲ ኤል ማለትም ማስተርስ በኮምፓራቲቭ ሎው ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቀው ወደ እናት ሀገራቸው ከተመለሱት የመጀመሪያዎቹ ወጣት ኢትዮጵያውያን መካከል አቶ ተሾመ አንዱ ነበር::

**የዛሬው የአፍሪካ ኅብረት የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመመሥረቻ ቻርተርን ካረቀቁት አንዱ ነበሩ። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሠረት አቶ ተሾመ ከፍተኛ የሕግ ድጋፍ አድርገዋል**

አቶ ተሾመ ትምህርታቸውን በ1950 አጠናቀው ከተመለሱ በኋላ፦

- ከ1950-1952 በመገናኛ ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና የሕግ አማካሪነት፤
- በ1953 በሥራ ሚኒስቴር በዋና ዳይሬክቶሬትነት፤
- 1954 በልማት ባንክ ዋና የሕግ አማካሪነት፤
- በ1955 የአፍሪካ አንድነት ማኅበር ቻርተር አርቃቂ ኮሚቴ አባልነት፤
- በ1957-1959 የኢትዮጵያ ጠቅላይ አቃቤ ሕግነት፤
- በ1959- 1966 በማዕድን ሚኒስቴር ሚንስትር ዴኤታነት::

በእነዚህ ዘመናት ክቡር አቶ ተሾመ በበርካታ የሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር በተካሄዱ ስብሰባዎች ላይ እየተገኙ ሀገራችንን በመወከል የጥናት ጽሑፎችን አቅርበዋል፤ በሳል ንግግሮችን አድርገዋል፤ ሀገራቸውን ወክለው በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ በገላጋይ ሽማግሌዎች ፊት በቀረበ ዓለም አቀፍ ክርክር ላይ ገጥመው የረቱበት አጋጣሚ አለ::

በተጨማሪም ታዋቂው የፍትሐ ብሔር ሕጋችን አርቃቂ የነበረው ፕሮፌሰር ሬኔ ዳቪድ በተሳተፈበት ዓለም አቀፍ ስብሰባ ላይ ሀገራቸውን ወክለው ተሳትፈዋል::

በተለይ የሥራ ሚኒስቴር በነበረበት ወቅት የአየር መንገድ የቦርድ ሰብሳቢ የነበሩት የወቅቱ የሥራ ሚኒስቴር ክቡር ደጃዝማች መንገሻ ስዩም (ልዑል ራስ) አየር መንገዱን ለማሳደግ ያደርጉት የነበረውን ጥረት ተገቢውን የሕግ ምክር በመስጠት ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል::

በዚህም ምክንያት አየር መንገዱ ከባለ ሞተር አውሮፕላን ወደ ጀት እንዲሸጋገር በቦርዱ ሰብሳቢ የተጀመረው ውጥን እውን በማድረግ የመጀመሪያውን 707 ቦይንግ ከክቡር ሚንስትሩ ጋር አሜሪካን ሀገር በመሄድ ተረክበዋል:: ክቡር አቶ ተሾመ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጠቅላይ አቃቤ ሕግም ሆነው ለ3 ዓመታት ያህል አገልግለዋል::

የዛሬው የአፍሪካ ኅብረት የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመመሥረቻ ቻርተርን ካረቀቁት አንዱ ነበሩ። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሠረት አቶ ተሾመ ከፍተኛ የሕግ ድጋፍ አድርገዋል። በማዕድን ሚኒስቴር በነበሩ ጊዜም ከፍተኛ ሥራ በመሥራት ትልቁ የተፈጥሮ ጋዝ የተገኘውም እርሳቸው በግንባር ቀደምትነት ባደረጉት ድርድር ነው። በዚህ ዓይነት ሥራቸውን ሲሠሩ እያሉ በ1966 አብዮት ሲከሰት እሳቸውም የቀድሞው ሥርዓት ባለሥልጣን በመባል ከ1967-1976ዓ.ም ድረስ ለ9 ዓመት በእሥራት ቆይተዋል።

የቀድሞው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማሕበር ፕሬዚዳንት አቶ ወንድማገኘሁ ገ/ሥላሴ የሀገሪቱን የማዕድን አዋጅ የተሟላ ለማድረግ አቶ ተሾመ ላቅ ያለ ሚና ተጫውተዋል ሲሉ ይናገራሉ። «ከ1928 ዓ.ም. ጀምሮ የፕላቲኒየም፤ ወርቅ እና ማዕድናት ፍለጋን የተመለከቱ የተለያዩ የተቆራረጡ ሕግጋት ነበሩ።» የሚሉት አቶ ወንድምአገኘሁ አቶ ተሾመ የማዕድን ሚኒስቴርን ከተቀላቀሉ በኋላ የተሟላ አዋጅ ገቢራዊ እንዲሆን አድርገዋል ሲሉ ተናግረዋል።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የልጅ ልጅ የሆኑት ልዑል በዕደማርያም መኮንን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመመሥረቻ ቻርተር ዝግጅት ላይ አቶ ተሾመ በጊዜው ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ከነበሩት አቶ ከተማ ይፍሩ እና አቶ ክፍሌ ወዳጆን ከመሳሰሉ ባለሙያዎች ጋር ላቅ ያለ ሚና መጫወታቸውን ተናግረዋል።

ልዑል በዕደማርያም በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የደርግ የአስተዳደር ሥርዓት ላይ የሰላ ትችት የሚሰነዝሩት አቶ ተሾመ ከቀዳማዊ ኃይለስላሴ ባለስልጣናት ጋር ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በእስር ላይ መቆየታቸውን ያስታውሳሉ። በንጉሳዊው ሥርዓት-መንግሥት ውስጥ በባለሥልጣንነት በማገልገላቸው ምክንያት ለእስር የተዳረጉት አቶ ተሾመ በወታደራዊ ፍርድ ቤት ቀርበው በነፃ እንዲለቀቁ ቢወሰንላቸውም ሳይፈቱ መቅረታቸውን ልዑል በዕደማርያም መኮንን ተናግረዋል።

አቶ ተሾመ ገብረማርያም በስማቸው ባቋቋሙት የጥብቅና ተቋም እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የማማከር አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል። ከእስር በተፈቱ ማግሥት በፖለቲካ እና ሕግ አማካሪነት የተሰጣቸውን ሥራ ጥለው በጥብቅና ሙያ የተሰማሩት አቶ ተሾመ የአፍሪካ ሀገራት የማዕድን ዘርፍን አስመልክቶ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ያማክሩ ነበር። ልዑል በዕደማርያም፤ አቶ ተሾመን «ስኬታማ» ሲሉ ይገልጿቸዋል።

የቀድሞው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማሕበር ፕሬዚዳንት አቶ ወንድምአገኘሁ ገ/ስላሴ አቶ ተሾመ በተደጋጋሚ ለተሻሻለው የኢትዮጵያ የማዕድን አዋጅ አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ ቆይተዋል ሲሉ ይናገራሉ። የውጭ የማዕድን ኩባንያዎችን ወደ ኢትዮጵያ ይጋብዙ እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ ወንድማአገኘሁ ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማሕበር መጠናከር ድጋፍ ያደርጋሉ ይሏቸዋል።

አቶ ተሾመ ገብረማርያም የራሳቸውን የጥብቅና ፈቃድ በማውጣት የራሳቸውን የጥብቅና ቢሮ ከፍተው ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገር ደንበኞች የሕግ አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። አቶ ተሾመ ገብረማርያም ዓለም አቀፍ የጠበቆች ማህበር(IBA)፣ ALN የተባለ የ11 ሀገሮችን ጠበቆች የሚያስተባብር ማህበር፣ የኢትዮጵያ ጠበቆች ማህበር እና ከሌሎች በርካታ የውጭ የሙያ ማህበራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ቢሮአቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ ግንባር ቀደም የሆነ ማድረግ ችለዋል።

በሥራ ዓለም ከ50 ዓመታት በላይ የዘለቁት አቶ ተሾመ ገብረማሪያም ከባለቤታቸው ከወይዘሮ አምሳለ መኮንን ፤ ወሰንየለሽ ተሾመን ወልደዋል:: አቶ ተሾመ በታኅሣሥ 2009 በናሚቢያ ለሥራ ባቀኑበት ሰዓት ድንገት በመታመማቸው ሐሙስ ሌሊት ታኅሣሥ 6 ፤ 2009 ዓ.ም ሕይወታቸው ሊያልፍ ችሏል:: የቀብር ሥነ ሥርዓቱም ረቡዕ ታኅሣሥ 12 ቀን 2009 ዓ.ም በቅድስት ሥላሴ መንበረ ጸባኦት ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል።

እኛም በዚህ ለሕዝብና ሀገራቸው መልካም ያደረጉና በተሰማሩበት ዘርፍ ሁሉ የማይነጥፍ ዐሻራ ማኖር የቻሉ ግለሰቦች ታሪክ አንስተን ለአበርክቷቸው ክብር በምንሰጥበት የባለውለታዎቻችን አምድ እውቁን የሕግ ምሁርና የኢትዮጵያ ባለውለታ አቶ ተሾመ ገብረማርያምን ላበረከቱት ዘመን ተሻጋሪ ሥራ አመሰገን። ሰላም!

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ዘመን
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የዋልያዎቹን የቻን ተሳትፎ የሚወስነው ፍልሚያ

ብርሃን ፈይሳ

በሀገር ውስጥ ሊጎች በሚሳተፉ ተጫዋቾች ብቻ የሚካሄደው የአፍሪካ ሀገራት ዋንጫ (ቻን) ከሁለት ወራት በኋላ በምስራቅ አፍሪካውያኑ ሀገራት አዘጋጅነት ይካሄዳል። ዩጋንዳ፣ ታንዛኒያ እና ኬንያ በጥምረት ለ8ኛ ጊዜ በሚያደርጉት በዚህ ውድድር ላይም 19 ሀገራት ተሳታፊ ናቸው። ከእነዚህ ሀገራት መካከል ለመሆንም ሀገራት የማጣሪያ ጨዋታዎቻቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

በማጣያው ተሳታፊ ከሆኑት ቡድኖች መካከል አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን (ዋሊያዎቹ) ዛሬ ከሱዳን አቻቸው ጋር ወሳኙን የመልስ ጨዋታቸው ያከናውናሉ። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ከሱዳን አቻው ጋር የሚያደርገው ጨዋታ በሊቢያ ቤንጋዚ መካሄዱ የሚታወስ ነው። ሁለቱ ጎረቤት ሀገራት በተገናኙበት ጨዋታም የሱዳን ብሄራዊ ቡድን ሁለት ለምንም በሆነ ውጤት የኢትዮጵያ አቻውን ማሸነፉ የሚታወቅ ነው። ሱዳኖች ከፍተኛ የማለፍ ተስፋ ይዘው በወጡበት ጨዋታም ያሲር ሞዛሚል እና ሙሳ ካንቲ በ7ኛው እና በጭማሪ ሰዓት ግቦቹን አስቆጥረዋል።

ኢትዮጵያ የምትገኝበት የመካከለኛው ምስራቅ ዞን 10 ሀገራት በማጣሪያው ይሳተፋሉ ተብሎ ቢጠበቅም ኤርትራ እና ሶማሊያ ተሳታፊነታቸውን በመሰረዛቸው ምክንያት ተጋጣሚዎቻቸው ብሩንዲ እና ኢትዮጵያ ሁለተኛውን ዙር ሊቀላቀሉ ችለዋል። በመጀመሪያው ዙር ከታንዛኒያ ጋር የደረሰው የሱዳን ብሄራዊ ቡድን በበኩሉ በደርሶ መልስ ጨዋታ አንድ እኩል በመለያየቱ በፔናሊቲ 6ለ5 በሆነ ጠባብ ውጤት ነበር ሁለተኛውንና የመጨረሻውን የማጣሪያ ዙር ሊቀላቀል የቻለው።



ዋልያዎቹ በቻን ለመሳተፍ ዛሬ ሱዳንን ቢያንስ 3ለ0 ማሸነፍ አለባቸው፣

ሁለቱም የደርሶ መልስ ጨዋታ በገለልተኛ ሜዳ በሊቢያ ቤንጋዚ የሚካሄድ ሲሆን፣ በመጀመሪያ ጨዋታ ኢትዮጵያ ባለሜዳ እንደመሆና በዝግ ስቴድየም ማድረጓ የሚታወስ ነው። በዛሬው ጨዋም በዚያው በቤኒና ማርቲየርስ ስታዲየም የሚደረግ ይሆናል። የዋልያዎቹ ጊዜያዊ ዋና አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ ተደጋግሞ የሚነሳውን የዋልያዎቹ የአጥቂ መስመር ተጫዋቾች ችግር ለመቅረፍ በዝግጅት ወቅት መሥራታቸውን ቢገልጹም በመጀመሪያው ጨዋታ የታየው ግን በተቃራኒ ነበር። ዛሬ በሚኖረው የሁለቱ ቡድኖች ጨዋታም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ሶስትና ከዚያ በላይ ግቦችን በተጋጣሚው ላይ በማስቆጠር ውጤቱን መቀልበስ ካልቻለ የቻን ተሳትፎ ያከትማል።

ኢትዮጵያ ሱዳንን የምትገጥመው በመድረኩ ለአራተኛ ጊዜ ለመሳተፍ መሆኑ ይታወቃል። በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን ስር የሚገኙ ስድስት ዞኖች የማጣሪያ ውድድራቸውን እያደረጉ ያሉ ሲሆን፤ ከታህሳስ 11-13/2017ዓ/ም እንዲሁም ከታህሳስ 18-20/2017 ዓ/ም ጨዋታዎቻቸውን ያከናውናሉ። ከየዞኑም ሶስት ሶስት ሀገራት የአፍሪካ ሀገራት ዋንጫን (ቻን) የሚቀላቀሉ ሲሆን፤ በመካከለኛው ምስራቅ አፍሪካ ዞን የውድድሩ አዘጋጅ የሆኑት ሶስቱ ሀገራት (ዩጋንዳ፣ ታንዛኒያ እና ኬንያ) በቀጥታ ማለፋቸውን ተከትሎ በማጣሪያው አንድ ሀገር ብቻ ለማለፍ ፍልሚያውን ያደርጋል።

ኢትዮጵያ በመጀመርያው የመድረኩ ተሳትፎ የምድብ ማጣርያ ሶስት ጨዋታዎችን አድርጋ ያለምንም ነጥብ በአራት የጎል እዳዎች ነበር የተሰናበተችው። በ2016 ርዋንዳ አስተናጋጅ በነበረችበት ውድድር ዴሞክራቲክ ኮንጎ ለሁለተኛ ጊዜ ቻምፒዮን ስትሆን፣ የኢትዮጵያ ተሳትፎ በአንድ ነጥብ ከምድቧ በመሰናበት ነበር ያጠናቀቀችው።

ከሁለት ዓመት በፊት በአልጄሪያ በተስተናገደው የቻን ውድድር ሶስተኛ ተሳትፎዋን ያደረገችው ኢትዮጵያ በተመሳሳይ አንድ ነጥብ ይዛ ከምድቡ ተሰናብታለች። ከምድብ ማጣሪያ ያልዘለለው የኢትዮጵያ የመድረኩ ተሳትፎ፣ ዘንድሮ ለአራተኛ ጊዜ ለመሳተፍ በሚደረገው የማጣርያ ጨዋታ ከዞኑ ጠንካራ ሀገራት መካከል አንዷ በሆነችውና ለቀጣዩ የአፍሪካ ዋንጫ ማለፋን ባረጋገጠችው ሱዳን ይፈተናል።

## ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

### ከአካባቢ ብክለትና መራቆት የጸዳ የአመራረት ሥርዓት ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት አንዱ መስፈርት

ሶሎሞን በየነ

በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ ዓለም ለምርትና ምርታማነት መዋዠቅ፣ ለድንገተኛ ተፈጥሯዊ አደጋ (ጎርፍ፣ አውሎ ንፋስ)፣ ለጤና መቃወስ፣ ለድርቅ … ወዘተ ህልቆ መሳፍርት ለሌለው ችግሮች ተጋልጣለች። ምድርም በአስፈሪ ሁኔታ እየሞቀች መጥታለች። ታዲያ በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን መላው ዓለምን ከሚያሳስቡ ሁነቶች አንዱና ቀዳሚው የአየር ንብረት ለውጥ ነው።

የሀገራት መሪዎች በተለያየ ጉባዔ በዚህ ጉዳይ ላይ ይመክሩበታል። አተገባበሩ ላይ ዳተኝነት ቢታይም መፍትሄ ይሆናሉ የተባሉ ውሳኔዎችንም ሲያሳልፉ ይስተዋላል። ሀገራትም መፍትሄ ይሆናል ያሉትን ርምጃ እየወሰዱ ይገኛሉ። የመፍትሄ ሃሳቦቹ በተጨባጭ መሬት ላይ ወርደው ችግሩን በዘላቂነት እንዲፈቱ ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፍ ጭምር ተዘጋጅቶላቸው ተፈፃሚ እየሆኑ ነው።

የአየር ንብረት ለውጥ ችግሩን ለማቃለል ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተቀብሎ እየተገበራቸው ከሚገኙ ሕጎች አንዱ፤ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከአካባቢ ጋር ተስማሚ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሂደት መከተል እንዳለባቸው በሕግ ተደንግጓል። ሀገራትም ለዚህ ሕግ ተፈፃሚነት ያላቸውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ እያሳዩ ነው።

በቅርቡ የአውሮፓ ሕብረት ባሳለፈው ውሳኔ የአካባቢ ብክለትና መራቆት የሚያስከትል ምርት ሕብረቱ እንደማይቀበል አሳውቋል። ከዚህ አኳያ በዓለም ገበያ ላይ ሰብሮ ለመግባት የተወዳዳሪነት አንዱ መስፈርት የሆነውን ከአካባቢ ጋር ተስማሚ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሥርዓት የማይከተሉ አምራች ኢንተርፕራይዞች ምርታቸው በዓለም ገበያ ላይ ተቀባይነትና ቦታ አይኑረው ማለት ነው።

ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የአነስተኛና መካከለኛ ፋይናንስ ፕሮጀክት አምራች ኢንተርፕራይዞች ከአካባቢ ብክለትና መራቆት የጸዳ የአመራረት ሥርዓት በመከተል ምርታቸው በዓለም ገበያ ላይ ተፈላጊ፣ ተወዳዳሪ እንዲሁም ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ደህንነት ባለሙያዎች ከአካባቢ ጋር የተስማማና ደህንነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሂደት ዙሪያ ሥልጠና ሰጥቷል፡፡

በሥልጠናው ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዋና ዳይሬክተር አለባቸው ንጉሤ (ዶ/ር) አምራች ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቱበት አካባቢ ከተፈጥሮ ጋር የተስማማ እንዲሁም ደህንነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሂደት እንዲከተሉ ማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ምርታቸው ተወዳዳሪነቱን እንደሚያሳድገው ገልፀዋል፡፡

በተለይ ምርታቸውን ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ አምራች ኢንተርፕራይዞች የአመራረት ሂደታቸው ወይም ሥርዓታቸው ከተፈጥሮና አካባቢ ጋር ተቃርኖ ያለው ከሆነ ኢትዮጵያን ጨምሮ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የተቀበለውን ጤናማ የአመራረት ሕግ የሚጥስ በመሆኑ በየትኛውም ሀገር ምርታቸው ተቀባይነት እንደማይኖረው የሚናገሩት ዋና ዳይሬክተር አለባቸው (ዶ/ር)፤ የክልልና ከተማ አስተዳደር በዘርፉ የሚሠሩ መሥሪያቤቶች የአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞችን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ከአካባቢ ጋር ተስማሚ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሂደት መከተል እንዲችሉ አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል። በአንጻሩ ኢንተርፕራይዞች ደግሞ በበኩላቸው ከባለሙያዎች የሚሰጣቸውን ትምህርት ወደ መሬት በማውረድ ከተፈጥሮ ጋር ተስማሚና ደህንነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሂደት ሊከተሉ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በሥልጠናው ማጠቃለያ ላይ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዱልፈታ የሱፍ በበኩላቸው የአካባቢውን ማህበረሰብ እየበከለ የሚያተርፍ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዝ ለጊዜው ቢያተርፍም በሂደት መክሰሙ አይቀሬ መሆኑን አመላክተው፤ ከወዲሁ ከአካባቢ ጋር ተስማሚ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሂደት በመከተል ተረፈ ምርትን መልሶ በመጠቀም ወደ አካባቢ በካይ ተረፈ ምርቶች እንዳይለቀቁ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ከአካባቢ ጋር ተስማሚ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሥርዓት መከተል ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት አንዱ መስፈርት መሆኑን አቶ አብዱልፈታ ጠቁመው፤ ይህንን የአመራረት ሥርዓት የማይከተሉ አምራች ኢንተርፕራይዞች ምርታቸው በገበያው ላይ ተቀባይነት የለውም። ከዚህ ቀደም በሚያመርቱበት አካባቢ ያለውን ማህበረሰብ እሴትና ባህል ማዕከል ማድረግ ያቃታቸውና ከገበያ የወጡ ኢንዱስትሪዎችን በምሳሌነት በመጥቀስ ጭምር አስረድተዋል።

ስለዚህ ከአካባቢ ብክለትና መራቆት የጸዳ የአመራረት ሥርዓት መከተል ከአምራች ኢንተርፕራይዞች በላይ ሊያሳስበው የሚገባ አካል የለም ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሥልጠናውን የወሰዱ የዘርፉ የክልልና ከተማ አስተዳደር አመራሮችና ባለሙያዎች በሥልጠናው ያገኙትን እውቀት ወደ አምራች ኢንተርፕራይዞች ማውረድ እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

በቀጣይ በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ሲተገበር በስፋት ኢንተርፕራይዞች ይቋቋማሉ። ይህንን ተከትሎ ኢንተርፕራይዞች የአካባቢ ተፅእኖ እንደማይፈጥሩ በማረጋገጥ ኢትዮጵያ በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም ያስቀመጠችውን አረንጓዴና ዘላቂ ኢንዱስትሪያላይዜሽን የመገንባት ግብ ለማሳካት የተቋሙ ሠራተኛ የራሱን ዐሻራ ማኖር ይገባል ሲሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አብዱልፈታ የሥራ መመሪያ ሰጥተዋል።

አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች የአካባቢ ደህንነትን ታሳቢ ያደረገ የአመራረት ሥርዓት እንዲከተሉ በቅድሚያ የዘርፉን አስፈጻሚ አካላት አቅም መገንባት ያስፈልጋል ያሉት ደግሞ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተ አቶ ጳውሎስ በርጋ ናቸው።

እርሳቸውም፤ የዘርፉን አስፈጻሚ አካላት አቅም ለመገንባት ሥልጠናው መዘጋጀቱን ጠቁመው፤ በቀጣይ የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት ከሥልጠናው ያገኙትን ልምድ እና እውቀት እንደ ግብዓት በመጠቀም ለአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች አካባቢን በማይበክል የአመራረት ሥርዓት ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት በትኩረት መሥራት እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል፡፡

የሥልጠና ተሳታፊዎች በበኩላቸው ከአካባቢ ብክለትና መራቆት የጸዳ የአመራረት ሥርዓት ዙሪያ ያሉ ዓለምና ሀገር አቀፍ ሕጎችና አሠራሮች በሚመለከት ጥሩ እውቀትና ተሞክሮ ማግኘታቸውን ገልጸው፤ ይህም ከአካባቢ ጋር ተስማሚ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሂደት ዙሪያ በቀጣይ በበለጠ ጠንክረውና ትኩረት ሰጥተው እንዲሠሩ እንደሚያግዛቸው ተናግረዋል፡፡

በስልጠናው የዓለም ባንክ የአካባቢና ማህበራዊ ጥበቃ ማዕቀፍ፣ የአባባቢና ማህበራዊ ጥበቃ አያያዝ፣ ዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ድጋፍ፣ ሪፖርት አዘገጃጀት፣ የተፅኖ አለካከ (impact assessment) እና መሠል ጉዳዮች ተካተዋል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ